# አል-ሂጅራ

## እስላማዊ የስደት አስተምህሮ

*ነፃነትን መቀበል ወይንስ እስልምናን በኃይል መጫን?*

*ሳም ሶሎሞን እና ኢ. አል መቅዲሲ*

# አበርክቶት

የኛ ተቃውሞ ያነጣጠረው ጎረቤቶቻችን በሆኑት ሙስሊም ግለሰቦች ላይ አይደለም፡፡ ይልቁኑ የሕግ ሥርአት ተቋም በሆነው እና ለማንኛውም ሃገር ወይንም ከእስልምና ንፅረተ ዓለም ውጪ ለሆነ ለማንኛው ንፅረተ ዓለም ታማኞች እንዳይሆኑ በመላው ዓለም ሙስሊም ያልሆኑ ሃገራት ውስጥ የሚገኙ ራሳቸውን ያገለሉ ማሕበረሰቦች ወኪል ሆኖ በሚሰራው እየገዘፈ በመጣው እስላማዊ ፍላጎት ላይ እንጂ፡፡

እየጨመረ የመጣውን ስደት፣ ራስን ከሌላው ሕብረተሰብ መነጠል እና ከዚህም የተነሳ ሙስሊም ባልሆኑት ሃገራት ውስጥ የተከሰተውን የሙስሊሞች ተፅዕኖ በተመለከተ ቀዳሚው የማንቂያ ደውል ድምፅ የተሰማው የግብፅ ተወላጅ ከሆኑት ባት ዬኦር ከተሰኙ አይሁዳዊት ሊቅ ነበር፡፡ ከትላንትናው በመነሳት የነገውን መተንበይ ያስችላቸው ዘንድ እስልምና የተለያዩ ማሕበረሰቦችን ሙሉ በሙሉ እንዴት እንደዋጠ ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን ታሪክ በማጥናት አሥርተ ዓመታትን አሳልፈዋል፡፡ ጦርነትን በማወጅ ወይንም ደግሞ ተሰደው በመምጣት ራሳቸውን በመነጠል በሚኖሩት ሙስሊሞች ቁጥር ኃይል በመጠቀም አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ወደ ዚሚ ደረጃ

በማውረድ ወይንም በቆየው አባባል በመሳርያ ኃይል - በሰይፍ በሚደረግ ጂሃድ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

ዩረቢያ፡ የአውሮፓና የአረብ ዛብያ የተሰኘው የባት ዬኦር የቅርብ ጊዜ መጽሐፍ እንዲሁም ይህንን ርዕስ የተመለከቱት ሌሎች መጻሕፍታቸው ያለፈውን ታሪክ እንዲሁም የእስልምናን አካሄድ እና ግብ በጥልቀት በመተንተን በተለይም በአውሮፓና በአሜሪካዎች በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ እየሆኑ የሚገኙትን እውነታዎች በመዘርዘር ያጠቃልላሉ፡፡ የእርሳቸውን እግር ተከትለው ለወጡት ሰዎች የተሰሚነት መሰረት ስለሆኑት ምሑራዊ ትንተናዎቻቸው፣ ፅናታቸው እና ለእውነት እና ለነፃነት ስላላቸው ጥልቅ ፍቅር አድናቆታችን የላቀ ነው፡፡

እኚህ ሴት በአውሮፓ ውስጥ ለፍርሃት መንገድ የከፈቱትን፣ የዚሚን ደረጃ ወደ መቀበል ያመሩትን፣ የንግግር፣ የእምነት እና የህሊና ነፃነቶችን አደጋ ላይ የጣሉትን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የሚከተሉትን የማመቻመች ድምፆች ተቃውመዋል፡፡

ይህንን ሥራ ለባት ዬኦር እናበረክታለን፡፡

በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ… ይህንን መጽሐፍ የምናበረክተው

ስለ ጥንካሬያቸው እና በዚህ ጉዳይ ላይ ደፍረው በመጻፋቸው እንዲሁም በግልፅ በመናገራቸው ለባሮነስ ኮክስ እና ለፕሮፌሰር ጆን ማርክስ፤

ለዚህ ጉዳይ ራሳቸውን በመስጠታቸው፣ ምንም የሚታይ ነገር በሌለበት ጊዜ የሕዝብ ቁጥር ለውጡን እና የሚያስከትለውን አደጋ በመተንበይ የተለመደውን እውቀት በመገዳደራቸው ለዶ/ር ፓትሪክ ሱክሄዶ፤

በብዕር ኃይል በመጠቀም ምቾት የማይሰጡትን እውነታዎች ያለፍርሃት ለሕዝብ ዓይን ግልፅ በማድረጋቸው ለሜላኒ ፊሊፕስ እናበረክታለን፡፡

በአውሮፓ ውስጥ.... የኃይል ጥቃት ዛቻን በመዋጋት የሕዝብን ጥቅም ከግል ጥቅማቸው በማስቀደማቸው ምክንያት ለጊርት ዊልደርስ እናበረክታለን፡፡

በመጨረሻም የይሁዶ-ወክርስቲያን ውርሶቻችንን ከጥቃት ለሚከላከሉት ሁሉ እናበረክታለን፡፡

ሳም ሶሎሞን እና ኤልያስ አል መቅዲሲ

እኛ ደራሲያን አብረውን ለቆሙት፣ ታማኝ በሆነው ምልጃቸው እጆቻችንን ለያዙት እና አትኩሮት እንዲኖረን ላደረጉት ሁሉ በቃላት ሊገለፅ የማይችለውን ልባዊ አድናቆታችንን እንገልፃለን፡፡

በማንበብ አስተያየቶቻቸውን የለገሱንን ሁሉ ለማመስገን እንወዳለን፡፡ ይህንን ጽሑፍ ያጎለበተው የእነርሱ ቀና ሂስ ነውና፡፡

በዚህ አስቸጋሪ ጉዞ ወቅት እገዛ ላደረጉልን እና ድጋፍ ለቸሩን ሁሉ ጥልቅ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

መቼም ቢሆን አስባችሁ ከማታውቁት በላይ በረከታችሁ የበዛ ይሁን፡፡

*ደራሲያኑ*

ሳም ሶሎሞን እና ኢ. አል መቅዲሲ፣ አል ሂጅራ፡ እስላማዊ የስደት አስተምህሮ - ነፃነትን መቀበል ወይንስ እስልምናን በኃይል መጫን? ህዳር 2008

ሳም ሶሎሞን እና ኢ. አል መቅዲሲ ይህንን መጽሐፍ በማሳተም ለአጠቃላዩ የምዕራብ ማሕበረሰብ ትልቅ አገልግሎት አበርክተዋል፡፡ ካላቸው የእስላማዊ ምንጮች እውቀት በመነሳትም በመሐመድ ምሳሌነት ላይ የተመሰረተውን የእስልምና ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የበላይነት ወደ አዳዲስ አካባቢዎች በማንኛውም መንገድ መስፋፋት አለበት የሚለውን ሰፊ ከሆነው የእስላማዊ የጂሃድ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘውን የእስልምና የስደት አስተምህሮ (ሂጅራ) ወቅታዊ አስፈላጊነት አስቀምጠዋል፡፡

ደራሲያኑ ሙስሊሞች ወደ ምዕራብ የሚሰደዱት ለኢኮኖሚያዊ እና ለግል ጉዳዮች እንደሆነ መቀበላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈጥሮው የእስልምና አስተምህሮ፣ ትውፊት፣ ልምምድ፣ ኃይማኖታዊ ተቋም እና አስተሳሰብ ተበታትነው የሚገኙትን ስደተኞች ራሳቸውን እንዲነጥሉ በማድረግ በሚሰፍሩባቸው አዳዲስ ሃገራት የሚገኙትን ሙስሊም ያልሆኑ ማሕበረሰቦች ፖለቲካዊ እና ባሕላዊ ሥርኣት እንዴት እንዲገዳደሩ እንደሚያደርጋቸው በግልፅ አሳይተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የአስተናጋጁ ማሕበረሰብ መስለም ሊቀር የማይችል ጉዳይ ነው፡፡

በምዕራብ ሃገራት ውስጥ የሚኖሩት ሙስሊሞች አናሳ እንደመሆናቸው መጠን ስላሉበት ሁኔታ ሁለት የተለያዩ ምርጫዎችን ይጋፈጣሉ፡፡ ስለ ሂጅራ እና በአሁኑ ዘመን እንደ ሞዴል ለሚኖረው የአስፈላጊነት ደረጃ ባላቸው አመለካከት ላይ ተመስርቶ፤ አናሳ የሆኑት ሙስሊሞች ግባቸው ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ጋር በመቀላቀል መኖር መሆኑን ሊወስኑ ይችላሉ ወይንም ደግሞ እስላማውያን የሚያቀነቅኑትን የሂጅራ ሞዴል በመቀበል በምዕራብ የሚገኘውን ማሕበረሰባቸውን ለደር *አል-ኢስላም* (የኢስላም ቤት) መስፋፋት እንደ መሸጋገርያ ድልድይ ሊቆጥሩት ይችላሉ፡፡

ምዕራቡን የማስለም እቅድ በደረጃ የተከፋፈለውን የመሐመድ *ሂጅራ* እንደ ምሳሌነት ይጠቀማል፡፡ ግቡንም ለመምታት የሚያስችሉ የተለያዩ ደረጃዎችን ያስቀምጣል፡፡ የኃይል ገፅታውን የማንቀሳቀሻ ጊዜ የሚደርሰው እስላማዊው እንቅስቃሴ ሙስሊም ያልሆነውን መንግሥት በመገልበጥ በእስላማዊ መንግሥት የመተካት በቂ አቅም ሲኖረው ነው፡፡ ከሙስሊም አናሳዎች የሚመጡ ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው *በሂጅራ* መነፅር ነው፡፡

ስደት ሰላማዊ እና ነውጠኛ የሆኑ አካሄዶችን የመጠቀም እምቅ አቅምን ያካትታል፡፡ በቅርቡ *በሌሞንድ ዲፕሎማቲኬ* ላይ የወጣ አንድ መጣጥፍ የመሐመድ ስደት ዛሬ ለሚገኙት ነውጠኛ ጂሃዳውያን ያለውን አስፈላጊነት በተመለከተ የሚከተለውን ብሏል፡

> የጂሃዳውያንን ባሕል ለመረዳት ሁለት ቁልፍ የሆኑ ነጥቦች አሉ፡፡ ለጂሃድ ወደ ውጪ ሃገራት መሄድ ብዙ ጊዜ ስደት ወይንም በአረብኛ ሂጅራ በመባል ይታወቃል፡፡ በ622 ዓ.ም. መሐመድ እና ተከታዮቹ ከመካ ወደ መዲና ያደረጉትን ሽሽት ለመግለፅ ተመሳሳይ የሆነ ቃል ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህም ለእስልምና ማዕከላዊ ጉዳይ ሲሆን የእስልምና ቀን መቁጠርያ ጅማሮ ነው፡፡ ለጂሃዳውያን ወደ አፍጋኒስታን ወይንም ወደ ኢራቅ መጓዝ ከነቢዩ እና ከተከታዮቹ ጉዞ ጋር የሚነፃፀር መንፈሳዊ ልምምድ ነው፡፡ የአል ዛርቃዊ ተተኪ እንደሆነ የሚነገርለት አቡ ሐምዛ አል-ሙሐጅርን የመሳሰሉ ጂሃዳውያን ታጣቂዎች "ስደተኛ" የሚል ትርጉም ያለውን "ሙሐጂር" እንደ ቅፅል ስም ይጠቀማሉ፡፡ ሁለተኛው ጠንካራ አፈ ታሪክ ቀለል ያለ ትጥቅ በታጠቁ ጥቂት ወጣቶች ግዛተ መንግሥት ይጠፋል - ይህም እውን የሚሆነው በምትሃታዊ ፅንፍ በመጠቀም ነው የሚል ነው፡፡
>
> *(ቪከን ቸቴርያን፣ "የኢራቅ ትውልድ"፣ ሌሞንድ ዲፕሎማቲኬ፣ የእንግሊዘኛ እትም፣ ህዳር 2008)*

የመሐመድ አስገዳጅ ሂጅራ ምሳሌነት እና በእርሱ ዘመን በሚገኙት ተከታዮቹ ላይ ያደረሰው ምትሃታዊ ተፅዕኖ ዛሬ በአለም ዙርያ እየተሰማ ነው፡፡

> ዛሬ ሙስሊሞች ወደ ምዕራብ እያደረጉ የሚገኙት ስደት የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ ይህ መጽሐፍ ግልፅ

የሆነ ትንቢታዊ ማስጠንቀቅያን ያስቀምጣል፡፡ ስለ ይሁዶ-ወክርስቲያን ባሕል ተጠብቆ መቆየት፣ ስለ ሕግ የበላይነት፣ ስለ እኩልነት፣ ስለ ግለሰቦች መብት እና ስለ ኃይማኖት ነፃነት ግድ የሚላቸው ሁሉ ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

ዶ/ር ፓትሪክ ሱክሄዶ

# መግቢያ

የሸሪኣ ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር እና ሕጋዊ ለማድረግ በብሪትሽ መንግሥት በቅርቡ ይፋ የተደረገው እቅድ ብዙ ሰዎች ይህ ሊሆን እንዴት ይችላል? በማለት እንዲጠይቁ አንቅቷቸዋል፡፡ ከዚህ የፍትህ ሚኒስቴር አፊሴላዊ ትግበራ በፊት የሸሪኣ ፍርድ ቤቶች ለዓመታት በዩናይትድ ኪንግደም ሙስሊም ማሕበረሰቦች መካከል ሲሰሩ መቆየታቸው ሲታወቅ ደግሞ ይህ ጉዳይ ይበልጥ እውን ሆኗል፡፡

ትክክለኛው ጥያቄ የሚከተለው ነው፡ *አናሳ ማሕበረሰብ እንዲህ ዓይነቶቹን ህግጋት እንዴት በተሳካ ሁኔታ ጠንካራ ወደ ሆነ ስርኣት ሊያሰርግ ቻለ?* ለዚህ አማራጭ ሥርኣት ትክክለኛዎቹ ምክንያቶችስ ምንድናቸው? ሰዎች በተለየ የሕግ ማዕቀፍ ስር ለመኖር የሚፈልጉ ከሆነ መጀመርያውኑ ስለምን ወደዚህ ተሰደው ይመጣሉ? በራሳቸው ሃገር ቢኖሩ ለእነርሱ የተሻለ አይደለምን? እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ!

በዩ ኬ እና በሌሎች የአውሮፓ ሃገራት ውስጥ ያለውን የሸሪኣ ፍርድ ቤቶች ጥያቄ ለመረዳት አንድ ሰው ዋና የሆነውን ገፅታውን ተጠግቶ መመልከት ይገባዋል - ይህም አጠቃላይ የሆነውን እስላማዊ የስደት አስተምህሮ ማለት ነው፤ በሙስሊሞች ወደ ምዕራብ ሃገራት እና ባጠቃላይ ወደ ነፃ ሃገራት የሚደረገው ስደት

በእስላማዊ አስተሳሰብ በተቀየሰ ዓላማ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስረ መሰረቶቹም ቁርአን እና ሱና ናቸው፡፡

ሂጅራን ወይንም የስደት አስተምህሮን እና ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች አስተምህሮዎችን ካልተረዳን በስተቀር አጠቃላይ የሆነውን የሙስሊሞች የስደት ጉዳይ መረዳት አዳጋች ነው፡፡ በዚህ ዘመን ባሉት ሙስሊሞች ዕይታ መሰረት ስደት መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ባደረገው ስደት ላይ የተመሰረተ እና ከእርሱም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡

# የመጀመርያው የመሐመድ ስደት

የመሐመድ ሂጅራ ወይንም ከመካ ወደ መዲና ያደረገው ስደት በጣም አስፈላጊው የእስልምና ክስተት ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን እስላማዊው የቀን መቁጠርያ ከዚያ የሚጀምር መሆኑ ለዚህ ማሳያ ነው፡፡ ሂጅራ እስልምናን እንደ ኃይማኖት እና ሙስሊሞችን ደግሞ እንደ ማሕበረሰብ ለውጧቸዋል፤ ይህም ደካማ ሕዝቦች ከመሆን ጠንካራ የፖለቲካ ተቋም ወደመሆን፣ የተበታተኑ የግለሰብ ታማኝ ቡድኖች ከመሆን የተጠናከረ ሰራዊት ወደመሆን፣ አንድነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ እና በመጨረሻም ሃያል ማህበራዊ-ኃይማኖታዊ የፖለቲካ መንግሥት ወደመሆን ለውጧቸዋል፡፡

የሂጅራ (መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረገው ስደት) ጠቃሚ ውጤት የእስልምና እንደ ኃይማኖት ብቻ ሳይሆን እንደ ማህበራዊ-

*ኃይማኖታዊ* እና እንደ *ማህበራዊ-ፖለቲካዊ ሥርኣት* ከመካ ባሻገር *መስፋፋት* ነው፡፡ ለዚህ ነው እስልምናን እንደ ሕይወት *መንገድ* እንዲሁም ትርጉም እንዳለው *ኃይማኖት* እና *ፖለቲካዊ ሥርኣት* ለማስፋፋት እና ከእስላማዊ *ሃገራት* ባሻገር ለማንሰራፋት *ሂጅራ* በጣም አስፈላጊው መንገድ እንደሆነ የሚቆጠረው፡፡

ስለዚህ *ሂጅራ* በእስልምና ነቢይ እንደተቀመጠ ምሳሌ በሁሉም ሙስሊሞች መከተል እና መተግበር ይኖርበታል፡፡

## *የነቢዩ ምሳሌነት*

የመሐመድ ምሳሌነት *ሱና* በመባል የሚታወቅ ሲሆን እንደ *ሸሪኣ* ዋና ምንጭ ከቁርአን ጋር እኩል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ በእርግጥ ያለ *ሱና* እስልምና የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ የሙስሊም ሕይወት ከቁርአን ይልቅ *በሱና* ነው የሚመራው፡፡ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ የእስላማዊው ኃይማኖት አሰራር መሐመድ ያደረገውን፣ የተናገረውን እና ያፀደቀውን በቀጥታ በመከተል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

*ሱና* የአረብኛ ቃል ሲሆን "ማቆም፣ ማስተካከል ወይንም ቅርፅ ማስያዝ" ማለት ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ *ሱነቱ ዐ'ነቢ* ወይንም "የነቢዩ ምሳሌነት" በመባል ይታወቃል፡፡

*ሱና* በግልፅ እና በትክክል የተመሰረተው በመዲና ነበር፡፡ እንጭጭ የነበረው የሙስሊም ማሕበረሰብ *ኣል ሙሐጂሩን* ማለትም

"ስደተኞች" በመባል የሚታወቁ የአረብ ጎሳዎች እና *አውስ* እና *ኻዝራጅ* ወይንም *አል-አንሳር* (ድል አድራጊ የስደተኞች ጠባቂዎች) በመባል የሚታወቁ የመዲና ጎሳዎች እና የሌሎችም ቅይጥ ነበር፡፡

እያንዳንዱ ጎሳ ከሌላው የተለየ የየራሱ እድሜ ጠገብ ትውፊት ስለነበረው እስልምናን እንደ ኃይማኖት እና መሐመድን እንደ ነቢያቸው የተቀበሉ ቢሆንም ከመሐመድ ሂጅራ ጥቂት ጊዜ በኋላ ግጭት መፈጠሩ አልቀረም፡፡ መሐመድ ትልቅ የሆነ ቀውስ ሊፈጥር የሚችለውን ነገር ወዲያውኑ ደረሰበት፡፡ ስለዚህም ሁሉንም ጎሳዎች የአባቶቻቸውን ልማዶች እና ከእስልምና በፊት የነበረውን ልማዶቻቸውን በሙሉ በመተው የአዲሱን እስላማዊ ማሕበረሰብ መንፈስ እንዲቀበሉ ጠየቃቸው፡፡[1] በዚህም መሰረት ሁሉም ሙስሊሞች በሁሉም መንገድ እና ጠባይ የእርሱን "ምሳሌነት" እንዲከተሉ የጠየቃቸው ሲሆን ይህም ደግሞ ለመሐመድ በተለያዩ መንገዶች በተገለጠለት በቁርአን ውስጥ ረዘም ባሉ ተከታታይ ጥቅሶች ተረጋግጧል፡ ከነዚህ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን እነሆ፡

> ሱራ 68፡4 "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡" (ይህም በሌላ አነጋገር ታማኝ የሆኑቱ ለሕይወታቸው እንደ ምሳሌ እንዲቀበሉት የተሰጠ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው፡፡)

---

[1] ለዚህ ጉዳይ ድጋፍ ለመስጠጥ መሐመድ ከእስልምና በፊት የነበሩት ልማዶች ሁሉ "ያለማወቅ ዘመን" ልማዶች እንደሆኑ አወጀ፡፡ ይህም በአረብኛ *አሰር አል ጃህሊያ* በመባል ይታወቃል፡፡

> ሱራ 53፡2-5 “ነቢያችሁ (ሙሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም፡፡ ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡ እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ ኀይሎቹ ብርቱው (መልአክ) አስተማረው፡፡ የዕውቀት ባለቤት የኾነው (አስተማረው፤ በተፈጥሮ ቅርጹ ኾኖ በአየር ላይ) ተደላደለም፡፡”

እንግዲህ እነዚህ መሐመድን ስለመከተል የሚናገሩት ጥቅሶች ሙሉ በሙሉ በቀጥታ ይወሰዳሉ፣ ማለትም መሐመድ ሙስሊሞች እርሱ የተናገረውን እና ግብሩን በሙሉ እንዲከተሉ ይጠብቅባቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም አስተጣጠብ፣ የጢም አስተዳደግ ወይንም ደግሞ የመፀዳጃ ቤት አገባብን የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮችን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው የመሐመድን ይሁንታ ያገኘ የሆነ ነገር ቢፈፅም የሱና አካል ተደርጎም ይወሰዳል፡፡

በእርግጥ ፍላጎታቸው መጪው ዓለም ብቻ እንደሆነ የሚናገሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ ለዚህም ምላሽ ሱራ 33፡21 ላይ በተጻፈው መሰረት የግድ መሐመድን መከተል እንዳለባቸው እና የእርሱን ምሳሌነት በመከተል እርሱ ያደርግ የነበራቸውን ነገሮች እንዲያደርጉ አላህ ይነግራቸዋል፡፡

> “ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ፡፡”

አዲስ ከሰለሙት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ መሐመድን በጥብቅ ለመከተል የሚያቅማሙና ፍላጎታቸው አላህን ብቻ መከተል እንደሆነ ይናገሩ ነበር፡፡ ስለዚህ መሐመድ ሱራ 4፡80 ላይ የሚገኘውን እንደተቀበለ ተናገረ፡

“መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡”

በሱራ 48፡10 ላይ እንደተጻፈው ከእርሱ ጋር ቃልኪዳን የተጋቡ ሰዎች ለአላህ ቃልኪዳን የገቡ ሰዎች እንደሆኑ እስከመናገርም ደርሷል፡

> “እነዚያ ቃል ኪዳን የሚጋቡህ ቃል ኪዳን የሚጋቡት አላህን ብቻ ነው፡፡ የአላህ እጅ (ኀይሉ) ከእጆቻቸው በላይ ነው፡፡ ያፈረሰም ሰው የሚያፈርሰው በነፍሱ ላይ ብቻ ነው፡፡ በእርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላም ሰው ታላቅ ምንዳን በእርግጥ ይሰጠዋል፡፡”

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሚገኙት መገለጦች ውስጥ አላህ እና መሐመድ በእኩል ስልጣን ፍርድን በመፍረድ አንድ ላይ ተቆራኝተዋል፡

> ሱራ 33፡36 “አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡”

በተጨማሪም፡

> ሱራ 9፡29 “ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው፡፡”

ዝም ብሎ በአላህ ማመን ብቻ በቂ አይደለም፡፡ እውነተኛ አማኝ ለመሆን አንድ ሰው በመሐመድ እና በእርሱ መደምደሚያነት አጥብቆ የሚያምን መሆን አለበት፡፡ ይህም ደግሞ የተገለጠ የቁርአን ክፍል ለመሆን ችሏል፡

> ሱራ 24፡62 “ምእመናን ማለት እነዚያ በአላህና በመልክተኛው ያመኑት፤ ከእርሱ ጋር በሚሰበሰብ ጉዳይ ላይ በኾኑ ጊዜ እስከሚያስፈቅዱ ድረስ የማይኼዱት ብቻ ናቸው፡፡”

> ሱራ 49፡15 “(እውነተኛዎቹ) ምእምናን እነዚያ በአላህና በመልእከተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶ ቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው፡፡”

በማስከተል ደግሞ የሁሉም ነገሮች ባለቤቶች አላህ እና መልእከተኛው መሐመድ እንደሆኑ ለዚህም ምክንያቱ ሁሉም ነገር የአላህ እና የመልእከተኛው ስለሆኑ እንደሆነ ተገለጠ፡

> ሱራ 8፡1 “ከጦር ዘረፋ ገንዘቦች ይጠይቁሃል፡፡ «የዘረፋ ገንዘቦች የአላህና የመልክተኛው ናቸው፡፡» ስለዚህ አላህን ፍሩ፡፡ በመካከላችሁ ያለችውንም ኹኔታ አሳምሩ፡፡ አማኞችም እንደኾናችሁ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ በላቸው፡፡”

ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ አላህ ሁሉንም ስልጣን ለመሐመድ ሊሰጠው ሆነ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም በሱራ 59፡7 መሰረት መሐመድ ትክክል መስሎ የታየውን መፍቀድ እና መከልከል፣ መስጠት እና መንሳት ይችላል፡፡

> “አላህ ከከተሞቹ ሰዎች (ሀብት) በመልክተኛው ላይ የመለሰው (ሀብት) ከእናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይኾን፡፡ ለአላህና ለመልክተኛው፣ ለዝምድና ባለቤትም፣ አባት ለሌላቸው ልጆችም፣ ለድኾችም፣ ለመንገደኛም (የሚሰሰጥ) ነው፡፡ መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት፡፡ ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡”

በሌላ አባባል የመሐመድ ስልጣን ከቁርአን ጽሑፍ የላቀ ነው ማለት ነው፡፡ መሐመድን ማስቀየም ከክህደት እኩል እንደሆነ እና የእርሱ መብት እና ድንጋጌም ከአላህ ጋር እኩል እንደሆነ ለሙስሊሞች ተነግሯቸዋል፡፡

ከዚህም በላይ የመሐመድ ስልጣን በምድራዊ ነገሮች ብቻ የተገደበ ሳይሆን ወደ መጪውም ዓለም የሚሻገር ነው፡

> ሱራ 4፡59 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፡፡ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡”

> ሱራ 3፡132 “ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ፡፡”

እስኪ ከሚቀጥለው ጥቅስ ጋር አነፃፅሩ፡

> ሱራ 24፡56 “ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ፡፡ ምጽዋትንም ስጡ፡፡ መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡ ለእናንተ ሊታዘንላችሁ ይከጀላልና፡፡”

ሁሉም እስላማዊ ልምምዶች ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ *ከሱና* የተገኙ ሲሆኑ አንዳቸውም በቁርአን ውስጥ ተመዝግበው አናገኝም፡፡ ለምሳሌ ያህል *አዛን* በመባል የሚታወቀው የፀሎት ጥሪ *ከሱና* የተገኘ ነው፣ ስንት ጊዜ እንደሚደረግ የሚናገረው የፀሎት ዝርዝር እና እንዴት እንደሚፀለይ እንዲሁም የትጥበት አፈፃፀም ዝርዝር ሁኔታ ወዘተ. የመጡት *ከሱና* ነው፡፡

*ሐጅ* ወይንም መንፈሳዊ ጉዞ እና ዝርዝር ሁኔታዎቹ፣ የአለባበስ *ሥርኣት*፣ የሙስሊም ኮፍያ፣ ሌሎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ተመንዝረው የወጡት *ከሱና* ነው፡፡ ስለዚህ

መሐመድ በእስልምና ውስጥ ያለው ሥልጣን ፍፁም ነው፡፡ እርሱ የሁሉም ነገር ማዕከል ስለሆነ ሙስሊሞች በሁሉም የህይወት ገፅታዎቻቸው እርሱን ሊከተሉት፣ እርሱን ሊመስሉት እና እርሱ የሆነውን ሁሉ ይሆኑ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአንድ ሙስሊም ሱና የአላህ የራሱ ቃል ነው፡፡

በዚህ መሰረት እንግዲህ የእርሱ የሂጅራ ወይንም የስደት ምሳሌነት ለእስልምና መጠናከር እና መስፋፋት በሙስሊሞች ላይ የተጣለ ግዴታ ነው ማለት ነው፡፡ ኢብን ተይሚያ[2] እንዲህ ብሎ በተናገረ ጊዜ ሁሉንም ነገር በጥሩ ሁኔታ ቋጭቶታል፡፡ የአላህ መብት እና የመልእክተኛው መብት ለዘለዓለም አንድ ላይ ተቆራኝተዋል፣ ምክንያቱም የአላህ እና የመልእክተኛው ድንጋጌ አንድ ናቸውና፣

[2] በኢብን ተይሚያ የተጻፈው ዋናው አረብኛ የሚከተለው ነው፡ يـف هباتــك : 41- 40 مراصـلا لولســـملاو بلـــع متـاش لوســـرلا ص : لوقـــي نبـــا ةيميـــت ةدحاو ؛ نمف بـذآ لوســـرلا دقـف بـذآ الله ، : " قـح الله قحـو هلوسـر نـــامزاتم نييـــــو مهــبر اا ةطسـاوب لوســـرلا ، يـل نـا ةهج ةمرح الله بلاعــت هلوسـرو ةهج مهنـم قـــيرط هـريغ او نمو هعاطأ دقـف عاطأ الله؛ نـا ةمأا ا نولصــــي ام مهنيـــب هنـــــايبو، اف زوجي نـا قـــرفي نيـــب الله هلوسـرو يـف ءيـش نـم هذه س دحأ روماا ببــــس هاوس، دقـو هماقأ الله مـاقم هســـفن يـف هرمأ هيهنـو هرابخـاو
ኢብን ተይሚያ "አሰሪም ወል መስሉል ዐላ ሸቲም አረሱል" በሚለው መጽሐፉ ገፅ 40-41 ላይ እንዲህ ይላል፡ "የአላህ መብቶች እና የመልእክተኛው መብቶች እኩል ናቸው፡፡ አለህን ለመታዘዝ የምንዞርበት አቅጣጫ እና መሐመድን ለመታዘዝ የምንዞርበት አቅጣጫ አንድ ነው፡፡ መልእክተኛውን የሚሳደብ ሰው አላህን ይሳደባል፣ መልእክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ደግሞ አላህን ታዞታል፣ ምክንያቱም የእስላማዊ ኡማ አባላት በመልእክተኛው በኩል ካልሆ በስተቀር ከፈጣሪያቸው ጋር ምንም ግንኙነት አይኖራቸውምና፡፡ በመልእክተኛው በኩል ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ አላህ የመቅረቢያ መንገድ የለውም፡፡ አላህም (መሐመድን) በሁሉም ረገድ ለማዘዝ፣ ለመከልከልም ሆነ ለማብራራት በራሱ ምትክ አስቀምጦታል፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ ጉዳዮች በማናቸውም በአላህ እና በመልእክተኛው መካከል ልዩነትን ማድረግ የተፈቀደ አይደለም፡"

ሊነጣጠሉም አይችሉም፣ ነቢዩን የሚያስቀይም ሰው አላህን ያስቀይማል፤ ነቢዩን የታዘዘ ሰው አላህን ታዞታል፡፡ ይህ ሑማ በመልእክተኛው በኩል ካልሆነ በስተቀር ከአባላቱ መካከል አንዱም እንኳ ከጌታው ጋር ግንኙነት የለውም፣ ሌላ ምንም መንገድ የለም፣ ያለ እርሱ ዓላማ ቢሶች ናቸው፤ **ምክንያቱም አላህ መሐመድን በራሱ ምትክ አስቀምጦታልና፣** ማዘዝ፣ መከልከል፣ መግለጥ እና መሰወር ይችል ዘንድ፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ጉዳዮች ዙርያ አላህንና መልእክተኛውን ነጣጥሎ ማየት አይቻልም፡፡

# የእስላማዊ ስደት ዓይነቶች

ሰዎች በአካባቢያቸውም ሆነ ከሃገር ወደ ሃገር የሚሰደዱባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ቦታ በአንድ ዓይነት እስላማዊ ስደት ላይ ብቻ እናተኩራለን፡ ለእስልምና እድገት በመግለጫ የተቀመጠውን ማለት ነው፡፡ እስላማዊ ስደት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ወይንም ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ የሚደረግ ውስጣዊ ስደት ሊሆን ይችላል፡፡ እስላማዊ መሪዎች የተወሰነን ሙስሊም ማሕበረሰብ ለመደገፍ አስፈላጊ እንደሆነ ከገለፁ ከአንድ ዩኒቨርሲቲ ወደ ሌላ የሚደረግም ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ቦታ አንድ ጊዜ በቁጥጥር ስር ከሆነ በኋላ እየተስፋፉ የሚገኘውን የሙስሊም ማሕበረሰብ ለማጠናከር እና የእስልምናን አርማ ከፍ አድርጎ ለማንሳት ፍቃደኛ የሆኑ ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄዱ ይጠየቃሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ስደት በሙስሊሞች ሁሉ ላይ፣

በተለይም ደግሞ አቅሙ ባላቸው ሰዎች ላይ በሕግ ተደነገገ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እስላማዊ በሆነ አባባል ስንናገር ስደት ከሃገር ወደ ሃገር በመሰደድ ብቻ የተገደበ አይደለም ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት በአንድ የቢሮ ህንፃ ውስጥ እንኳ ሊደረግ ይችላል፡፡

መሐመድ ወደ መዲና መሰደዱ መካ ከነበረበት ጊዜ ይልቅ ነፃነትን በማጎናፀፍ የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥሮለታል፡፡ በመካ እርሱና ተከታዮቹ ክትትል ይደረግባቸው ነበር ነገር ግን በመዲና ያሻውን ማድረግ ይችል ዘንድ ነፃነትን አግኝቷል፡፡ በጠላቶቹ ላይም ጥቃትን ለመፈፀም ራሱን እና ተከታዮቹን ማዘጋጀት፣ ማንቀሳቀስ እና ማደራጀት ይችል ዘንድ በመዲና በሚገኘው መስጊድ ውስጥ የራሱን ማዕከላት አቋቁሞ ነበር፡፡ ይህ ወደ እርሷ በመሰደድ ነዋሪዎቿን አስገዝቶ መኖርያው ባደረጋት በመዲና ውስጥም ሆነ ቀደም ሲል ተሰዶ በመውጣት ኋላ ላይ ግን ባሸነፉት በመካም ውስጥ ተመሳሳይ ነበር፡፡ ስለዚህ ስደት የሚታየው አስተናጋጅ የሆነውን ማሕበረሰብ ክፍት ወይንም እስላማዊ ካልሆነ ማሕበረሰብ ወደ እስላማዊ ማሕበረሰብ ወይንም ደግሞ ቢያንስ እስልምና የበላይ ወደሆነበት ማሕበረሰብ ለመለወጥ የሽግግር ጊዜ ተደርጎ ነው፡፡ ከዚህ አዲስ ከተገኘ የበላይነት ልክ መሐመድ እንዳደረገው የመጡባትንም ሃገር እንኳ ተፅዕኖ ሊያሳድሩባት ይችላሉ፡፡

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የትንሳኤው ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ የመንግሥቱን የምስራች እንዲያውጁ ለደቀ መዛሙርቱ ታላቁን ተልዕኮ እንደሰጠ ሁሉ መሐመድም አንድ ተመሳሳይ የሆነ ነገር አድርጓል፡፡ ቁርአን ሱራ 3፡83 ላይ የሚከተለውን ይናገራል፡

> “በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ፤ በውድም በግድም ለርሱ የታዘዙ ወደርሱም የሚመለሱ ሲኾኑ (ከሓዲዎች) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን?”

በእስልምና ለአላህ የሚሆነው መገዛት ልክ ጥቅሱ እንደሚናገረው በውድም ሆነ በግድ ያሉትን አማራጮች ሁሉ በመጠቀም እውን ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህንን ግብ እና የማሳኪያ መንገዶቹን በልቡ ውስጥ በመያዝ የእስልምና ነቢይ የሆነው መሐመድ እንዲህ በማለት ተናገረ፡

**“አላህ ያዘዘኝን አምስት ትዕዛዞች እሰጣችኋለሁ፡ እንድትሰባሰቡ፣ እንድታደምጡ፣ እንድትታዘዙ፣ እንድትሰደዱ እና ለአላህ ብላችሁ ጂሃድን እንድታውጁ፡፡”[3]**


ስለዚህ ሂጅራ ወይንም ስደት በብዙ ምክንያቶች በሙስሊሞች ሁሉ ላይ የተደነገገ ነው፤ በጣም አስፈላጊው ግን ስደት በሌላ ሃገር ውስጥም ሆነ እንደ አጠቃላይ ማሕበረሰብ ለእስልምናና

[3] ሐዲስ ቁጥር 2863 ኪታብ አል አምሣሌል በትርሚዚ የተዘገበ፣ እንዲሁም በኢማም አህመድ ኢብን ሀንበል እንደ ሐዲስ ቁጥር 17344 የተዘገበ፡፡

ለሙስሊሞች ድልን ለማምጣት ጂሃድን የማወጅ ዝግጅት መሆኑ ነው፡፡

በስዕል 1 ላይ እንደሚታየው አምስቱ የእስልምና አዕማዶች አማኞች የአላህን ጉዳይ በጂሃድ ወደ ፊት እንዲያራምዱ የማነሳሳት እና የማበረታታት ዓላማ አላቸው፡፡ ጂሃዱ የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል፡፡ ግልፅ የሆነ ጦርነት ወይንም ደግሞ የረቀቀ ስልት የሚከተል ሊሆን ይችላል ነገር ግን አሁን እያየነው ያለነው የስደት ጂሃድን ሲሆን እንዴት ከግብ እንደሚደርስ ለማወቅ የተመሰረተበትን እስላማዊ አስተምህሮ እናብራራለን፡፡

መሰባሰብ፣ ማድመጥ፣ መታዘዝ፣ መሰደድ እና ስለ አላህ ጂሃድን ማወጅ የሚሉት አምስቱም መመሪያዎች በሙሰሊም ሊቃውንት በመብራራት ወደ ስልታዊ አስተምህሮዎች ተለውጠዋል፡፡




*ስዕል 1፡ የጂሃድ አስተምህሮ የሁለቱ የማይነጣጠሉ የእስልምና ይዘቶች መሰረት ነው፡ እነኚህም ኃይማኖት እና መንግሥት ናቸው። አምስቱ አዕማዶች (1) ሸሃዳ (ስለ አላህ እና መሐመድ መመስከር)፣ (2) ሰላት (ፀሎት)፣ (3) ሳውም (ፆም)፣ (4) ዘካት (ኃይማኖታዊ ግብር)፣ እና (5) ሐጅ (ወደ መካ ጉዞ)። አምስቱ ኃላፊነቶች፡ (1) መሰብሰብ፣ (2) መስማት (3) መታዘዝ፣ (4) መሰደድ (5) ጂሃድን ማወጅ ናቸው። ልብ በሉ እንደ ሌሎች የእስልምና ሕግጋት ምንጮች ጂሃድ ሁሉንም የሚያቅፍ*

*ስለሆነ በዚህ ስዕል እንደ መሰረት ተቀምጧል፡፡ በእስልምና "መገዛት" የባርያ እና የጌታ መገዛት መሆኑንም ልብ በሉ፡፡*

1. **መሰባሰብ፡** *(ተጀምህ)* ጀመዐ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ሥረወ ቃሉ መስጊድ ከሚለው ጋር አንድ ነው፡፡ ትርጉሙም መሰባሰብ፣ ጉባኤ ማድረግ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሙስሊሙን ማሕበረሰብ መቀላቀል ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው የዚያ አካል ለመሆን በአላህ እና በመልእክተኛው ማመን ይጠበቅበታል - ይህም ማለት "ለሰው ሁሉ እንደተላከ የመጨረሻ ነቢይ" በመሐመድ ማመን ማለት ነው፡፡ በሚቀጥለው ጥቅስ ውስጥ "እነዚያ ያመኑት" የሚለው እርሱን ተከትለው ለተዘረዘሩት ነገሮች እንደ መነሻ ነጥብ ወይንም እንደ አያያዥ ሆኖ መቀመጡን ልብ በሉ፡፡

> ሱራ 2፡218 "እነዚያ ያመኑትና እነዚያም (ከአገራቸው) የተሰደዱት በአላህም መንገድ ላይ የተጋደሉት እነዚያ የአላህን እዝነት ይከጅላሉ፡፡ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡"

> ሱራ 8፡72 እነዚያ ያመኑና የተሰደዱ፡፡ በአላህም መንገድ ላይ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የታገሉ፡፡ እነዚያም (ስደተኞቹን) ያስጠጉና የረዱ፡፡ እነዚያ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ እነዚያም

ያመኑና ያልተሰደዱ እስከሚሰደዱ ድረስ ከነሱ ምንም ዝምድና የላችሁም፡፡ በሃይማኖትም እርዳታን ቢፈልጉባችሁ በእናንተና በነሱ መካከል ቃል ኪዳን ባላችሁ ሕዝቦች ላይ ካልኾነ በስተቀር በናንተ ላይ መርዳት አለባችሁ፡፡ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡

ሱራ 8፡74-75 እነዚያም ያመኑና የተሰደዱ በአላህም መንገድ ላይ የታገሉ፣ እነዚያም ያስጠጉና የረዱ እነዚያ እነሱ በእውነት አማኞች ናቸው፡፡ ለእነሱም ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አላቸው፡፡ እነዚያም በኋላ ያመኑና የተሰደዱ፣ ከእናንተም ጋር ኾነው የታገሉ እነዚያ ከናንተው ናቸው፡፡ የዝምድናዎች ባለቤቶችም በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው በከፊሉ (መውረስ) የተገቡ ናቸው፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡

ሱራ 9፡20 እነዚያ ያመኑት፣ ከአገራቸውም የተሰደዱት፣ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡

ለመሰብሰብ መስጊድ እንደሚያስፈልግ ግልፅ ነው ወይንም ደግሞ በእስልምና *ሐውዛዎች፣ ሙሰሊያዎች፣ ዘውያዎች* ወዘተ. በመባል የሚታወቁ አነስተኛ ክፍሎች ያስፈልጋሉ፡፡

የመስጊድን ቦታ እና አስፈላጊነት ለመረዳት በእነዚህ ደራሲያን የተፃፈውን፡ *መስጊድ እና በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ሚና* የሚለውን መጽሐፍ ተመልከቱ፡፡

2. **መስማት፡** መስማት ለቁርአን እና ለሱና (ለመሐመድ ምሳሌነት) ስልጣን ራስን መስጠት ነው፡፡[4]
3. **መታዘዝ፡** በማሕበረሰቡ ውስጥ በስልጣን ላይ ባሉት በኩል ለአላህ መታዘዝ ቁርአን የደነገገው ነገር ነው፡፡[5] ሱራ 4፡59 እንዲህ ይላል፡

> “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፡፡ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡”

የስልጣን ባለቤቶች ማለት ኢማሞች እና እስላማዊ ሊቃውንት ማለትም *ኡላማ* በመባል የሚጠሩት ማለት ነው፡፡

[4] ገፅ 20 ላይ “የነቢዩ ምሳሌ” የሚለውን ክፍል ተመልከቱ፡፡
[5] ዝኒ ከማሁ

4. ***መሰደድ፡*** ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች 2፡218፣ 8፡72፣74፣75፣ 9፡30፣ 16፡41፣ 16፡110 እምነትን ከስደት ጋር ያቆራኛሉ፡፡

5. ***ጂሃድን ማወጅ፡*** *ጂሃድ* በዚህ ቦታ አቅሙ ባላቸው ሙስሊሞች ሁሉ ላይ የተጣለ ትዕዛዝ እና ግዴታ ነው፡፡ ይህ ግዴታ ሙስሊም ባልሆኑት ዘንድ ብዙ ጊዜ የአጥፍቶ መጥፋት ተልዕኮን የመሰለ መስዋዕትነት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ከቁርአን አኳያ የራስን ምቾት በመሰዋት ከመሰደድ ጀምሮ *በጂሃድ* ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች በገንዘብም ሆነ በሌላ በማንኛውም መንገድ ድጋፍ በማድረግ ሁኔታዎችን እስከ ማመቻቸት የሚደርስ ሊሆን ይችላል፡፡ *ፆም* እና *ፀሎት* ግዴታዎች እንደሆኑ ሁሉ *ጂሃድም* ግዴታ ነው፡፡ እስኪ እዚህ ጋር አንድ ጥቅስ ብቻ እንጥቀስ፤ ሱራ 2፡216

> "መጋደል እርሱ ለእናንተ የተጠላ ሲሆን በእናንተ ላይ ተጻፈ፡፡ አንዳች ነገርን እርሱ ለናንተ የበለጠ ሲሆን የምትጠሉት መኾናችሁ ተረጋገጠ፡፡ አንዳችንም ነገር እርሱ ለናንተ መጥፎ ሲሆን የምትወዱት መሆናችሁ ተረጋገጠ፡፡ አላህም (የሚሻላችሁን) ያውቃል ግን እናንተ አታውቁም፡፡"

ጂሃድን ከስደት ጋር በማስተካከል ስደትን ለላቁ ግቦች በተለይም አንድን ማሕበረሰብ እስላማዊ ወደ መሆን

ለመለወጥ ግብ እንደ መረማመጃ ድንጋይ ያቀርባል፡፡ አሁን ያለውን ማሕበረሰብ መለወጥ ማለት ማስለም ማለት ነው፡፡ ይህ ቀስ በቀስ እንደ ጠብታ ቋሚ የሆኑ ጥያቄዎችን በማቅረብ ወይንም ደግሞ አሉታዊ አስተያየቶችን በመስጠት፤ ለሙስሊም ማሕበረሰቦች ጥንካሬ እና መብቶች ድምፅ በመሆን ጥያቄዎችን በማቅረብ፤ አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ለእስልምና የበላይነት በማመቻቸት፤ በጋብቻ (ሙስሊም ወንዶች የአስተናጋጁን ማሕበረሰብ ሴቶች እንዲያገቡ የሚደረግ ሲሆን ነገር ግን ሙስሊም ሴቶች ሙስሊም ያልሆኑ ወንዶችን ማግባት የሚችሉት ከሰለሙ ብቻ ነው፡፡) በእነዚህ መመሪያዎች እና ተግባራት እስልምናን ላዕላይ በማድረግ እና በተለይም ደግሞ በማሕበራዊ-ፖለቲካ ምህዳር ስርኣቶች ላይ የበላይ በማድረግ ማሕበረሰቡ በመጨረሻ እንዲቀየር ይደረጋል፡፡

መሐመድ እንዲህ ማለቱ ይነገራል *"ኩፍር (አለማመን) እስካለ ድረስ ወይንም ደግሞ ጠላት እስካለ ድረስ ስደት መቆሚያ የለውም"*[6] (*ኬንዝ አል ኡመል* 46274)፡፡ በሌላ አባባል እስልምና ላዕላይ ስርኣት እንደሆነ

[6] http://www.al-eman.com/Islamlib/viewchp.asp?BID=137&CID=647&SW=46274#SR1

የማይታሰብባቸው ሙስሊም ያልሆኑ ማሕበረሰቦች እስካሉ ድረስ ጂሃድ መቀጠል አለበት፡፡ ጂሃድ በተለያዩ መንገዶች ሊገለፅ ይችላል ነገር ግን ሁሉም አንድ ዓላማ ነው ያላቸው እርሱም የእስልምናን የበላይነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ምድር ለእስልምና አገዛዝ እስክትንበረከክ ድረስ ስደት የማይቀር ግዴታ መሆኑን መሐመድ ግልፅ አድርጓል፡፡

> "ሰዎች ሆይ እስልምናን አጥብቃችሁ በመያዝ ተሰደዱ ጂሃድ እስከቀጠለ ድረስ ሂጅራ ወይንም ስደት ይቀጥላልና" (*ኬንዝ አል ኡመል* 46260)፡፡[7]

እንዲህ ዓይነቶቹ ፖለቲካዊ አስተምህሮዎች በኃይማኖታዊ መነሳሳት እና ቅንዓት ሰዎች እንዲከተሏቸው እና እንዲማሯቸው መደረጉ ከግምት ውስጥ ሲገባ በተለይም በምዕራባውያን ሃገራት እና በሌሎች ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የሙስሊሞች ስደት እና በመዋለድ መብዛት በአንክሮ መመልከት ያሻል፡፡ ከላይ በተባለው መሰረት አንድ ሰው የተወሰኑ አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ ያስፈልገዋል፡

[7] http://www.al-eman.com/Islamlib/viewchp.asp?BID=137&CID=647&SW=46274#SR1

1. በህዝብ ብዛት ቆጠራ ጥናቶች እንደተተነበየው በምዕራቡ ዓለም የሚኖረው ሕዝብ አብላጫው ሙስሊም የሚሆንበት ጊዜ ይመጣ ይሆን? ይህ የሚሆን ከሆነ ደግሞ፡
2. የምዕራቡ ዓለም ወደ *ደር አል ኢስላም* (የኢስላም ቀጠና) ይቀየር ይሆን?
3. የምዕራቡ ዓለም (የሰለመው አውሮፓ እና ዩ ኤስ ኤ) የአላህን ቃል የበላይ በማድረግ አርማውን ከፍ አድርጎ በማንሳት ዜጎቹ ደግሞ በፅናት ሲታገሉት የኖሩትን *ጂሃድን* ለአላህ ሲሉ ይተገብሩ ይሆኑን?

## *የሙስሊሞች ስደት ወይንስ እስላማዊ ወረራ?*

ቀደም ሲል እንደተባለው በየእለቱ ለሚደረገው ስደት የተለያዩ ምክንያቶች እና መንስኤዎች አሉ፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ጦርነቶች፣ ወዘተ. ነገር ግን እየተመለከትን ያለነው ከውጪ ሲታይ ምንም ያህል ቅንነትን የተሞላ እና ያልተገናኘ ቢመስልም ነገር ግን ከኃይማታዊ ድንጋጌ የመነጨውን በሙስሊሞች ሙስሊም ወዳልሆኑ ሃገራት የሚደረገውን ስደት ነው፡፡

ሙስሊም ወዳልሆኑ ሃገራት የሚደረጉ ሁሉም የሙስሊም ስደቶች በኃይማኖታዊ ጥላ ስር የማይደረጉ መሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል - ማለትም በኃይማኖታዊ አስተምህሮ የተደነገገ እና ፖለቲካዊ

ቢሆንም ነገር ግን እንደርሱ ያልሆኑ አሉ፡፡ ወደፊት እንደሚብራራው የስደተኞቹ የመጀመርያው ዓላማ ከአስተናጋጁ ሕብረተሰብ ጋር በመቀላቀል መኖርን ጨምሮ ሌሎች ግቦችን በመፈለግ ላይ የተመሰረተ ቢሆን እንኳ የመሐመድ ሱና ስደተኛ የሙስሊም ማሕበረሰብን አቅም ያለው እና ተራማጅ ማሕበራዊ-ፖለቲካዊ ኃይል እንዲሆን ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሁሉ በውስጡ ሰንዟል፡፡

እስላማዊውን ማሕበረሰብ የተደላደለ እንዲሆን የማድረግ ክንውን በፍቃደኞች እና የሕብረተሰብ ወይንም የመስጊድ አገልጋዮች በሆኑ ቅጥረኛ ግለሰቦች መረብ የሚከወን ነው፡፡ እነዚህም ሰዎች የአዲሶቹን ስደተኞች አሰፋፈር በመምራት ማሕበረሰቡን በቅርብ ርቀት የሚከታተሉ ናቸው፡፡ አዲሶቹ ስደተኞች የሃገር ቤት ምግቦች ወደሚሸጡባቸው ቦታዎች ስለሚሳቡ ወይንም ደግሞ በካፌዎች፣ በሬስቶራንቶች እና በሌሎች የመገናኛ ቦታዎች የማዘውተር ሁኔታ ስለሚኖራቸው የሕብረተሰብ/መስጊድ ሰራተኞች እነዚህን ቦታዎች በማዘውተር ለአዲሶቹ ስደተኞች ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ፡፡ እነዚህ ፍቃደኛ ግለሰቦች በጣም የተለሳለሱ እና ክህሎት ያላቸው አሻሻጮች በመሆናቸው ለአዲሶቹ ስደተኞች ሀዘኔታ እና አሳቢነታቸውን ማሳየት ይችሉበታል፡፡ እርዳታን ይሰጧቸዋል እንዲሁም የአስተናጋጇን ሃገር ጓዳ ጎድጓዳ ስለሚያውቁ ለአዲሶቹ ስደተኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ያመቻቹላቸዋል፡፡

ስደተኞቹ ለመደላደል የሚያስፈልጓቸው ከጊዜያዊ ማረፍያ ጀምሮ የብድር ገንዘብ እና የነፃ ምግብ አቅርቦትን የመሳሰሉ መሰረታዊ ነገሮች መረብ ውስጥ አሉበት፡፡ ከዚህ በመጀመር ስደተኞቹ ሳያውቁት ቀስ በቀስ ነገር ግን በተቀናጀ መርሐ ግብር በትምህርቶቻቸው በማጥመቅ ወደ እነርሱ ተዋረድ ያስገቧቸዋል፡፡ የመስጊድ/ማሕበረሰብ ሰራተኞች መረቦቻቸውን አስፍተው ነው የሚጥሉት፣ ማለትም ሁልጊዜ አዲስ መጪዎችን የሚያፈላልጉ ቢሆንም እንቅስቃሴያቸውን በእነርሱ ዙርያ ብቻ አይገድቡም፡፡ ከአስተናጋጁ ሕብረተሰብ ወደ እስልምና የሚገቡ አዳዲስ ሰዎችን ለማግኘት በትጋት ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም የስደተኞች ሁለተኛ ወይንም ሦስተኛ ትውልዶች በሆኑ ልጆች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱም እንኳ ቅሬታ ባደረባቸው ሰዎች ላይ ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ እና ወደ ሌሎቹም የሚዘልቅ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ቀዳሚው እና ዋናው ዓላማ አሁን ያለውን የሙስሊም ማሕበረሰብ ማደላደል ሲሆን ያንን በተሳካ ሁኔታ በመፈፀም ብቻ ነው ሸሪኣን ማወጅ እና ስለ እርሱም መጋደል እንዲሁም ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ ልዩ የሆነ ስፍራን ማስገኘት የሚቻለው፡፡

የተሳካለት እና የሚታይ እስላማዊ ህብረተሰብ ለመፍጠር ቀዳሚው መሰረታዊ መርህ **ራስን መነጠል** እና **ራስን መለየት** የሚል ነው፡፡ ስኬቱም ሌሎች የማይገቡበትን የተከለከለ ልዩ ክልል በመፍጠር

ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ይህም ሊመጣ የሚችለው በእስልምና አስተምህሮ በተደነገጉ የተለያዩ እርምጃዎች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህን እስላማዊ ሙዳየ ቃላት እንዲሁም ብዙዎቹ ሕጋዊ ፍቃድ ያገኙበትን እስላማዊ አስተምህሮች፣ መመርያዎች እና ደንቦች ማወቅ እና ምን እንደሚያመለክቱም ደግሞ ከእስላማዊ የሕግ አካሄድ አኳያ መረዳት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## *ግላዊ ስደትን ወይንም ደግሞ መቀላቀልን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ መሰደድን የሚከለክሉ መመሪያዎች*

ሐዲስ ቁጥር 2645 በአቡ ዳውድ[8] እንደተዘገበው እንዲሁም *አ-ጃሚኤህ* በሚለው ማስተማርያው እንደ ሐዲስ ቁጥር 1640 በቲርሚዚ[9] የተዘገበው ተመሳሳይ ሐዲስ መሐመድ እንዲህ ማለቱን ይጠቅሳሉ፡

> እኔ በአረማውያን/ ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች መካከል ከሚኖር ከእያንዳንዱ ሙስሊም ነፃ ነኝ፡፡

ይህ ማለት መሐመድ ምላሽ አይሰጣቸውም፣ ስለ እነርሱ ጣልቃ አይገባም፣ አላህ ይቅር እንዲላቸውም አይለምንም ማለት ነው፡፡ እንዲሁም አስተናጋጅ ማሕበረሰቦች ቢሆኑም እንኳ ሙስሊም

8 http://www.qarn15.net/f/f1/f1f5/f1f5f18.htm
9 http://www.qarn15.net/f/f1/f1f5/f1f5f19.htm

ካልሆኑ ሰዎች ጋር በመተባበር ኩፍርን ስለፈፀሙ እርሱ (መሐመድ) ስለ እነርሱ ካሉበት ኃላፊነቶች ነፃ ነው ማለት ነው፡፡

ይህንንም በማድረግ መሐመድ ተከታዮቹ ለግል ጥቅማቸው ወይንም ለግል ደስታቸው ሲሉ ሙስሊም ወዳልሆኑ ሃገራት እንዳይሰደዱ እና ሙስሊም ካልሆኑ ሕብረተሰቦች ጋር መስተጋብር እንዳይፈጥሩ ከልክሏቸዋል፡፡ ነገር ግን እስልምናን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ማስፋፋትን የመጨረሻ ግባቸው አድርገው በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት የሚሰደዱ ከሆነ ደስታና የግል ጥቅምን ማግኘት ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ይህ በማታለል የተሞላ የመሐመድ ወታደራዊ ስልት ነበር፡፡

በሌላ አባባል ከአስተናጋጁ ሕብረተሰብ ጋር "ምንም አይነት መደባለቅ የለም"፡፡ እንግዲህ አንድ ሰው የመኖርያ ፍቃዱ ወይንም ለኑሮ የሚያስፈልገው ነገር የተወሰነ ዓይነት መቀላቀል በማሳየት ጠላትን (ሙስሊም ያልሆነውን ተቀባይ ሕብረተሰብ) በማርካት ላይ የተመሰረተ ከሆነ እስላማዊ የማድረግ ግብ እስኪሳካ ድረስ የታይታ እና ጊዜያዊ መሆን አለበት፡፡[10] (ሙድዐራት የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

[10] http://www.islam-qa.com/en/ref/27211/???%20?????%20???%20 &http://www.islam-qa.com/en/ref/13694/???%20?????%20???%20

በተጨማሪም አቡ ዳኡድ በሐዲስ ቁጥር 2789[11] መሐመድ እንዲህ ማለቱን ዘግቧል "ሙስሊም ካልሆኑት ጋር በመወዳጀት ወይንም ከእነርሱ ጋር በመቀላቀል አብሯቸው የሚኖር ሰው ከእነርሱ እንደ አንዱ ነው፡፡" ይህም ማለት ይህንን የሚያደርግ ሰው እንደሙስሊም የማይቆጠር ሲሆን *ካፊር (የማያምን)* ተብሎ ለመፈረጅ የተጋለጠ ነው፡፡

አል ኃኪም በሌሎች ቃላት እንዲህ በማለት አስቀምጦታል "ሙስሊም ካልሆኑት ጋር አትስፈሩ ወይንም አትኑሩ ከእነርሱም ጋር ወዳጆች አትሁኑ ምክንያቱም ያንን የሚያደርግ ሰው ከእኛ ወገን አይደለምና"[12]

ራስን መነጠል *የአል ወላዕ ወ አል ባራዕ* (መወዳጀት እና አለመቀበል) አካል የሆነ የቁርአን መሰረታዊ አስተምህሮ ነው፡፡[13] ይህ ከብዙ ቁርአናዊ ጥቅሶች የተጨመቀ ቢሆንም ነገር ግን እኛ ሁለት ጥቅሶችን ብቻ እንጠቅሳለን፡

> ሱራ 58፡22 "በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣

11 http://www.al-eman.com/Hadeeth/viewchp.asp?BID=7&CID=34&SW=2787#SR1

12 አል ሙስተራክ ቅፅ 2 ገፅ 141

13 "ኮመን ዎርድ" ለሚለው አከራካሪ ጉዳይ በደራሲው በተፃፈ ምላሽ ላይ የዚህን ሰፋ ያለ ማብራርያ ይመልከቱ

ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፡፡ ከሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ያገባቸዋል፡፡ አላህ ከእነርሱ ወዷል፡፡ ከእርሱም ወደዋል፡፡ እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ንቁ! የአላህ ሕዝቦቹ እነርሱ ምኞታቸውን የሚያገኙ ናቸው፡፡"

ሱራ 9፡29 ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው፡፡

ይህ ራስን የመነጠል ትዕዛዝ ቀደም ሲል እንደተገለፀው መሰረቶቹ ቁርአናዊ ትዕዛዝ እና ሱና ናቸው፡፡ የመሐመድን ምሳሌነት በተመለከተ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የሐዲስ ማጣቀሻዎች በተጨማሪ የሐዲስ ሊቅ በሆነው ኢማም አቡ ሀኒፋ እና ዐኒሳኢ የተዘገበ አንድ ትውፊት እናከላለን፡

ኢማም አህመድ አቡ ሀኒፋ[14] እና ዐኒሳኢ[15] እንደዘገቡት ጀሪር የተባለ ሰው ለነቢዩ ቃልኪዳን ሊገባለት ሄደ፡፡ መሐመድም

[14] ሙስናድ አሕመድ ቅፅ 4/365
[15] ሱናን ዐኒሳኢ 4177

> የጀሪርን ቃልኪዳን ተቀብሎ ከመደገፉ በፊት የሚከተለውን ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠ “እርሱ (ጀሪር) አላህን እንዲያመልክ፣ መደበኛ ፀሎት እንዲፀልይ፣ *ዘካት* እንዲከፍል፣ ለሙስሊሞች ታማኝ እንዲሆን፣ ሙስሊም ባልሆኑት ላይ ኢድሎን እንዲፈፅም እና ከአረማውያን ወይንም መድብለ አማልክትን ከሚያመልኩ ሰዎች ራሱን እንዲለይ፡፡”

ከላይ የተቀመጠው የሚያመለክተው ሙስሊሞች ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ መኖርን ምርጫቸው ካደረጉ ቀዳሚ ዓላማቸው ሊሆን የሚገባው ስለ እስልምና ጥቅም ሲሉ ራሳቸውን ማጠናከር ነው፡፡ በአንድ ሃገር ውስጥ እስላማዊ የሆነ ስልጣንን ወይንም ደግሞ ሃገርን ማግኘት የሚችሉ ድምፃቸው የሚሰማ ማሕበረሰብ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ዋና ዓላማቸው ካልሆነ እና ለግል ጥቅማቸው ከሆነ ግን በኃይማኖታዊ ቋንቋ ስንናገር እስላማዊ ሃገር ካልሆነው ከአዲሱ አካባቢያቸው ወደ ሙስሊም ሃገር የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

ሆኖም ግን እውነታው አንድ ሰው ምንም ያህል ቢለፋ አንዴ የተሰደደ እንደሆን እንደ ከሃዲ *ሥርኣት* ከሚቆጠረው እስላማዊ ካልሆነ ሃገር ሕግጋት እና የሕግ *ሥርኣት* ጋር እንዲሁም በእስልምና *ካፊር* ተደርገው ከሚቆጠሩ ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር ያስፈልገዋል፡፡

ይህም ብዙዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲያነሱ አድርጓል፡

1. ሙስሊሞች ወደ ምዕራብ በገፍ የሚሰደዱት እና የሚባዙት ስለምንድነው?
2. እነዚህ መመርያዎች ባሉበት ሁኔታ ሙስሊሞች በምዕራባውያን ሃገራት ውስጥ መገኘታቸውን እንዴት ነው ማፅደቅ የሚችሉት?
3. ሙስሊሞች እየተሰደዱ ያሉት እስልምናን ባለመታዘዝ ነው ወይንስ ተቀባይነት ያለው ነገር ስለሆነ ነው? ተቀባይነት ያለው ከሆነ እንዴት እና በምን ሁኔታ ስር ነው?

በምዕራብ ሃገራት የሚገኙ ብዙ ምሑራኖቻችን የእስልምናን የተለያዩ አስተምህሮዎች ባለማወቅ እነዚህ ስደቶች በአብላጫው የኢኮኖሚ ጉዳዮች እንደሆኑ በመደምደም “እንዴት” ከሚሉት ጥያቄዎች በስተጀርባ ያሉትን አስተምህሮዎች መለየት ተስኗቸዋል፡፡

በሚያስደንቅ ሁኔታ ከላይ የተጠቀሰው ለምን የሚለው ጥያቄ (ቁጥር 1) ሙስሊም ወዳልሆኑ ሃገራት በተለይም ደግሞ ወደ ምዕራባውያን እየተሰደዱ የሚገኙትን ሙስሊሞች እስልምናን እንደ ኃይማኖት እንዲሁም እንደ ፖለቲካዊ እና ገዥ ሥርኣት እንዲያስፋፉ እና እንዲያጠናክሩ ትዕዛዝን ለመስጠት ሲታወጁ በነበሩ እና እየታወጁ በሚገኙ ብዙ *ፈቱዋዎች*[16] ግልፅ ተደርጓል፡፡ በእርግጥ የዚህ መጽሐፍ ርዕሰ ጉዳይ ይህንኑ አረፍተ ነገር ግልፅ ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ በእስልምና የሕግ አካሄድ እና ከፍተኛ

[16] አባሪ አንድን ይመ.

ተሰሚነት ባላቸው የእስልምና ሊቃውንት ላይ የተመሰረተውን ሙሉ አመክንዮ መረዳት ይችል ዘንድ እውነተኛ የሆነ አንባቢ አባሪ "ሀ" ላይ የሚገኘውን እንዲመለከት ይጠየቃል፡፡

በቁጥር 2 እና 3 ላይ የሚገኘው ለምን የሚለው ጥያቄ ማለትም ሙስሊሞች በምዕራብ ለመኖር የተጣለውን ክልከላ እንዴት ሕጋዊ እንደሚያደርጉ የሚጠይቀው ሥልታዊ ጠቀሜታው የላቀ ስለሆነ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

ከእስልምና የዕይታ ነጥብ አኳያ የተከለከለው ወይንም ደግሞ *ሐራም* የሆነው *ሐላል* ወይንም የተፈቀደ እንዴት ሆነ ለሚለው ምላሹ በሁለት እስላማዊ ዘርፎች ውስጥ ይገኛል፡

(ሀ) *ኃይማኖታዊ* የአስተምህሮ ትዕዛዛት

(ለ) እስላማዊ የሕግ አካሄድ *መመሪያዎች*

ሁለቱም *ኃይማኖታዊ* የአስተምህሮ ትዕዛዛት እና እስላማዊ የሕግ አካሄድ *መመሪያዎች* አንድ ላይ የተሰባጠሩ ናቸው ስለዚህ ሰዎች የሚከተሉት እስላማዊ የሕግ አካሄድ *መመሪያዎችን* ነው፡፡ ነገር ግን የሕግ ባለሙያዎች የሚያወጧቸው እነዚህ *መመሪያዎች* የተመሰረቱት እና ተመዘው የሚወጡት ከ*ኃይማኖታዊ* አስተምህሮዎች ነው፡፡ እነዚህ *ኃማኖታዊ* አስተምህሮዎች ደግሞ ከሚቀዱባቸው ምንጮች የተነሳ ትክክለኛ እና ተግባራዊ ናቸው፡፡

እነዚህ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ከሁለት ምንጮች የተቀዱ ናቸው፡፡ ሁለቱም ምንጮች ደግሞ ዋና ምንጮች ናቸው፤ እነዚህም ቁርአን እና ሱና ወይንም ደግሞ የነቢዩ ምሳሌነቶች ናቸው፡፡

# *የሕግ አካሄድ መመሪያዎችን አመጣጥ መረዳት*

ሕጋዊ መመሪያዎች በሙስሊም ሊቃውንት የሚታወጁት በቁርአን ስልጣናዊ ትምህርቶች እና *በሱና* ወይንም የመሐመድ ምሳሌነት ማለትም በተግባራቱ፣ ንግግሩ ወይንም ደግሞ እርሱ ባፀደቀው ነገር ላይ በመመስረት ነው፡፡ ሁለቱን አንድ ላይ በትክክል መጠቀም ፅንሰ ሐሳቦችን ወይንም ደግሞ አስተምህሮዎችን ይፈጥራል፡፡

እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች እና አስተምህሮዎች ደግሞ በተራቸው በዘርፎች ወይንም ደግሞ ምን፣ በምን ሁኔታዎች ስር፣ መቼ እና ለማን እንደተፈቀደ በሚያብራሩ ዘርፎች ስር ይከፋፈላሉ!

ስለዚህ እስኪ *"የተከለከለው የተፈቀደ ወደመሆን እንዴት ተለወጠ?"* ወደሚለው ጥያቄያችን እንመለስ፡፡

# በታይዕሲር *ሁኔታዎችን ማመቻቸት*

ለአዲስ ስደተኞች እና ለሚሰልሙ ሰዎች የመነሻ ነጥብ ዝውውራቸውን ቀለል ባለ ውል አማካይነት ማመቻቸት ነው፡፡ እስልምና የሚያዛቸውን ሁሉ ማድረግ በመጨረሻ ሸክማቸውን ለማቃለል የሚደረግ ነው፡፡ መሐመድ ይህንን ያገኘው *ታይዐሱር* ወይንም *ታይዕሲር* የተሰኘ ፅንሰ ሐሳብ በመፍጠር ነው፡፡ የዚህም ትርጉም "ማቃለል፣ ማመቻቸት" ወይንም ደግሞ "የአንድን ሰው ሸክም ማቃለል" ማለት ሲሆን በሚከተሉት ደመቅ ባለ ቀለም በተፃፉ የቁርአን ጥቅሶች ክፍሎች ላይ የተመሰረተ ነው፡

ሱራ 2፡185 “(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ **አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡** ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)፡፡”

ሱራ 4፡28 “**አላህ ከእናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል፡፡** ሰውም ደካማ ኾኖ ተፈጠረ፡፡”

ሱራ 2፡286 “**አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡** ለርስዋ የሠራችው አላት፡፡ በርስዋም ላይ ያፈራችው (ኀጢአት) አለባት፡፡ (በሉ)፡- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፤ (አትቅጣን)፡፡ **ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን፡፡** ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን፡፡ ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምሕረት አድርግ፡፡ እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና፡፡ በከሓዲዎች ሕዝቦች ላይም እርዳን፡፡”

> ሱራ 65፡7 “የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ፡፡ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይቀልብ አላህ **ነፍስን የሰጣትን እንጅ አያስገድድም፡፡** አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል፡፡”

በሌላ አባባል በኃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ እና በሌሎች በማናቸውም አቅጣጫዎች ሁሉ የሙስሊሞችን ሸክም ማቃለል የአላህ መሻት እና ፍቃድ ነው፡፡ ነገር ግን ያ ማለት ከሁሉም ሰው ላይ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነትን መውሰድ ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ ዘርፉ ኃላፊነቱን መሸከም የማይችሉትን ወይንም ደግሞ ውሱን የሆነ አቅም ያላቸውን ወይንም ደግሞ ደካማ የሆኑትን ወዘተ. ብቻ እንዲሁም ችግሮቻቸውን ለማሸነፍ ትዕዛዛቱን የሚፈልጉትን ወደማጠቃለል አንሷል፡፡ ስለዚህ በውጪ ሲታዩ  ትዕዛዝ እየጣሱ ያሉ ቢመስሉም ነገር ግን በውስጥ አዋቂነት ከእነርሱ ሚፈለገውን ማንኛውንም ነገር እየፈፀሙ ነው፡፡

በሌላ አባባል ፍላጎት አላቸው ማለት ነው፡፡ ይህ ፍላጎት ደግሞ ሌላ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ፍላጎት እስልምናን የማስፋፋት ቅንዓት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በግል ድካሞቻቸው ምክንያት ከጠላቶቻቸው ጋር በማመቻመች ያንን ማድረግ ተስኗቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የጠላት አኗኗር ምናልባትም ማራኪ ሊሆን ይችላል ወዘተ. ወይንም ደግሞ በሌላ ወገን ምናልባት የግል ድካም ሳይሆን ነገር ግን አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አስገዳጅ ሁኔታ

ምናልባት ከእስልምና አስተምህሮዎች በተፃራሪ ሴቶች እና ወንዶች በተደባለቁበት አካባቢ መስራት ወይንም ደግሞ አሳማ እና አልኮልን የመሳሰሉ የተከለከሉ ምርቶችን ማቅረብ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አባባል ከአንድ ሰው ፍላጎት ውጪ በግድ የተጫነ ነገር ማለት ነው፡፡ ድብቅ የሆኑ ሁኔታዎች፣ ተጨባጭ የሆኑ ችግሮች ወይንም ደግሞ እንዲሁ በውስጠ አዋቂነት የሚታወቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንስኤዎቹ ምንም ሆኑ ምን እነዚህ በቁርአን መሰረት ዱሩርዐ (የግድ የሚያስፈልጉ ነገሮች) በመባል ተለይተዋል፡፡

## ዱሩርዐ (የግድ የሚያስፈልጉ ነገሮች)

እነዚህ "የግድ የሚያስፈልጉ ወይንም ደግሞ አስገዳጅ ሁኔታዎች" የሚባሉት በአነስተኛ ዘርፎች እና መሐመድ በሕይወቱ ውስጥ ላጋጠሙት አስፈላጊ ነገሮች ምላሽን በመስጠት የቁርአንን መገለጦች በገዛ ሕይወቱ ሙሉ ባደረጋቸው ነገሮች የሚመሩ ናቸው፡፡

ስለ ዱሩርዐ የሚናገሩ የተወሰኑ የቁርአን ጥቅሶች እነሆ፡

> ሱራ 6፡119 "ወደርሱም (መብላት) ከተገደዳችሁበት በስተቀር በእናንተ ላይ እርም የተደረገውን ለእናንተ (አላህ) በእርግጥ የዘረዘረ ሲኾን ከዚያ በእርሱ ላይ የአላህ ስም ከተጠራበት የማትበሉት ለናንተ ምን (ምክንያት) አላችሁ? ብዙዎቹም ያለ ዕውቀት በዝንባሌዎቻቸው ያሳስታሉ፡፡ ጌታህ እርሱ ወሰን አላፊዎቹን ዐዋቂ ነው፡፡"

> ሱራ 5፡3 “በክት፣ ፈሳሽ ደምም፣ የእሪያ (አሣማ) *ሥጋም*፣ በርሱ ከአላህ (ስም) ሌላ የተነሳበትም፣ የታነቀችም፣ ተደብድባ የተገደለችም፣ ተንከባላ የሞተችም፣ በቀንድ ተውግታ የሞተችም፣ ከርሷ አውሬ የበላላትም (ከእነዚህ በሕይወት ደርሳችሁ) ያረዳችሁት ብቻ ሲቀር ለጣዖታትም የታረደው በአዝላምም ዕድልን መፈለጋችሁ በእናንተ ላይ እርም ተደረገ፡፡ ይህ ድርጊት አመጽ ነው፡፡ ዛሬ እነዚያ የካዱት ከሃይማኖታችሁ ተስፋ ቆረጡ፡፡ ስለዚህ አትፍሩዋቸው፡፡ ፍሩኝም፡፡ ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡ በረኃብ ወቅት ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ሳይሆን (እርም የኾኑትን ለመብላት) የተገደደ ሰውም (ይብላ)፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡”

ስለዚህ *በዱሩርዐ* (የግድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች) ስር የተከለከለው ይፈቀዳል፣ ልዩ ሁኔታ ሕግ ይሆናል ሕግ ደግሞ ሁኔታዎች እስኪቀየሩ ድረስ ወይንም ደግሞ ዓላማ ግብ እስከሚመታ ድረስ ይታገዳል፡፡ ስለዚህ ይህ መርህ ሙስሊሞች ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ የሚገጥሟቸውን እንቅፋቶች ሁሉ ለማለፍ፤ ከመኖርያ ፈቃድ ደንቦች አንስቶ የአስተናጋጇን ሃገር ዜግነት እስከማግኘት እና እስላማዊ *ሸሪኣን* ቀስ በቀስ እስከማስገባት ድረስ በስራ ላይ ይውላል፡፡ (ለምሳሌ ያህል በዩ ኬ ውስጥ ለነዚያ ሁሉ ዓመታት በገበያ አዳራሾች ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሙስሊሞች ደካሞች

በመሆናቸው ምክንያት የአሳማ ስጋ እና አልኮል ሲያቀብሉ የነበሩ ሲሆን *የዱሩርዐ* ፅንሰ ሐሳብ በተግባር ላይ ይውል ነበር፡፡ ነገር ግን የሙስሊም ማህበረሰብ በቁጥር እና በጥንካሬ ካደገ በኋላ በቀጣሪዎቻቸው ላይ ተቃውሞን በማሰማት አበረታች ውጤቶችን አግኝተዋል፡፡)

*ደሩርዐ* የሙስሊም ማሕበረሰቦችን ፍላጎት መፈፀምን ይፈቅዳል፡፡ እነዚህም ደግሞ በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን አመለካከት ተከትለው ሊለወጡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በመጨረሻ እነዚህ ጥያቄዎች በሕጎች ውስጥ የሚገኙ ክፍተቶችን በመጠቀም ግብ እንዲመቱ ይደረጋል፡፡ ይህ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የሚፈፀም ሲሆን ብዙ ጊዜ ግን ከዚህ በፊት የነበሩትን የሕግ አካሄዶች በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህም ነገሮች በአስተናጋጇ ሃገር የተለያዩ ክልሎች እና ግዛቶች ውስጥ ዝግ በሆኑ የሙስሊም ማሕበረሰቦች መካከል ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ እነርሱም ብዙ ጊዜ ከመንግሥት ጋር ጥሩ ግንኙነት ባላቸው እና ለዘብተኛ እንዲሁም ለሕግ የሚገዙ በሚመስሉ መስጊዶቻቸው እና ሌሎች እስላማዊ ተቋሞቻቸው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ የአስተናጋጁን ማሕበረሰብ "አጠቃላይ ለውጥ" የተቀናጀ መርሐ ግብር በሚቆጣጠሩ ሰዎች እና ተቋማት መረብ በኩል ሥራቸውን ይሰራሉ፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለው እነዚህ ሁሉ ፍላጎቶች ብዙ ጊዜ ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ኃይማኖታቸውን በለወጡ ጥሩ አቀባበል

በተደረገላቸው እና በጥሩ ሁኔታ በሰለጠኑ ሰዎች አማካይነት እንደ ጥያቄዎች እና ሕጋዊ የኃይማኖት መብቶች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ የፍላጎት ጥያቄዎች አስተናጋጁ ማሕበረሰብ እንደ ኢምንት በሚቆጥራቸው በተለያዩ ጉዳዮች ዙርያ በተበታተነ ሁኔታ እዚህም እዚያም ይቀርባሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ የፍላጎት ጥያቄዎች አጠቃላይ ሥርኣቱን በመቀልበስ የመበታተን ውስጣዊ እምቅ አቅም ያላቸው ሲሆን ይህም ሁኔታ ደረጃ በደረጃ በስተመጨረሻ ወደ ሸሪአ (እስላማዊ ህግ) ይመራል፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አስተናጋጁ ማሕበረሰብ እስላማዊ ልምምዶችን እና የኑሮ ዘይቤን እንዲቀበል ቅድመ ሁኔታ ስለሚቀመጥበት፣ አዲስ ልምምድ ስለሚሆንበት፣ አብሮት እንዲኖር ስለሚደረግ እና በስተመጨረሻም የዚያ አካል እንዲሆን ስለሚደረግ ከከፍተኛ ፍርሃት እና ድንጋጤ የመነጩ ምላሾችን በመስጠት እንደ አዲስ ክስተት መመልከት ይጀምራል፡፡

ለምሳሌ ያህል ቀላል ጉዳይ የሆነውን እስላማዊ የአለባበስ ሥርኣት እስኪ አስቡ፡፡ አንዳንዶች ባሕላዊ እንደሆነ የሚያስቡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ኃይማኖታዊ ነው ይላሉ፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ ሴቶችን ዝቅ በማድረግ እኩል እንዳልሆኑ፣ የተቃወሰ አዕምሮ እንዳላቸው እና በአደባባይ መታየት እንደማይገባው ነገር ያቀርባቸዋል፡፡ የአለባበስ ሥርኣቱ በሙስሊሞች መቼት ውስጥ የተገለለ ማሕበረሰብን ፅንሰ

ሐሳብ ያስከትላል፡፡ ከጊዜ በኋላም የተገለለው ማሕበረሰብ እና መመሪያዎቹ ሁሉ እስላማዊ ደንቦች በመሆን ያልቅላቸዋል፡፡

አስተናጋጁ ሕብረተሰብ የተገለለውን የሙስሊም ሕብረተረሰብ አንዴ ከተቀበለ የተለዩ የመዋኛ ገንዳዎች እንዲኖሩ ወይንም ደግሞ ወንዶች እንዲገቡ የማይፈቀዱባቸው ጊዜያት እንዲኖሩ ጥያቄ ይቀርባል፡፡ ይህም አንዴ ከተሳካ ጥያቄዎቹ ወደ ትምህርት ቤቶች እና ወደ ሌሎች የሕዝብ መሰብሰብያዎች ይሸጋገራሉ፡፡ ሙስሊም ሆነም አልሆነም ወንድ ዶክተር ሙስሊም ሴትን እንዳይመረምር ጥያቄ ስለሚቀርብ  ሆስፒታሎች እና ክሊኒኮች ሴት ዶክተሮችን ለማቅረብ ይገደዳሉ፡፡ ከዚህ መመርያ የተነሳ ጠንከር ያሉ ተቃውሞዎች ይሰማሉ ነገር ግን ጠቅላላው ማሕበረሰብ እና ሃገር በማያስተውሉበት ሁኔታ ሸሪኣ አፍንጫቸው ስር ይተገበራል፡፡ይህ እንግዲህ እስላማዊው አጀንዳ ከሁሉም ፅንፎች እንዴት እየተሳበ እንደሚመጣ ለማሳየት አንድ ምሳሌ ብቻ ነው፡፡

የሰዑዲ አረብያ ኡላማ ሊቀ መንበር የነበሩት እና የሰዑዲ ግንባር ቀደም ሊቅ የሆኑት ሼኽ ባዝ[17] የሚከተለውን ጥያቄ ተጠይቀው ነበር፡ “አንድ ሰው ሚስቱን አስከትሎ ወደ አረማውያን ሃገር

[17] እጅግ እውቅ የሰዑዲ አረብያ እስላማዊ ሊቅ የሆኑት ሼኽ አብደል አዚዝ ቢን አብዱላህ ብን ባዝ በ1910 የተወለዱ ሲሆን በ27 ዓመታቸው የህግ ባለሙያ ሆነው በተለያዩ የስልጣን እርከኖች ላይ የተሸሙ ሲሆኑ የሰዑዲ አረብያ ግንባር ቀደም ሊቃውንት ሊቀ መንበር፣ የጥናት እና *የፈትዋ* ክፍል መሪ፣ የዓለም እስላማዊ ሊግ መስራች እና መሪ፣ የዓለም የመስጊዶች ምክርቤት መሪ፣ የብዙ መጽሐፍት እና መጣጥፎች ደራሲ፣ በሙቶዎች የሚቆጠሩትን *ፈትዋዎች* ያወጁ ሰው ነበሩ፡፡ ሕይወታቸው ያለፈው በ2000 ዓ.ም. ነበር፡፡

መኳዙን በተመለከተ ያለው እስላማዊ አመለካከት ምንድነው?" ምላሻቸውም የሚከተለውን ይመስል ነበር፡[18] ወደ አረማውያን ምድር በመሄድ መኖር የተከለከለ ነው ነገር ግን ኃይማኖታቸውን የሚያውቁ እና እስልምናን ማስፋፋት የሚችሉ፣ ራሳቸውን መጠበቅ የሚችሉ እንዲሁም በአረማውያን ክፉ ማታለል የማይጠለፉ ሰዎች ቢሄዱ ምንም ተቃውሞ የለም፤ ከእነዚህም ክልከላዎች መካከል አንዱም እንኳ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

ሌላ ሳሌህ አል ፋውዛን የተባሉ እጅግ ታዋቂ የሆኑ ሊቅ እና የህግ ባለሙያ እንዲህ በማለት ያክላሉ፡[19] እስልምናን ከመስበክ ጎን ለጎን ሌላው ዓላማ በከሃዲዎች ምድር ያሉትን ሙስሊም ማሕበረሰቦች ማጠናከር መሆን አለበት፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱም እንኳ የሙስሊም ስደተኛ ዓላማ ካልሆነ በመሰደዱ ምክንያት ኃጢአትን ሰርቷል፡፡

[18] http://www.sobe3.com/vb/showthread.php?t=4128
[19] ዝኒ ከማሁ

## *የትክክለኛ እስላማዊ ስደቶች ምክንያቶች እና ግቦች*

በመሐመድ ከ1400 ዓመታት በፊት የተጀመረው እስላማዊ ወረራ እንዳከተመ የሚያስብ ሰው ካለ ተሳስቷል፡፡ መሐመድ የጀመረው ወረራ ከሞስኮ እስከ ኒውዮርክ ከባርሴሎና እስከ ብራዚል ቀጥሏል፡፡ እስላማዊ በሆነ መንገድ ስንናገር *ሂጅራ* ወይንም ስደት ከ1400 ዓመታት በፊት ከመካ ወደ መዲና የተደረገ ብቻ እንደሆነ የሚያስብ ሰው እንዲሁ ተሳስቷል፡፡ ምክንያቱም መሐመድ እንዲህ ብሏልና፡

> "ፀሐይ በስተ ምዕራብ እስክትወጣ ድረስ ስደት ይቀጥላል፣ ንስሐ እስኪያከትም ድረስ *ሂጅራ* አይቆምም፣ ፀሐይ በስተ ምዕራብ እስክትወጣ ድረስ ደግሞ ንስሐ አያከትምም፡፡"
>
> በአህመድ እና በአቡ ዳውድ የተዘገበ ሐዲስ ቁጥር 3453

*ሂጅራ* (ስደት) አንድ ቦታ፣ ማሕበረሰብ ወይንም ሃገር በቁጥጥር ስር እስኪሆን በእስላማዊ አነጋገር *ፋቴህ* (ድል) እስኪገኝ ድረስ አይቆምም፡፡ በሐዲስ ቁጥር 3455 ላይ እንደተጠቀሰው ያኔ ብቻ

ነው *ሂጅራ* ሊቆም የሚችለው፡፡ በሌላ አነጋር ሙስሊም ስደተኞች እንቅስቃሴያቸውን የሚቀጥሉ ቢሆኑም ያ አካባቢ እንደ እስላማዊ ይዞታ ስለሚቆጠር ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ የሚደረግ ውስጣዊ እንቅስቃሴ ብቻ እንደሆነ ነው የሚታሰበው፡፡ ይህም በቶሮንቶ ካናዳ ውስጥ እንደሚገኘው እንደ ሚሲሳውጋ፣ በዮርክ ሻየር እንግሊዝ ውስጥ እንደሚገኘው እንደ ዴውስበሪ ግዙፍ በሆነ ሙስሊም ማሕበረሰብ ቁጥጥር ስር የገባ ክፍለ ከተማ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሙስሊሞች የበላይ በመሆን የተለያዩ እስላማዊ ተቋማትን የሃገሪቱን ህግ ችላ ባለ ሁኔታ ያንቀሳቅሳሉ፡፡ በእንዲህ ሁኔታም ከተሞች *ሸሪኣን* እንደ አገዛዝ ዓይነት በመቀበል ለእስላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ይዳርጋሉ፡፡ ስለዚህ አዲስ መጪዎች ወይንም ስደተኞች አካባቢው *ዳር አል ኩፍር* ወይንም የከሃዲዎች ቀጠና በነበረ ጊዜ የመጀመርያዎቹ ሰፋሪዎች የነበሯቸውን ዓይነት ከልክ ያለፉ ሁኔታዎች እና ዋስትናዎች አያገኙም፡፡

ነገር ግን የአዲስ መጪዎች ኃላፊነት ከመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች የከበደ በመሆኑ ሽልማታቸውም የላቀ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው መሐመድ እንዲህ ብሏል፡

> “ከድል በኋላ *ሂጅራ* (ስደት የለም) ነገር ግን *ጂሃድ* እና ውስጣዊ መሻት ብቻ ነው፤ አንዴ ከሰፈራችሁ ተስፋፉ፡፡” (በቡኻሪ የተዘገበ)

በሌላ አባባል የሙስሊም ማሕበረሰብ ከመስጊዶች እና ከሌሎች እስላማዊ ተቋማት ጋር የሚመሰረት ቢሆንም የተፅዕኖ ክልሉ የተመጠነ እና *በኩፍር* (አለማመን) የተከበበ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ስለ አላህ *ጂሃድን* ማወጅ እና እስልምና በመፈራት ተገቢውን ክብር እንዲያገኝ ማስቻል የአዲስ መጪዎች ወይንም የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ልጆች *ሥራ* ነው የሚሆነው፡፡

ስለዚህ አዲስ ሰፋሪ የሆኑት ማሕበረሰቦቻቸው አፈሴላዊ በሆነ ሁኔታ ስደተኞች እንደሆኑ የማይታሰቡ ስለአላህ ብለው *ጂሃድን* የማወጅ ፍላጎት ያላቸው እና እስልምናን ወደፊት የሚያራምዱ ሦስተኛ ወይንም አራተኛ ትውልዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ (ልክ በዩ ኬ እና በሌሎች የአውሮፓ ክፍሎች እንደሚታየው ማለት ነው፡፡) ትክክለኛው የሽብርተኝነት ስጋት የሚመጣው ከነዚህ አካባቢዎች ነው፡፡ የጂሃድ ፅንሰ ሐሳብ እና ተጨማሪ መሬቶችን ስለመውሰድ *ጂሃድ እና እርሱን መፈለግ* በሚል ርዕስ በሼኽ ዐዘመል በተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ በስፋት እና በጥልቀት ተነግሯል፡፡ መጽሐፉም በመገናኛ መረብ ላይ ይገኛል፡፡[20]

ወደ *ሂጅራ* ወይንም የሙስሊም ስደቶች መለስ ብለን ስናይ በተፈጥሯቸው ከሌሎች የስደት ዓይነቶች ይለያሉ፡፡ ምክንያቱም *ሂጅራ* እንደ እስላማዊ ፅንሰ ሐሳብ የመኖርያ አካባቢን መቀየር

[20] Sheik Abdel Muhssen bin Abdullah A'zamaal http://www.taimiah.org/Display.asp?ID=94&t=book80&pid=2&f=bmr00081.htm

ማለት ብቻ አይደለም ነገር ግን የመረዳት፣ የልማዶች፣ የጠባይ፣ የደንቦች እና የስርኣቶች ለውጥ ማለት ነው፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ እስላማዊ ባይሆንም ነገር ግን እስልምናን በሚደግፍ የፖለቲካ ኃይል መሰረት በመጠቀም ነው፡፡ ስለዚህ ከነፃነት ለአላህ ባርያዎች ወደመሆን የሚደረግ ለውጥ ነው፡፡

# *የስደት ግብ*

"እንዴት" የሚለውን የማፅደቅ ጥያቄ ወይንም ሁሉንም ደንቦች በማገድ ከልክ ያለፉ ደንቦችን ተግባራዊ የሚያደርገውን "ሸክምን ማቅለል" እና *ደሩርዐን* (የግድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን) ከተመለከትን ዘንዳ አሁን ደግሞ ወደ እስላማዊ ስደት ዓላማዎች እና ግቦች እንዲሁም እነዚህ ዓላማዎች እና ግቦች የሚመሩባቸውን መመሪያዎች ወደ ማየት እናተኩራለን፡፡

*የሂጅራ* (እስላማዊ ስደት) ዋነኛ ግብ የእስላማዊ መንግሥት ምስረታ ነው፡፡ ይህም *በዳዐዋ* በኩል ነው፡፡ *ዳዐዋ* ማለት "መጥራት" ማለት ነው፡፡ በእስላማዊ አነጋገር "ወደ እስልምና መጥራት" ማለት ሲሆን እስልምናን ለመቀበል የሚደረግ የሚስዮን ጥሪ ነው፡፡ በግል የመስለም ጥሪ አይደለም ነገር ግን ውጭያዊ ገፅታው እንደርሱ ሊመስል ይችላል፡፡ *ዳዐዋ* ኃይማኖታዊም ፖለቲካዊም ነው ምክንቱም በእስልምና በተቀደሰው እና በፖለቲካ እንዲሁም በመንግሥት እና በኃይማኖት መካከል ልዩነት የለምና፡፡

ዳዕዋ የእስልምናን መልዕክት በማስፋፋት እስላማዊ ምንግሥት የማቋቋም ጉዳይ ነው፡፡ እስልምናን ማስፋፋት እንደ ቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊነት ሥራ ብቻ አይደለም ነገር ግን እስላማዊ መንግሥት ለመመስረት እንደ አላህ ሰራዊቶች ሊነሱ የሚችሉ ማሕበረሰቦችን ማቋቋም ነው፡፡ እስላማዊው መግለጫ እና አዋጁ የሚደመድሙት የዚህች ዓለም የፖለቲከ ኃይል እና መንግሥታት በሙሉ የአላህ እና የመልእከተኛው የመሐመድ መሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህ ትክክለኛዎቹ ውሳኔ ሰጪዎች አላህ እና መልእከተኛው ናቸው፡፡ የተቀሩት ሁሉም ውሳኔዎች ሰው ሰራሽ ናቸው እናም እንደ ኩፍር ወይንም አለማመን እና እንደ ክህደት ሊቆጠሩ ይገባቸዋል (ይህንን ሰፋ ባለ ሁኔታ *ተምኪን* በሚለው ርዕስ ስር እንመለከታለን)፡፡ ከዚህ የተነሳ ከኃይማታዊ እና የህግ አተገባበር አኳያ *ሂጅራ* በሙስሊም ሊቃውንት ለጂሃድ እና ለእስላማዊ መንግሥት ምስረታ እንደ መንገድ ጠራጊ እና ቅድመ ሁኔታ ይታያል፡፡

ይህ ጉዳይ በሼኽ መንሱር ግልፅ ተደርጓል፡፡[21] እንዲህ አሉ፡ በቁርአን መሰረት *ሂጅራ* ከእምነት ቀጥሎ የሚመጣ እና በአላህ መንገድ ጂሃድን ማወጅ የሚያስከትል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ስደት በራሱ እምነት ሲሆን *የሂጅራ* ተግባራዊ ውጤት ደግሞ በአላህ መንገድ ጂሃድን ማወጅ ነው፡፡

---

[21] ሼኽ ዶ/ር መሐመድ ሙተዋሊ መንሱር በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሲሆኑ የብዙ እስላማዊ መፃሕፍት ደራሲ፣ እጅግ እውቅ ተናጋሪ እና የብዙ እስላማዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች አዘጋጅ ናቸው፡፡ http://www.islamonline.net/arabic/Daawa/2006/02/article01.shtml

መንሱር እና ሌሎች ሙስሊም ሊቃውንት እምነታቸውን የመሰረቱት በሚከተሉት የቁርአን ጥቅሶች ላይ ነው፡

> ሱራ 2፡118 "እነዚያ ያመኑትና እነዚያም (ከአገራቸው) የተሰደዱት በአላህም መንገድ ላይ የተጋደሉት እነዚያ የአላህን እዝነት ይከጅላሉ፡፡ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡"
>
> ሱራ 8፡72 "እነዚያ ያመኑና የተሰደዱ፡፡ በአላህም መንገድ ላይ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የታገሉ፡፡ እነዚያም (ስደተኞቹን) ያስጠጉና የረዱ፡፡ እነዚያ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ እነዚያም ያመኑና ያልተሰደዱ እስከሚሰደዱ ድረስ ከነሱ ምንም ዝምድና የላችሁም፡፡ በሃይማኖትም እርዳታን ቢፈልጉባችሁ በእናንተና በነሱ መካከል ቃል ኪዳን ባላችሁ ሕዝቦች ላይ ካልኾነ በስተቀር በናንተ ላይ መርዳት አለባችሁ፡፡ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡"
>
> ሱራ 8፡74 "እነዚያም ያመኑና የተሰደዱ በአላህም መንገድ ላይ የታገሉ፣ እነዚያም ያስጠጉና የረዱ እነዚያ እነሱ በእውነት አማኞች ናቸው፡፡ ለእነሱም ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አላቸው፡፡"
>
> ሱራ 9፡20 "እነዚያ ያመኑት፣ ከአገራቸውም የተሰደዱት፣ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡"

ሼኽ ሀሊማ[22] እንደተናገሩት ከሂጅራ ዓላማዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

1. ጂሃድን ለማነሳሳት
2. ሙስሊሞችን ለማጠናከር
3. ኃይላቸውን ከማያምኑ ሰዎች በላይ ከፍ ለማድረግ

ሂጅራ እና ጂሃድ የማይነጣጠሉ ጓደኞሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ (ሂጅራ እና ጂሃድ) ህልውና ይኖራቸው ዘንድ አንዳቸው ለሌላቸው ያስፈልጋሉ፡፡ ይህ ሁሉ ከላይ በተጠቀሱት የቁርአን ጥቅሶች በሚገባ ተገልጿል፡፡ በማስከተልም እንዲህ አለ፡

> "ያለ ሒጅራ ወይንም ስደት ኃይማኖታዊ አቅም የለም፡፡ ሙስሊሞች ወደዚያ በመሰደድ ካልሰፈሩ በስተቀር እስልምና ባለማመን ይዞታ ውስጥ ሊገለጥ አይችልም፡፡ የሙስሊሞች ቁጥር ጥቂት ሆኖ የሚቆይ ከሆነ እና በአዳዲስ እና ተጨማሪ ሙስሊም ሰፋሪዎች በመታገዝ ቁጥራቸው ከፍ ካላለ በስተቀር የእስልምና ኃይል ሊታወቅ አይችልም፡፡"
>
> http://www.saaid.net/Doat/Zugail/166.htm

የወሃቢዝም መስራች የሆነው መሐመድ አብዱል[23] ወሃብ ስለ ጂሃድ በጻፈው መጽሐፉ ውስጥ[24] እምነታቸውን በግልፅ መለማመድ እና

[22] አቡ በሲር አተርሱሲ በሚለው ቅፅል ስሙ የሚታወቅ ሲሆን ለኃይማኖቱ ሲል ሃገሩ ሦርያን ለቆ የወጣ ዕውቅ ሰው ነው፡፡
[23] የወሃቢዝም መስራች ሲሆን በኢብን ተይሚያ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድሮበታል

ማሳየት በሚችሉ ሰዎች ላይ ሒጅራ ግዴታ መሆኑን ምክንያቱ ደግሞ ጂሃድን ማድረግ እና የሙስሊሞችን ቁጥር ማብዛት እንደሚችሉ ጽፏል፡፡

በጣም ታዋቂ ሙስሊም አሳቢ የሆኑት ሼኽ ሁሴን ሻሀታት[25] እንደተናገሩት ከመካ ወደ መዲና የተደረገው ሂጅራ ለአላህ ኃይማኖት እና እስላማዊ መንግሥት ለማቋቋም እንዲሁም እንደ ምሳሌ እና ሰርቶ ማሳያ በመላው ዓለም ላይ ለማንሰራፋት ተብሎ የተደረገ ነበር፡፡ ከመካ ወደ መዲና የተደረገው ስደት ለኃይማኖት ተብሎ እንደተደረገ ጂሃድ ይታሰባል፡፡ በሌላ አነጋገር የመሐመድ ሒጅራ የሰው ሥራ ሳይሆን ነገር ግን አስቀድሞ የተወሰነ እና የአላህን ኃይማኖት ለማፅናት በማሳብ ያደረገው ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ከሒጅራ ጋር ተያይዞ አዲስ የሙስሊም ማሕበረሰብ መጥቷልና፤ ከማሕበረሰቡም ጋር የአዲስ ህግ አስፈላጊነት ይፋ ሆኗል፤ ከዚያም እስላማዊው መንግሥት ተግባራዊ ሆኗል፤ ከዚያም የሰላም እና የጦርነት መርሆች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ታክስ፣ ሙስሊም ካልሆኑት ጋር የስምምነት ውል መፈራረም፣ የሙስሊሞች ጠባይ

---

[24] http://www.kl28.com/books/showbook.php?bID=37&pNo=1

[25] http://www.ikhwanonline.com/Article.asp?ArtID=33506&SecID=363 ዶ/ር ሽሐታት ከብራድፎርድ ዩኒቨርሲቲ ዩ ኬ በፍልስፍና ፒ ኤች ዲ ያገኙ ሲሆኑ በእስልማዊ ፋይናንስ፣ ዘካት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ዕውቅና ያላቸው ሊቅ እንዲሁም በብዙ እስላማዊ ጉዳዮች ላይ እስላማዊ አሳቢ እና ጸሐፊ ናቸው፡፡

እና የየዕለት ሕይወታቸውን እንዴት እንደሚመሩ የሚናገር ውሳኔ ይፋ ሆኗል፡፡

በካይሮ ዩኒቨርሲቲ የእስላማዊ ህግ ፕሮፌሰር እና የአሜሪካ እስላማዊ ዩኒቨርሲቲ መሪ የሆኑት ዶ/ር ሳላዐዲን ሱልጣን[26] እንደተናገሩት የጥቂት ሙስሊሞች በምዕራብ ሃገራት ውስጥ መስፈር የእስልምናን መልዕክት ለማወጅ ሙስሊሙን ማሕበረሰብ እንደ አዲስ ኃይል መፍጠር እና ከእንደገና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው "የእስልምናን መልዕክት ማወጅ" ሁሉን የሚያጠቃልል ስልታዊ ንግግር ሲሆን ቀለል ባለ አነጋገር ጊዜው ሲደርስ *የሸሪኣን* ህግ እንደ ኑሮ ዘይቤ የሚያስተዋውቅ እና በኃይል የሚጭን እስላማዊ ማሕበረሰብ ማቋቋም ማለት ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተባሉት ላይ በመመስረት ከእስልምና የህግ አካሄድ አንፃር ወደ ምዕራብ ሃገራት የሚደረገው የሙስሊሞች ስደት እስላማዊ መንግሥት በምዕራብ ሃገራት ውስጥ ለማቋቋም በሚያስችለው መሰላል ላይ ለመውጣት ከሁሉም የላቀ እርምጃ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ በምዕራብ ውስጥ የእስላማዊ ተልዕኮ ዋና ዓላማ ነው፡፡

---

[26] በባህሬን ይኖር የሆነ ታዋቂ ትውልደ ግብፃዊ ሙስሊም ሰባኪ ሲሆኑ በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የፕሮፌሰር ማዕረግ አላቸው፡- ባህሬን፣ ካይሮ፣ ኮሎምበስ ኦሀዮ፣ ሚችጋን፣ ኦፐን አሜሪካን ዩኒቨርሲቲ፣ ቦስተን፡፡ የብዙ ማጻሕፍቶች እና መጣጥፎች ደራሲ፣ እንዲሁም በእስላማዊ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ሐተታ ሰጪ እና ብዙ ፈትዋዎችን ያወጁ ናቸው፡፡
http://www.islamonline.net/Arabic/Daawa/2003/08/article09.shtml

ይህ ሼኽ አብዱል ኻሊቅ[27] *በምዕራብ የእስላማዊ ተልዕኮ ዋና ዓላማዎች*[28] በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ውስጥ ያሰፈሩት ነው፡፡ ብዙ ነገሮችን ጨምሮ እንደ አስተያየት የሰጡት ነገር ቢኖር የሙስሊም ማሕበረሰብ ተረጋግቶ ቦታ መያዝ እና ማሕበረሰቡ በውስጡ ለሚገኝበት የአለማመን ሥርኣት ሳይሆን ለዓለም አቀፉ እስላማዊ ኡማ ታማኝነታቸውን እና ቃል ኪዳናቸውን እንዲጠብቁ የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት አስተናጋጅ ማሕበረሰቡን አለማስተናገድ እና እሴቶቹን አለመቀበል ማለት ነው፡፡

በእሳቸው አመለካከት መሰረት የሙስሊም ማሕበረሰብ ስለ ኃይማኖቱ በተለይም ፍፁም አሃዳዊ ስለሆነው የእስልምና *የተውሂድ* አስተምህሮ በሚገባ መማር ያስፈልገዋል፡፡ ትክክለኛ ኢማሞች የሚያገለግሉባቸውን መስጊዶችንም በየቦታው ማቋቋም ግድ ይላቸዋል፡፡ እንደ እስላማዊ ማሕበረሰብ ኑባሬ ማሳያ የአደባባይ ፀሎቶችም በየጊዜው መደረግ እንዳለባቸው አፅንዖት ሰጥተዋል፡፡ ሰባኪዎችን መቅጠር፤ ቤተ መጻሕፍትን እና የጥናት ማዕከላትን መክፈት፤ ለሕፃናት ምቹ የሆኑ ነገሮችን፣ የትምህርት ክፍሎችን እና ለአካባቢው ነዋሪዎች ለየት ያሉ ዝግጅቶችን ማዘጋጀትን የመሳሰሉትን በማድረግ ወደ አስተናጋጅ ማሕበረሰቦች መግባትንም እንደዚሁ፡፡

---

[27] ሼኽ ዶ/ር አብዱል ረህማን ቢን አብዱል ኻሊቅ በ1939 በግብፅ የተወለዱ ሲሆኑ የእስላማዊ ሸሪኣ ፕሮፌሰር እና በተለይም ደግሞ ስለ ታማኝነት እና የሙስሊሞች ቃልኪዳን የሚናገሩ ብዙ መጻሕፍት ደራሲ ናቸው፡፡

[28]

አረብኛን መማር ቅድምያ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በማስከተልም ኻሊቅ የስደተኞች ልጆች ለመፀለይ ብቻ ሳይሆን ከወላጆቻቸው እና ከአያቶቻቸው ሃገራት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራቸው አረብኛን በሚገባ መማር አለባቸው ለሚለው ሐሳብ አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡

በማስከተልም በሙስሊሞች አጀንዳ ላይ ጎልቶ መስፈር ያለበት ነገር ሙስሊሙ ማሕበረሰብ የአስተናጋጁን ማሕበረሰብ ዜግነት ማግኘት እና የሙስሊሙን ማሕበረሰብ ጉዳዮች ለማስከበር በብሔራዊ ምርጫዎች ውስጥ መሳተፍ አለበት የሚለውን የሼኽ አቡበክር ጃቢር አል ጀዚሪን ፈትዋ ይጠቅሳሉ፡፡ የሚያጠቃልሉትም የሙስሊሞች ሙስሊም ወዳልሆኑ ሃገራት መሰደድ እና በተለይም ደግሞ ወደ ምዕራብ የሚደረገው ስደት ቅድመ ጂሃድ እስልምናን አቅም እንዲኖረው ማድረግ እና ማደላደል ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ደግሞ በሙስሊሞች ላይ በሕግ እንደተደነገገ ይናገራሉ፡፡

# *የሂጅራ የ "ምን" ይዘቶች*

## አጭር ዳግም ቅኘነት

"እንዴት" የሚለውን ማለትም ሀራም የሆነውን (የተከለከለውን) ወደ ሀላል (የተፈቀደ እና የታዘዘ) መቀየርን እና የሂጅራን ዓላማዎች እና ግቦች ከጂሃድ እና አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ከማስለም ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተመልክተናል፡፡

በመሐመድ ሕይወት እና በቁርአን ውስጥ በተለያየ ሁኔታ በተቀመጠ መልኩ የተወሰኑ የሂጅራ መሰረቶችን አስተዋውቀናል፡፡ ከውስጣዊ ጂሃድ አተገባበር ጋር የተያያዙትን "አምስቱን ግዴታዎች" የቁርአንን ትዕዛዛት በማገድ "ሸክምን ከማቅለል" (ተይሲር) ጋር እና የግድ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች (ዱሩር0) ጋር አያይዘን ተመልክተናል፡፡

ሂጅራ በእስልምና ውስጥ ዓላማዎች እና ግቦች እንዳሉትም ግልፅ አድርገናል፡፡ እነዚህ ከቁርአን እና ከሱና በመነጨ ሁኔታ መለኮታዊ በሆኑ ሁኔታዎች እና ስልቶች ስር ይንቀሳቀሳሉ፡፡

አሁን ደግሞ የእንቅስቃሴው ዋና አካል ወደሆነ ጉዳይ እናልፋለን፡፡ አዳዲስ የሚመጡ ሰዎችን በውጪ ሃገራት (ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት) ውስጥ ከሚገኘው ነባር ከሆነው የሙስሊም ማሕበረሰብ ጋር ስለሚቀላቀሉበት ሁኔታ የሚናገሩ መርሆችን፣ ዓላማዎችን እና ፕሮግራሞችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህም ማሕበረሰቦች የስደትን ዓላማዎች እና ግቦች ለማሳካት እና አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ለማስለም እንዲሁም እስላማዊ መንግሥትን ለማቋቋም ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ራሳቸውን ነጥለው ይኖራሉ፡፡

እንደ እስላማዊ የህግ አካሄድ ሁለት ተግባራዊ መሆን የሚገባቸው በጣም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት አሉ፡ እነዚህም ***ተምኪን*** እና ***ዒዳድ*** በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህን ቃላት ከማስተዋወቃችን እና ከማብራራታችን በፊት እነዚህ ቃላት ልክ እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን በመነጣጠል ለየብቻቸው ሙሉ በሙሉ ማብራራት ይቸግራል ምክንያቱም እነዚህ እርስ በርሳቸው በጥልቀት የተቆራኙ ስለሆኑ አንዳቸው ያለሌላቸው ሊሰሩ ወይንም ህልውና ሊኖራቸው አይችልምና፡፡

## ተምኪን *ወይንም አቅምን ማጎልበት*

*ተምኪን* ማለት ማበርታት፣ ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ፣ አፅንዖት መስጠት፣ ማስቻል፣ ማደላደል ወይንም አቅም መስጠት (ማስታጠቅ) ማለት ነው፡፡

በሌላ አነጋገር የመጀመርያውን ትውልድ ወይንም ደግሞ በማሕበረሰቡ ውስጥ የተወለደ እና የተራባውን አራተኛ ትውልድ እንዲሁም አዲስ የመጣውን ስደተኛ የሙስሊም ማሕበረሰብን ልባዊ መሰጠት ጥልቀት እንዲኖረው በማደረግ ነው ማለት ነው፡፡ ልባዊ መሰጠታቸውን ማጠናከር እና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ድምፃቸውን የሚያሰሙበትን እና የሚገዙበትን እንዲሁም ሕይወታቸውን የሚመሩበትን የሸሪኣን ህግ ተግባራዊነት እንዲጠይቁ የሚያስችላቸውን እስላማዊ መለያቸውን እንዲያደላድሉ ይረዳቸዋል፡፡ ይህም ደግሞ የሸሪኣ ህግ ነው፡፡ በእስላማዊ አነጋር *ተምኪን* ማለት በአንድ ጉዳይ ላይ ማዘዝ ወይንም በአንድ ጉዳይ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ማግኘት ማለት ነው፡፡

## *ዒዳድ ወይንም ዝግጅት*

ዒዳድ ወይንም ዝግጅት የማንበብ፣ መሳል፣ ማስተካከል እና ቁጥሮችን መጨመር ወይንም ማባዛት ሁለትዮሻዊ ፅንሰ ሐሳብን የያዘ ነው፡፡ ስለዚህ ትርጉሙ “መዘጋጀት እና በተጠንቀቅ መቆም” ማለት ነው፡፡ ቁርአናዊ በሆነ ሁኔታ ስንናገር በወታደራዊ ትጥቅ መዘጋጀት እና በተጠንቀቅ መቆም ማለት ነው ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ዝግጅት ከሌለ በስተቀር *ተምኪን* ምንም ጥቅም የለውምና፣ ጅሃድም ሊታወጅ አይችልምና፡፡

የበለጠ ግላዊ ከሆነው *ከተምኪን* በተለየ ሁኔታ ዒዳድ የበለጠ መዋቅራዊ እና የወል ነው፡፡ የትጥቅ እና የዕዝ ማዕከላት ዝግጅት፣

ሥርአትን የመፍጠር፣ ክህሎትን የማካፈል እና አስፈላጊ ሲሆን ጂሃድን ለማወጅ የተቀናጀ ጥረትን በተለያዩ መረቦች ላይ የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡

ስለ ሁለቱም ፅን ሐሳቦች ማለትም ስለ *ተምኪን* እና ዒዳድ ሊባሉ የሚችሉ ብዙ ነገሮች አሉ ነገር ግን በብዙ ክፍሎች እና ንዑስ ክፍሎች የሚከፈሉ ብዙ ጥልቅ ነገሮቻቸው በቀጥታ ከኛ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያልተገናኙ በመሆናቸው ከያዝነው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ብቻ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ሐሳባዊ የሆነ ዒዳድ እና ተግባራዊ ዒዳድ አለ፡፡ ተግባራዊ ዒዳድ የአንድን ተልዕኮ  የተወሰነ ገፅታ የሚያመቻች አስፈላጊ የሆነ ዝግጅት እና ስልጠና ነው፡፡

## የተምኪን *(የማስታጠቅ) አስፈላጊ የሆኑ መልኮች*

*የተምኪን* ስልታዊ አካሄዶች ብዙ ናቸው፡፡ አሁን በሁለት መልኮች ላይ እናተኩራለን፡

1. ውስጣዊ *ተምኪን* ወይንም በሙስሊም ማሕበረሰብ መካከል የማረጋጋት ሥራ፡፡
2. ከሙስሊሞች እና ሙስሊም ካልሆኑት ጋር ውጫዊ *ተምኪን፡፡*

መጀመርያ ውስጣዊ ማረጋጋት፡ እስላማዊ በሆነ ሁኔታ ስንናገር የማጠናከሩ ሂደት ዝግ ያለ እና ጊዜ የሚፈጅ ቢሆንም ነገር ግን

በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሙስሊሞችን እና መሪዎቻቸውን በሥራ እንዲወጠሩም የሚያደርግ ነው፡፡

በእስልምና ውስጥ ጠልቆ መግባት አስተምሕሯዊ እና የአንድን ሰው ኃይማኖታዊ ልምምድ እና እምነት ማደላደል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ ሂደት "ወግ አጥባቂ በሆነ አመለካከት ማጥመቅ" ተብሎ የበለጠ ሊገለፅ ይችላል፡፡ መጀመርያ አካባቢ ላይ ይህ ውስጥ ለውስጥ በዝምታ የሚፈፀም ነው፡፡

ይህ እንግዲህ አንድ ሰው ቀደም ሲል የሚያውቀውን ነገር ድምፅ ሳያሰሙ የመመስረት ወይንም ደግሞ የማደላደል ቀዳሚው እርምጃ ነው፡፡ *የተምኪን* መሰረቶች በያንዳንዱ እስላማዊ ጓዳ ጎድጓዳ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ይህም ከመስጊድ ጀምሮ እስከ *መድረሳ፣* እስላማዊ የባሕል ማዕከላት፣ እስላማዊ ትምሕርት ቤቶች፣ የሙስሊም ወጣት ክበቦች፣ የእስላማዊ *ዳዐዋ* ወይንም ሚስዮን ማዕከላት እና በሁሉም ዓይነት እስላማዊ የመገናኛ ብዙኃን ውስጥ፣ ወዘተ. ይገኛሉ፡፡

ትልቁ ዓላማ ነባር የሆነውን የሙስሊም ማሕበረሰብ ማደላደል እና ሙስሊም መሆናቸው የታወቀ እና እስላማዊ ማንነታቸውን በኩራት ከጥቃት እንዲከላከሉ ማስቻል ነው፡፡

*ተሚኪን* የሚለው ቃል በራሱ ከቁርአን የተገኘ ሲሆን ወደ አማርኛ ሲተረጎምም "ማስመቸት" ተብሏል፡

ሱራ 18፡84 “እኛ ለእርሱ በምድር አስመቸነው፡፡ ከነገሩም ሁሉ (መዳረሻ) መንገድን ሰጠነው፡፡”

ሱራ 7፡10 “በምድርም ላይ በእርግጥ አስመቸናችሁ፡፡ በእርሷም ላይ ለናንተ መኖሪያዎችን አደረግንላችሁ፤ ምስጋናችሁ በጣም ጥቂት ነው፡፡”

ሱራ 12፡56 “እንደዚሁም ለዩሱፍ በምድር ላይ ከእርሷ በፈለገው ስፍራ የሚሰፍር ሲሆን አስመቸነው፡፡ በችሮታችን የምንሻውን ሰው እንለያለን፡፡ የበጎ ሠሪዎችንም ዋጋ አናጠፋም፡፡”

ሱራ 28፡6 “ለእነርሱም በምድር ላይ ልናስመች ፈርዖንንና ሃማንንም ሰራዊቶቻቸውንም ከእነሱ ይፈሩት የነበሩትን ነገር ልናሳያቸው (እንሻለን)፡፡”

ሱራ 22፡41 “(እነርሱም) እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቸው ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፣ ዘካንም የሚሰጡ፣ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፣ ከመጥፎ ነገርም የሚከለክሉ ናቸው፡፡ የነገሮቹም ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ነው፡፡”

ዐሰላቢ[29] እና አል ሻሄሪን[30] የመሳሰሉ ዕውቅ እስላማዊ ሊቃውንት በዚህ ጉዳይ ላይ በሰፊው ጽፈዋል፡፡

29 http://www.islamtoday.net/articles/show_articles_content.cfm?id=177&catid=191&artid=7135 በሊብያ የተወለዱ ሲሆን በተምኪን እና

በእርግጥ *ሂጅራ* (ስደት) እስላማዊ ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ ወደ *ተምኪን፣* መጠናከር እና መደላደል የሚመራ የመጀመርያው እርምጃ ነው፡፡ የተሰደደውን የአብርሃምን ምሳሌ ብንጠቅስ፡

> ሱራ 29፡26 "ሉጥም ለእርሱ አመነ፤ (ኢብራሂም) «እኔ ወደ ጌታዬ ተሰዳጅ ነኝ፡፡ እነሆ እርሱ አሸናፊው ጥበበኛው ነውና» አለም፡፡"

መሐመድ እና ተከታዮቹ ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ እርሱን በማረጋጋት እና አቅምን በመስጠት ረገድ ሂጅራ በጣም ወሳኝ ነበር፡፡

አል ሻሃሪ ይህንን ጉዳይ (عوامل النصر والتمكين في دعوات المرسلين)*በመልዕክተኞች የማደላደል (የተምኪን) ጥሪ ውስጥ የሚገኙ የድል ፍሬ ነገሮች* በሚል ርዕስ በጻፉት *መጽሐፋቸው* ጠለቅ ባለ ሁኔታ ተንትነዋል፡፡

በሌላ አነጋገር አስተምሕሯዊ ዝግጅት የሆነው ውስጣዊ የሆነ መሰጠት እና አስተናጋጁ ማሕበረሰብ ክፉ እና ፀረ እስልምና ነው የሚለውን እምነት ማስተላለፍ ክፉውን ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ውስጥ የማስወገድን ኃላፊነት የሚሸከም ራሱን የነጠለ እና የለየ የሙስሊም ማሕበረሰብ ወደ መፍጠር ይመራል፡፡ የእንዲህ ዓይነቱን ማሕበረሰብ መፈጠርም አስፈላጊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

---

እስላማዊ ሕግ በ1999 ዓ.ም. ዶክትሬታቸውን ከኡምዱርማን ዩኒቨርሲቲ ወስደዋል፡፡ ስለ *ተምኪን* እና የመሐመድ ጓደኞች ሲራ በርካታ መጽሐፍቶችን ጽፈዋል፡፡

[30] http://mahawer.al-islam.com/dawaBooks/078.doc

እንደ አላህ ወታደሮች የአላህ ጠላቶች ተወግደው ወይንም ደግሞ ተሸንፈው ማየት የሙስሊሞች ኃላፊነት ነው፡፡ ይህም ደግሞ የሚጀመረው እስልምናን እና “አረማዊ” የሆነውን ሥርኣቱን በሚቃወሙ በአቅራብያ በሚገኙ ሰዎች ይሆናል፡፡ በሱራ 9፡123 ላይ በተጻፈው መሰረት በአቅራቢያ የሚገኘው አካባቢ ንቁ የሆነውን እስላማዊ ቡድን ወይንም ደግሞ የአካባቢውን ሴል የአላህ ጠላቶች ተሸንፈው ለማየት ግድ እንዲላቸው ያደርጋል፡፡

> “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች ተዋጉ፡፡ ከእናንተም ብርታትን ያግኙ፡፡ አላህም ከሚጠነቀቁት ጋር መኾኑን ዕወቁ፡፡”

እነዚህ የግድ መወገድ አለባቸው፡፡ በካዮች ከሆኑት ከአላህ ጠላቶች ምድርን ማፅዳት ደግሞ የአላህ ታማኝ ወታደሮች ግዴታ ነው፡፡ ስለዚህ በግልፅ እንደሚታየው ያ አስተምህሯዊ ልፈፋ አንዴ ከተሳካ በኋላ ነውጠኛ የሆነው ቁሳዊው ጂሃድ መደምደምያው ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይዘግይም ይፍጠንም ትክክለኛዎቹ ቡድኖች እና ትክክለኛው አወቃቀር እስካሉ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በሂጅራ (ስደት) በኩል የሚደረገው የማደላደል ወይንም አቅምን የመስጠት ፅንሰ ሐሳብ ዝም ብሎ ብቻ የአንድን ሰው ምሳሌነት መከተል ማለትም መሐመድን እንደ ነቢይ መከተል ማለት አይደለም ነገር ግን በሱራ 24፡55 ላይ እንደተጠቀሰው አላህ

ለሙስሊሞች ድልን እና በምድር ላይ መደላደልን እንደሚሰጣቸው ቃል በመግባት የሰጠው ትዕዛዝ ነው፡፡

> “አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ለይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፡፡ በእኔ ምንንም የማያጋሩ ኾነው ይግገዙኛል፡፡ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው እነዚያ እነርሱ አመጸኞች ናቸው፡፡”

ባመኑ ሰዎች “መልካም” የመስራትን ፅንሰ ሐሳብን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ያ “መልካም” ነገር ድሆችን እና አቅመ ደካሞችን መርዳት ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ የላቀ ነው፡፡ “መልካም” የተባለው ነገር ግብ ለእነርሱ የተመረጠላቸውን እና በሱራ 3፡19 መሰረት “በአላህ ፊት የተወደደ ኃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው” የተባለለትን የአላህን ኃይማኖት ማስፋፋት ነው፡፡ ሌላ ምንም ዓይነት ኃይማኖትም ሆነ ሥርኣት በአላህ ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ በሱራ 3፡85 ላይ በተጻፈው መሰረት በምድርም ላይ ሆነ በሚመጣው ዓለም አይቀበላቸውም፡፡

> “ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡”

የአላህን ኃይማኖት ማስፋፋት የሙስሊሞች ግዴታ ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ የዚህን ኃይማኖት መጠናከር ማየት የሁሉም ሙስሊም አማኞች ግዴታ ነው፤ ስደተኞችም ይሁኑ ነዋሪዎች፣ አዲስ መጪዎችም ይሁኑ በአራተኛ ትውልድ ላይ የሚገኙ፣ ከሚኖሩበት ማሕበረሰብ ከተለየ ጎሳ ቢሆኑ ወይንም ደግሞ ከነባሩ ማሕበረሰብ አዲስ የሰለሙ እንኳ ቢሆኑ ማለት ነው፡፡

## *ውጭያዊ ተምኪን ወይንም በሙስሊሞች እና ሙስሊም ባልሆኑት ዘንድ እስልምናን ማደላደል*

ይህ ዓይነቱ *ተምኪን* ሙስሊም ባልሆኑት ሰዎች ላይ ሲተገበር በጣም አደገኛ ከሆኑ ሥልታዊ አካሄዶች መካከል አንዱ ይሆናል፡፡ ይህ መርህ *ተዐሊፍ አል ቁሉብ* ወይንም ደግሞ “የልቦች እርቅ” በመባል ይታወቃል፡፡ በሌላ አነጋገር ለእስልምና እና ለሙስሊሞች ጥሩ የሆነ ልብ እንዲኖራቸው በማድረግ ሙስሊም ባልሆኑት ዘንድ ጥሩ ቦታን የማግኘት አካሄድ ነው፡፡ ይህ በመሐመድ እና በተከታዮቹ ሲተገበር የነበረ እና አሁን እንኳ እየተተገበረ የሚገኝ ቁርአናዊ አስተምህሮ ነው፡፡ በሱራ 9፡60 ላይ ይገኛል፡

> “ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በእስልምና)

> ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሠሩ፣ በመንገደኛም ብቻ ነው፡፡ ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡"

ጠበሪ ይህንን ጥቅስ ሲያብራራ አዲስ የሰለመ ሰው የአላህን ነቢይ ሲቀበል ኃይማኖታዊ ታክስ ከሆነው *ከሰደቃ* ብዙ ክፍል ይሰጠዋል በማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ይህ "መልካም የሆነ ኃይማኖታዊ ልምምድ ነው፡፡"

የእስልምናን ጠላቶች ልብ ለማለዘብ በጥሬ ገንዘብም ሆነ በመልክ የሚደረግ ክፍያ ትንታኔ ያለ ልዩነት በሁሉም እስላማዊ የህግ አካሄዶች መመርያዎች[31] ውስጥ ይገኛል፡፡

*በዘካት* ላይ ግንባር ቀደም የህግ ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር ጋዚ አነያት[32] እንደተናገሩት "ልቦችን ማስታረቅ" ሰዎችን ወደ እስልምና ለመሳብ የሚጠቅም *የዳዕዋ* ዓይነት ነው፡፡ ይህ የጋዚ አመለካከት ይህ "ልቦችን የማስታረቅ" ልምምድ ከእስልምና መስፋፋት ሊነጠል የማይችል ነገር ግን ሙስሊም ያልሆኑትን ድል ለመንሳት ጠንካራ

[31] አል አህቃም አል ሱልጣንያ አል ማሩዲ ገፅ 123፤ አል አህቃም አል ሱልጣንያ አል ፋረዐ ገፅ 132፤ ረውደናት ዐታሊቢን አል ነዋዊ ቅፅ 2 ገፅ 313፤ ዐተሺል ኢብን ጆውዚያ አል ግሀረኒቲ ቅፅ 2 ገፅ 78፤ ተፍሲር ኢብን ከሢር ቅፅ 2 ገፅ 365፤ ፊቅህ አል ዘካት አል ቃርዳዊ ቅፅ 2 ገፅ 603፤ ሙቀዊማት አል ኢቅቲሳድ አል ኢስላሚ አብዱል አልሰሚ አል መስሪ 140፤ ተፍሲር አል ሙኒር ቅፅ 10 ገፅ 270፤ ተፍሲር አል ታባሪ ቅፅ 4 ገፅ 313፤ ፈት አል ቀዲር አል ሸውካኒ ቅፅ 2 ገፅ 374፤ አል ዘካት ፊ አል መሰሊህ አል ዐማ ዶ/ር ፋሪስ ገፅ 31፤ አል ካት አል ጆማሚ ገጽ 72

[32] ኢስተክህዳም አል ዋዛፊ ሊ አል ዘካት ዶ/ር ጋዚ አነያት ገፅ 48፣ 68-69

የሆነ ስልት መሆኑን በተናገሩ ሙስሊም ሊቃውንት ድጋፍ ተችሮታል፡፡[33]

ስለዚህ ልቦችን ማስታረቅ ግለሰቦችን "ለመማረክ" በሁሉም ዘርፎች የሚገኙትን እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ የገንዘብ ድጎማ፣ ደህንነት፣ መገናኛ ብዙኃን፣ ኢኮኖሚ እና ፖለቲካን የመሳሰሉ ተቋማትን ሁሉ ሰርጎ ለመግባት ህጋዊ ፍቃድ የሚሰጥ እስላማዊ መርህ ነው፡፡

ዶ/ር አነያት በመጽሐፋቸው ውስጥ በግልፅ እንዳሰፈሩት[34] ከእስላማዊ *ዘካት* ሙስሊም ላልሆኑት የሚሰጥ ክፍያ "ልቦችን በማስታረቅ" መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እስልምናን በመጥፎ ብርሃን የሚያሳዩ ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች  በእስልምና ላይ የሚሰነዘሩ  የትችት ድምፆችን እና የተቃውሞ ብዕሮቻቸውን ዝም የማስባያ መንገድ ነው፡፡ ይህንንም በመከወን እነዚህኑ ድምፆች እና ብዕሮች ለእስልምና አፍ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የበለጠ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት በማግኘት ሊፈፀም ይገባል የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡ በጥቅሉ ጋዜጠኞች ስለ እስልምና ቀና በሆነ ልቦና እንዲዘግቡ ይፈልጋሉ ማለት ነው፡፡

ተመሳሳይ የሆነ ስልት በሼኽ ዶ/ር ሙስጠፋ አል ዘርቃ ተነድፏል፡፡[35] እርሱ እንደጻፈው ከሆነ ባለፉት ዘመናት የክፍያ

[33] http://web.macam.ac.il/~tawfieq/moallafa-2.htm
[34] ኢስተክህዳም አል ዋዛፊ ሊ አል ዘካት ዶ/ር ጋዚ አነያት ገፅ 48፣ 68-69
[35] አሁን በሕይወት የሌሉት ዶ/ር ዘርቃ የዘመናችን ታዋቂ የሀንበሊ ፊቅህ ሊቅ ነበሩ፡፡ አል ሙድክሀል አል ፊቅሂ አል ዐኣም ሙስጠፋ አህመድ አል ዘርቃ ቅፅ 1 ገፅ 160

ተቀባዮች የጎሳ መሪዎች የነበሩ ሲሆኑ አሁን ደግሞ የጋዜጣ አዘጋጆች መሆን ያስፈልጋቸዋል፡፡ እስልምናን የሚያቀነቅኑ የአዳዲስ መጽሔቶች ህትመቶችን ማቋቋም ወይንም ልዩ የሆነ የመገናኛ ብዙኃንን ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የመገናኛ ብዙኃንን ዘመቻ ለእስልምና ድጋፍ መጠቀምን በተመለከተ ሼኽ ሰዒድ አል ሐዊ[36] ከዶ/ር ዘርቃ ጋር ይስማማሉ፡፡ ዶ/ር አቡ ፋሪስ[37] ደግሞ እንደ ተናገሩት ልቦችን ማስታረቅ ከእስላማዊ ሸሪአ ዘላለማዊ ተኣምራት መካከል አንዱ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረግ እና ጥቅም ላይ መዋል ያስፈልገዋል፡፡ ሰዒድ አል ሐዊ[38] ፖለቲኞች አድሎ ሊደረግላቸው ይገባል በማለት ጉዳዩን አስፍተውታል፡፡ በሌላ አነጋገር ፖለቲከኞች ለእስልምና እና ለሙስሞች ልባቸው የተከፈተ ይሆን ዘንድ የዚህ ስጦታ ተካፋዮች መሆን አለባቸው፡፡

ግብፃዊ አጥኚ የሆኑት ኢብራሂም አል-ቀብቲ እንደተናገሩት ባለፉት አሥርተ ዓመታት ሙስሊም አቀንቃኞች እስልምናን ፖለቲካዊ እና ንፅረተ ዓለማዊ ኃይል እንዲሁም የአብዛኛው ሰው ኃይማኖት ለማድረግ ጥረታቸውን በቀጠሉ ቁጥር የአውሮፓ ማሕበራዊ ገፅታ ተቀይሯል፡፡ ይህ የሆነው በሰው ቁጥር መጨመር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ወደ አውሮፓ ማሕበራዊ፣ ሲቪል፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ

[36] ከ20 በላይ የሸሪአ መጻሕፍትን የጻፉ ተዋቂ ደራሲ ሲሆኑ በሺአ ሊቃውንት ዘንድ የታወቁ እና የተከበሩ ናቸው፡፡ የሦርያ ተወላጅ ሲሆኑ በዮርዳኖስ ውስጥ ነበር የሞቱት፡፡ አል ኢስላም ሰዒድ አል ሐዊ ቅፅ 1 ገፅ 124

[37] ኢንፋቅ አል ዘካት ፊ አል መስሊህ አል ኣዕመ ዶ/ር አቡ ፋሪስ ገፅ 35-36

[38] http://web.macam.ac.il/~tawfieq/moallafa-2.htm

ተቋማት ሰርጎ በመግባትም ጭምር ነው፡፡ ይህ እቅድ ደግሞ በ1980 ዓ.ም. በአውሮፓ እስላማዊ ምክር ቤት ይፋ መደረጉን አክለው ይገልፃሉ፡፡ ይህ ስልት *እሰላማዊ ማሕበረሰቦች ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ* በሚል ርዕስ በታተመ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ ሙስሊሞች እንደ ተነጠሉ ማሕበረሰቦች በመኖር አውሮፓውያን የማሕበረሰቦቹን ማሕበራዊ እና ኃይማኖታዊ ፍላጎቶች እንዲሞሉ እንዲጠይቁ ይመከራል፡፡ ይህንንም በማድረግ ሙስሊሞች ኃይማኖታዊ እና ህጋዊ ማዕከላት የተሟሉላቸውን እስላማዊ ማህበረሰቦች ክፍልፋዮች ይመሰርታሉ፡፡ ከአውሮፓውያን ማሕበረሰቦች ጋር ስብጥር እንዳይፈጥሩ ያደርጋሉ ነገር ግን እስልምናን ለማስፋፋት ሙስሊም ካልሆኑት ጋር በቂ መስተጋብር ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ደግሞ አስተናጋጁን ማሕበረሰብ እስልምና የበላይ ወደሚሆንበት እስላማዊ ማሕበረሰብ የመለወጥን ዋና ግብ ለመምታት ይቻል ዘንድ በሙስሊሞች ሁሉ ላይ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡

በዩኬ ውስጥ በሚገኘው ኢስላሚክ ፋውንዴሽን ተመሳሳይ የሆነ ስልት ይፋ ሆኗል፡ *በምዕራብ ውስጥ ያለው እሰላማዊ እንቅስቃሴ* በሚል ርዕስ አሁን በሕይወት በሌሉት በኩራም ሙራድ የተጻፈው መጽሐፍ ለእስላማዊ ወረራ እንደ መሰረተ ሐሳብ እያገለገለ ይገኛል፡፡ አንድ ሰው ለዘብተኞቹ ይህንን ጉዳይ እንዴት እንደሚያዩት ይጠይቅ ይሆናል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች አውሮፓን

በማስለም ዕቅድ ረገድ ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ፡፡ ብቸኛ ልዩነታቸው የነበረው እና ሆኖ የሚቀጥለው ሙስሊሞች ምን ያህል በፍጥነት ወይንም በዝግታ መሄድ እንደሚገባቸው በሚወስነው የልቦች እርቅ አካሄድ ላይ እና ሙስሊሞች ነውጠኛ ጂሃድን መጠቀም እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው እንዲሁም አካሄዱ ምን ያህል ውጤታማ ነው የሚለው ነው፡፡

የዚህ ስልት ተግባራዊነት በዩኬ፣ ስዊድን፣ ፊንላንድ፣ ሆላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ እስፔን፣ ጣልያን፣ ቤልጂየም እና አውስትራልያ ውስጥ እየሆነ ያለውን ነገር ስንመለከት ግልፅ ይሆንልናል፡፡ ይህም ሀርቫርድን የመሳሰሉ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች እና የኢቪ ሊጎች[39] እንዲሁም ሌሎች[40] እንዴት በእስላማዊ ሰርጎ ገብነት እንደተሞሉ በሚገልፀው የሻኪር ዐ'ነቢሊሲ መጣጥፍ በሚገባ ተመልክቷል፡፡ በሰዑዲ አረብያ እና በተባበሩት የአረብ ኤምሬቶች የገንዘብ ድጋፍ የተሰሩ ትልልቅ መስጊዶችን፣ እስላማዊ አካባቢዎችን እስላማዊ ካልሆኑ ተፅዕኖዎች መከላከል በሚል ስም በአብያተ ክርስቲያናት እና በአገልጋዮቻቸው ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እየተመለከትን ነው፡፡ ሐላል ሥጋ በትምህርት ቤቶች፣ በወኅኒ ቤቶች፣ በሆስፒታሎች እና በሕዝብ መገበያያ ቦታዎች ልክ እንደ ሂጃብ፣ የአደባባይ ፀሎቶች፣ ግዙፍ የሆነው የገንዘብ ፍሰት[41] የሸሪኣ

[39] http://www.alarabiya.net/views/2008/06/25/52060.html
[40] http://www.meforum.org/article/883
[41] http://www.alaswaq.net/articles/2007/09/09/10655.html

ተግባራዊነት እና የብሪቲሽ መንግሥት ለነዚህ ፍርድ ቤቶች እውቅና መስጠት ሁሉ የተለመደ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ እድገቶች የላቁ *የተምኪን* ውጤቶች ናቸው፡፡ በዩኬ ውስጥ የሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን በተለይም ቢቢሲ እና በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙት የመገናኛ ብዙኃን ለእስልምና ክፍት መሆናቸው "በልቦች መታረቅ" ላይ ከተመሰረተው *የተምኪን* አካሄድ መርሆች የተነሳ ነው፡፡

በጣም ግራ በሚያጋባ ሁኔታ  ሙስሊሞች ሁል ጊዜ ክርስቲያኖችን ከእስልምና ተመላሾችን በገንዘብ ይገዛሉ በማለት ይከሷቸዋል ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዲህ ዓይነት አስተምህሮ የትም አይገኝም፡፡

## *ዒዳድ (ዝግጅት)*

ዒዳድ ወይንም ዝግጅት ከትጥቅ በተለይም ደግሞ ከወታደራዊ ትጥቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ነገር ግን በቁርአናዊ መሰረቶቹ ላይ ብርሃን ከመፈንጠቃችን በፊት በዚህ የማስታጠቅ ሂደት ውስጥ ያለውን ቦታ እና አስፈላጊነት እናብራራ፡፡

ይህ የዝግጅት ሂደት ትክክለኛው ዝግጅት የሚከወንባቸውን አወቃቀሮች ይሻል፡፡ ዝግጅት ቀለል ካለው ደረጃ እጅግ እስከ ተወሳሰበው ደረጃ ሊሄድ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙስሊሞች ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ፣ የከበቧቸውን ጉዳዮች እና ለእስላማዊ ግዴታዎቻቸው ምን ያህል ታማኞች እንደሆኑ ማወቅ የዒዳድ አካል ነው፡፡

የዝግጅት ሂደቱ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን ይችላል፡፡ ሙስሊሞች በጣም ወሳኝ የሆነውን ተልዕኮ እንዲፈፅሙ ከመላካቸው በፊት ሁሉም ዓይነት ድጋፎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙስሊሞች የተባበረ ድምፅ በማሰማት እስላማዊ ፍላጎቶቻቸውን ያሟሉ ዘንድ ባለ ሥልጣናትን የሚጠይቁበትን መንገድ ማወቅ የዲዳድ ዓይነት ነው፡፡ የዝግጅት ሂደቱ በሙስሊም ማሕበረሰብ መካከል በሚቀርብበት እና ሥራ ላይ በሚውልበት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል፡፡ ባለሥልጣናትን ከማሳመን ጀምሮ እንዲፈሩ እስከማድረግ ድረስ ባለው አሰራር ሙሉ በሙሉ ሊለያይ ይችላል፡፡

የዝግጅት ሂደቱ ነገሮችን የማብራራት ችሎታ ባላቸው ምሑራን የሚመራ ስርኣት መመስረትን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አስተምህሮዎችን በሚገባ የማብራራት እና በተለይም ደግሞ አድማጮቻቸውን በሚያራምዱት አስተሳሰብ የማጥመቅ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚችሉ የአካባቢው ምሑራን ካልተገኙ ደግሞ ድንበር ዘለል ምሑራን ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

የዝግጅት ሂደቱ ከአካባቢው ማሕበረሰቦች ጋር የግንኙነት መስመሮችን በማበጀት በአካባቢው አስተናጋጅ ማሕበረሰብ ዘንድ ታማኝነት ማግኘትን ይጠይቃል ይህም የሚደረገው ደግሞ ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ ጥብቅና እንዲቆሙ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህ የግንኙነት መስመሮች ሙስሊም ማሕበረሰብ በአስተናጋጁ

ማሕበረሰብ መካከል ህልውናው እንዲቀጥል የሚያስችሉ ቁልፎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙስሊሙ ማሕበረሰብ እንደ ውለታ ምላሽ ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ድምፅ ለመስጠት በጋራ ቃል ይገባል፡፡ የሙስሊሙ ማሕበረሰብ መሪ አባላቱን አስቤዛቸውን ከአንድ ቦታ ብቻ እንዲገዙ በማዘዝ የንግድ ሰፈሩ ህልውና በሙስሊም ማሕበረሰብ ላይ የተንጠለጠለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በግልፅ እንደሚታየው እነዚህ የግንኙነት መስመሮች የገንዘብ፣ የፖለቲካ ወይንም ደግሞ ጥሩ መደላድል ለማግኘት የሚያስፈልጉ ምንም ዓይነት አቅርቦቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ይህ በሚገባ የታሰበበትን ውዥንብር በአስተናጋጁ ማሕበረሰብ መካከል በመፍጠር ከእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙትን በጎ ምላሾች ዋስትና ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡ በአምስተርዳም ከተማ ጥቃት ተፈፀመ ብንል በሮተርዳም ከተማ ውስጥ የሚገኙት “አዎን በአምስተርዳም ውስጥ ጥቃት መፈፀሙን እናውቃለን ነገር ግን እዚህ በሮተርዳም የሚገኙ ሙስሊሞች በጣም ሰላማዊና ጥሩ ወዳጆች ናቸው” በማለት ይናገራሉ፡፡ ይህ ብዙኃኑን ሕዝብ ግራ በማጋባት ምንም እርምጃ እንዳይወስዱ ወይንም ደግሞ ቸልተኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ የመጨረሻው ውጤት ወይንም ደግሞ አጠቃላይ የሆነው ድምዳሜ ምናልባት ጥቂት መስመር የሳቱ ሙስሊሞች ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን እዚህ በሮተርዳም ውስጥ የሚገኙቱ ሰላማውያን ናቸው የሚል ነው፡፡

የዝግጅት ሂደቱ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ሰዎችን እና ሰርጎ ለመግባት የሚያስችሉ መንገዶችን ይፈልጋል ነገር ግን ከዚያ በላይ ለሰልፍ አደባባይ የሚያስወጣ ምክንያት ወይንም ደግሞ ትኩረት ለመሳብ የሚያስችሉ ጉዳዮችን መፍጠርን ይፈልጋል፡፡ ትኩረት የሚደረገው በአንዳንድ ሙብቶች ክልከላዎች ወይን ደግሞ ስህተቶችን በማስተካከል ላይ ነው ነገር ግን ለበለጠ የማስለም ሂደት እና ሙስሊም ያልሆነው ማሕበረሰብ እና ባለ ሥልጣናት እጅ እንዲሰጡ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ መንገድን ይጠረጋል፡፡ በዚህም ሳብያ አካባቢያዊ ጉዳዮች ሃገራዊ እንዲሆኑ እና ሃገራዊ ጉዳዮች ደግሞ ዓለም አቀፋዊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ነገር ግን ይህንን ሁሉ ግብ ለመምታት እና በአባልነት የሚመዘገቡ ሰዎችን ለማግኘት ስደት የግድ መኖር አለበት፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ዓይነት ስደት ሳይሆን የሙስሊም ስደት ነው ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት ዝግጅቶች እና ፍልሚያዎች በቀጥታ የተገናኙት ከስደት ጋር ነውና፡፡ ያለ ስደት ጠላትን ለማስረግ የሚቻልበት መንገድ አይኖርም፡፡ የእስልምናን ኃይማኖት ንፅህና እና የበላይ የሆነውን ሥርአቱን ሳይረዱ የጠላትን መሰረት ለመናድ እና ለመበታተን አይቻልም፡፡

ይህ የዝግጅት ፅንሰ ሐሳብ ቁርአናዊ ድንጋጌ ሲሆን በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ አላህ በግልፅ የመናገር ኃላፊነቱን በመውሰድ

ከጥቂት መመርዎች ጋር በቁርአን ውስጥ አስፍሮታል፡፡ መጀመርያ እስቲ ሱራ 8፡60 ላይ የሚገኘውን ቁርአናዊ ጥቅስ እንመልከት፡

> “እነዚያም በኋላ ያመኑና የተሰደዱ፣ ከእናንተም ጋር ኾነው የታገሉ እነዚያ ከናንተው ናቸው፡፡ የዝምድናዎች ባለቤቶችም በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው በከፊሉ (መውረስ) የተገቡ ናቸው፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡”

ግንባር ቀደም እስላማዊ ሊቅ እና የሰዑዲ አረብያ ዋና ሙፍቲ የሆኑት ሼኽ ኢብን ባዝ[42] የዝግጅትን ፅንሰ ሐሳብ ሲያብራሩ እንደተናገሩት  ዝግጅት ምስጢሩ ውስጣዊ ሲሆን ክብደት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ስለዚህ በሁሉም ዓይነት መሳርያዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡ ዝግጅቱም የልብ ወይንም የአዕምሮ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዊ ነው፡፡ በማስከተልም አንድ ሰው በመከላከል ወይንም ደግሞ በማጥቃት ጂሃድ ውስጥ ይሳተፍ እንደሆን ስለማያውቅ ከሁሉም ዓይነት የጦር መሳርያዎች ጋር መተዋወቅ አለበት ብለዋል፡፡ ምን ዓይነት መሳርያዎች - የምድር፣ የባሕር ወይንም የአየር መሳርያዎች ያስፈልጉ ይሆን? አንድ ሰው በሚገባ መዘጋጀት ያስፈልገዋል ነገር ግን ምንም እንደሌለው በማስመሰል በሌሎች ዘንድ መታየት አለበት፡፡ ስለ ጉዳዩ  የኢታላይነት ባሕርይ ማሳየት አለበት ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ እንዲህ ብለዋልና፡

---

42 http://www.binbaz.org.sa/index.php?pg=mat&type=article&id=528

“ጦርነት አታላይነት ነው፡፡” ባዝ በማስከተልም እንደተናገሩት ብዙ ውጊያዎች በመሳርያ የበላይነት ድል አልተነሱም ነገር ግን በአታላይነት ስልቶች ጠላትን ግራ ለማጋባት ብዙ ክህሎትን በሚፈልገው ማታለል ነው፡፡

ዒዳድ መሳርያን መያዝ እና መጠቀም መቻል ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ዶ/ር ዐሊ መሐመድ አል ሰላቢ[43] ከሆነ ዒዳድ በንዑሳን ክፍሎች የሚከፋፈል ሲሆን ቀስ በቀስ የሚያድግ ሂደት ነው፡፡ በማስከተልም የሰርጎ ገብነትን፣ በራስ መተማመንን የማግኘትን እና የእስልምናን ተቃዋሚዎች ለማዳከም የሚደረግ ሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን ያብራራሉ፡፡[44]

እንዲሁም አል ሸሃሪ[45] እንዳብራሩት የዒዳድ ተምኪን በአንድ ጀምበር የማይሳካ እና ነገር ግን የተወሰነለት ሂደት ያለው ነው፡፡ ሂደቱ ከመሰረታዊው እስከ ከፍተኛው ድረስ እርሳቸው *የተምኪን* ደረጃዎች በማለት በሚጠሩት ሁኔታ አንዱ በሌላው ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሚገባው ለአንባቢዎቻቸው ግልፅ አድርገዋል፡፡[46]

---

43 ተብሲር አል ሙዕምኒን ቢ ፊቅህ ዐነሴር ዋ አል ተምኪን ፊ ቁርአን አል ከሪም

44 http://www.islamtoday.net/articles/show_articles_content.cfm?id=177&catid=191&artid=7135

45 አወሚል ዐነሲር ዋ አል ተምኪን ፊ ዳዋት አል ሙርሰሊን

46 http://mahawer.al-islam.com/dawaBooks/078.doc

የዒዳድ በጣም ወሳኙ ቅድመ ሁኔታ የቁጥሮች መጠን ወይንም ማባዛት ነው፡፡

ዒዳድ የመጣው ዐዳድ ከሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም "መቁጠር" ማለት ነው፡፡ ሙስሊም ሊቃውንት ይሄንን ቁጥራቸውን መጨመር መሆኑን እንደሚያመለክት ይናገራሉ፡፡ ቁጥራቸው በጨመረ ቁጥር የመፅናት እና ተፅዕኖ በማሳደር ሁሉንም ነገር የመቆጣጠር ዕድላቸውም ከፍ ይላል፡፡ ከስደት እና ከጂሃድ ጋር የተቀናጀው ይህ የማብቃት እና የዝግጅት አጠቃላይ ሁኔታ አንድ የቱርክ ጋዜጠኛ ከጀርመን ጋዜጣ ጋር ቃለ መጠይቅ ባደረገበት ወቅት በግልፅ ተነግሯል፡[47] "እናንተ ጀርመኖች እኛ ቱርኮች ወደ ሃገራችሁ የምንመጣው ሥራ ፍለጋ እና የገንዘባችሁን ሽርፍራፊ ፍለጋ ይመስላችኋል፡፡ አይደለም፣ እኛ ወደዚህ የምንመጣው ሃገራችሁን በመውሰድ በውስጧ በመደላደል ከዚያም ትክክል መስሎ የታየንን ማድረግ ነው፡፡ ይህንን የምናደርገው ደግሞ በእናንተው ይሁንታ እና በራሳችሁ ሕግ በመጠቀም ነው፡፡"

ይህ የሙስሊሞች ቁጥር መጨመር በአሁኑ ጊዜ በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ የተለመደ ሆኗል፡፡ የሕዝብ ቆጠራ እንደሚያሳየው ነባር የሆኑ ሕዝቦች የወሊድ መጠናቸውን ከፍ ካላደረጉ በስተቀር በሃያ ዓመታት ውስጥ በአብዛኞቹ የምዕራብ አውሮፓ ሃገራት ውስጥ ሙስሊሞች አብላጫውን የሕዝብ ቁጥር ይይዛሉ፡፡ ይህ የመዋለድ

[47] http://www.elaph.com/ElaphWriter/2004/11/23948.htm

ጉዳይ ሳይሆን ነገር ግን በዒዳድ አስተምህሮ የተደነገገ ግልፅ ዕቅድ ነው፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ የሙስሊሞች መድብለ ጋብቻ በአውሮፓውያን መንግሥታት ዘንድ ዕውቅናን ማግኘቱ የቁጥራቸው በፍጥነት መጨመር ከማናቸውም ምክንያታዊ ስሌቶች ያለፈ ነው ያስብላል፡፡

## ተምኪን እና ግቦቹ

*ተምኪን* የተለያዩ መልኮች ያሉት ቢሆንም ነገር ግን አንድ ዓላማ ነው ያለው እርሱም ሥልጣንን መያዝ ወይንም የመግዛት አቅምን ማግኘት ነው፡፡ ያ ካልተሳካ ግን ቀጣዩ ሥራ እስልምናን የሚደግፉ ህጎች እና ደንቦችን በማውጣት እስልምና ላይ የሚሰሙ የትችት ድምፆችን ዝም ማሰኘት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሸሪኣን በኃይል በመጫን እና ከሁሉ በላይ በማድረግ በሁሉም የማሕበረሰቡ ገፅታዎች በተለይም በማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ገፅታዎች ላይ በመተግበር ሕብረተሰቡን በእስልምና "ቀለማት"መሙላትን ያጠቃልላል፡፡

የእስልምናን *የሂጅራ* (ስደት) አስተምህሮ እና አቅምን የመስጠት ንዑሳን ክፍሎቹን - *ተምኪን* እና የተለያዩ ክፍልፋዮቹን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ሁሉ የሰው ሐሳቦች ወይንም የሰው እቅዶች አይደሉም፡፡ ነገር ግን ሁሉም መለኮታዊ ተስፋዎች እና በአላህ ለሙስሊሞች በምድር ላይ የተሰጡ ድሎች ናቸው፡፡

ቁርአን ህንን በሱራ 24፡55 ላይ በግልፅ ያውጃል፡

> “አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፡፡ በእኔ ምንንም የማያጋሩ ኾነው ይግገዙኛል፡፡ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው እነዚያ እነርሱ አመጸኞች ናቸው፡፡”

ይህ ሁሉንም ነገር የመቆጣጠር ፅንሰ ሐሳብ በሙስሊም ሊቃውንት በመደበኛነት የሚነገር እና በግልፅ የሚታወጅ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሼኽ ዩሱፍ አል ቃርዳዊ[48] መጪው ጊዜ የእስልምና እንደሆነና ከሁሉ ልቆ እንደሚደምቅ እና ሁሉንም ኃይማኖቶች እንደሚያሸንፍ በተደጋጋሚ ተናግረዋል፡፡ ቃርዳዊ ፈትዋቻውን የመሰረቱት ሙስሊሞች ቆስጠንጥንያን ባሸነፉ ጊዜ ሮምን እንደሚያሸንፉ መሐመድ በተናገረው ላይ ነው፡፡ በማስከተልም እስልምና መላዋን አውሮፓን እንደሚቆጣጠር ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም የእስልምናው ነቢይ መሐመድ የፋርስን፣ የሦርያን፣ የግብፅን እና የየመንን ሐብት እንደሚቀራመቱ እና ሮምንም እንደሚያሸንፉ ቃል ስለገባላቸው

48 http://www.islamonline.net/fatwa/arabic/FatwaDisplay.asp?hFatwaID=2042

ነው::[49] ስለዚህ በእስልምና ሮምን ድል መንሳት መለኮታዊ ተስፋ ነው:: ከዚህ የተነሳ ሙስሊሞች ሮምን ለመቆጣጠር ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ:: ሮም ማለት ደግሞ ተምሳሌታዊ በሆነ ንግግር አውሮፓ ማለት ነው:: ለዚህ ነው ሙስሊሞች አውሮፓን ለመቆጣጠር የሚቋምጡት::

49

" وخرج رسول الله فاخذ رداءه وجلس قال سلمان يا رسول الله رايتك حين ضربت ما تضرب الضربة إلا كانت معها برقة قال له رسول الله يا سلمان رأيت ذلك فقال أي والذي بعثك بالحق يا رسول الله قال فإني حين ضربت الضربة الأولى رفعت لي مدائن كسرى وما حولها ومدائن كثيرة حتى رأيتها بعيني قال له من حضره من أصحابه يا رسول الله ادع الله أن يفتحها علينا ويغنمنا ديارهم ويخرب بأيدينا بلادهم فدعا رسول الله بذلك ثم ضربت الضربة الثانية فرفعت لي مدائن قيصر وما حولها حتى رأيتها بعيني قالوا يا رسول الله ادع الله أن يفتحها علينا ويغنمنا ديارهم ويخرب بأيدينا بلادهم فدعا رسول الله بذلك ثم ضربت الثالثة فرفعت لي مدائن الحبشة وما حولها من القرى حتى رأيتها بعيني قال رسول الله عند ذلك دعوا الحبشة ما ودعوكم واتركوا الترك ما تركوكم).

سنن النسائي (المجتبي) كتاب الجهاد باب غزوة الترك والحبشة. حديث رقم 3176

فكسر ثلثها، وقال: "الله أكبر، أعطيت مفاتيح الشام، والله إني لأبصر قصورها الحمراء من مكاني هذا". ثم ضرب الثانية فقطع الثلثالآخر فقال: "الله أكبر، أعطيت مفاتيح فارس، والله إني لأبصر قصر المدائن أبيض". ثم ضرب الثالثة وقال: "بسم الله" فقطع بقية الحجر فقال: "الله أكبر، أعطيت مفاتيح اليمن، والله إني لأبصر أبواب صنعاء من مكاني هذا الساعة" (2).

رواه أحمد 303/4 وقال ابن حجر: إسناده حسن، انظر: الفتح 458/7

http://www.iid-alraid.de/EnOfQuran/Subject/00001/00002/00017/00040/00096.htm

# ፖለቲካዊ ስልቶች እና ኃይማኖታዊ ስደት

አሁን እንግዲህ በተለይም ወደ ምዕራብ እየተደረገ የሚገኘውን ዘመናዊ ስደት ለመረዳት አንድ ሰው የመሐመድን ኦሪጅናል ሂጅራ እርሱ የተጠቀማቸውን ስልቶች በመመርመር ማየት እንደሚገባው እጅግ በጣም ግልፅ ሆኗል፡፡

ከላይ በተባሉት ነገሮች መሰረት ግልፅ የሆነ ነገር ቢኖር ስደታቸውን በተመለከተ ያለው እስላማዊ ዕቅድ ሁለት መልክ ያለው መሆኑ ነው፡

(ሀ) ስደቱን የሚያስቀጥል የረጅም ጊዜ ስልት

(ለ) የረጅም ጊዜ ዕቅዱን ለመደገፍ የስደት ግቦችን ለመምታት የሚያስፈልጉ የአፈፃፀም ሂደቶችን እና የሚያስፈልገውን ጊዜ በማስላት የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ማውጣት

ምናልባት አንድ ሰው መሐመድ ወደ መዲና ለመሰደድ ባሰበ ጊዜ ይህ ሁሉ በአዕምሮው ውስጥ ነበረን? በማለት ሊጠይቅ ይችላል፡

በሌላ አባባል የመሐመድን ዕቅዶች እና እንዴት አካሄዱን እንደተለመ ስንመረምር ሳለን አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ይከሰታል፡ የሆነ ዓይነት ስልት ማለትም ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ግልፅ የሆነ

ዕቅድ ነድፎ ነበረን፣ ወይንስ የሆነው ሁሉ በዕድል እና ወሳኝ በሆኑ ጊዜያት ተከስተውለት ቀኑን ያሰመሩለት መልካም ሐሳቦች ናቸው?

የሆነ ዓይነት ስልት ከሆነ ምን ነበር? ያ ዝም ብሎ ግምት ብቻ እንዳልሆነ በምን እናውቃለን? ነገር ግን አንዳንዶች እንደሚሉት በአጋጣሚ ብልጭ ያለ ሐሳብ እና አጋጣሚ ወይንም ዕድል ብቻ ከሆነ ምንም መመርመር የሚገባው ነገር አይኖርም፡፡

እኛ የምናስበው እርሱ የነደፈው ስልት እንደሆነ ነው፡፡ ብዙ ጠላቶች ስለ ነበሩት እነርሱን እንዴት መጣል እንዳለበት እና ማስገበር እንዳለበት የሚያሳየውን ስልት ነድፎነበር፡፡ ይህም ደግሞ እነርሱን በመነጠል፣ ከእነርሱ ጋር ከሚዋጉት ባላንጣዎቻቸው ጋር ጥንቃቄ የተሞላበትን ግንኙነት በመፍጠር ከዝያም በትልቅ ፖለቲካዊ ዘዴ በማስኬድ ነበር፡፡ መለስ ብሎ ለማየት ጊዜው አሁን ነው፡፡

ኋላ ላይ መዲና ብሎ ወደ ጠራት ወደ ያስሪብ ለመሄድ መገለጥ አግኝቶ ነበርን? ወይንስ የተሰላ ስልት ነበር?

መሐመድ በመካ ለቁረይሾች ነቢያዊ ትሪ እናዳለው በማስመልከት ያደረገው ግለ አዋጅ ትልቅ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ ከተከታዮቹ ዘንድም ግፊት ስላደረበት ወደ አቢሲንያ በመሄድ እንዲጠለሉ ፍቃድ ሰጣቸው፡፡ ከቁረይሾች ጋር የነበረውን ልዩነቶች ለማለዘብ በመፈለግም ማዕከላዊ የሆኑ አስተምህሮዎችን በማመቻመች ስምምነትን ለመፍጠር ሞከረ፡፡ አንድ ቀን በካዕባ በነበረ ጊዜ

ዐይኖቹን አንስቶ ሲመለከት ግርምትን በሚፈጥርበት ሁኔታ የብዙ ዋና ዋና ጎሳዎችን መሪዎች በዚያ ተመለከተ፡፡ ዛሬ በሱራ 53 ላይ የሚገኘውንም አዲስ መገለጥ እንዳገኘ ተናገረ፡፡ በካዕባም ይህንን ሲደግም ሳለ  የቁራይሽ ጣዖታት ከአላህ የማማለድ ስልጣን እንዳላቸው በመናገር ከፍ ከፍ አደረጋቸው፡፡ ይህም ደግሞ የመካን ጣዖታውያን ስላስደሰታቸው ከእርሱ ጋር ሰገዱ፡፡ ነገር ግን ያ እውነት ስለመሆኑ ተከታዮቹ ጥያቄን ባቀረቡለት ጊዜ ችግር ተፈጠረ፡፡ እውነት ከሆነ የራሳቸውን ጣዖታት በማጥፋታቸው ተከታዮቹ ተሳስተው ነበረን? እውነት ከሆነ ስለ ምን ቀደም ብሎ አልተናገረም ነበር? ያ ቢሆን ኖሮ ዘመዶቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው አንዳንዶች ከቦታቸው ሳይደርሱ መንገድ ላይ የቀሩበትን ያንን ጉዞ አስቸጋሪውን በረሃ በማቋረጥ ባላደረጉ ነበር፡፡ መሐመድ በሁሉም አቅጣጫዎች ወጥመድ ውስጥ ገባ፡፡ እርሱም ደግሞ በተራው ልክ እንደ እነርሱ ሁሉ ግራ መጋባቱን በመናገር ሊያሳምናቸው ቻለ፡፡ መገለጦቹን የሚያመጣለትን መልአክ እንደሚጠይቅ በመናገር የተለመደ ምላሹን ሰጣቸው፡፡ በሚቀጥለው ቀን  እነዚህ “የሰይጣን ጥቅሶች” መሆናቸውን ነገራቸው ምክንያቱም መሐመድ በተመሳሳይ ጊዜ እያደመጠ እና እየደገመ ሳለ ገብርኤል ደግሞ መሐመድ ትንፋሹን እስኪሰበስብ ድረስ እየጠበቀ ሳለ ሰይጣን ጣልቃ በመግባት የገብርኤልን ድምፅ በማስመሰል ተናግሮ ነበርና፡፡

ይህ ጉዳዩን በሁለቱም ወገኖች በኩል አወሳሰበው፡፡ ከተከታዮቹ መካከል አንዳንዶች የተጠራጠሩ ቢሆኑም ለእርሱ አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ማሳመን ችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን የሰይጣን ጥቅሶች ማብራርያ ትርጉም ኃይማኖታቸው ሰይጣናዊ መሆኑን እና ከእርሱ አዲስ መገለጥ ጋር ያልተገናኘ መሆኑን ስለሚያሳይ ቁረይሾች ተከፉ፡፡ ባለፈው ቀን ላይ የተናገረውን ስለ ካደ እና ስለ ሻረ ቁረይሾች እንደተከዱ እና እንደ ተታለሉ ተሰማቸው፡፡ ይህ የመሐመድን አቋም የበለጠ ለጥቃት የተጋለጠ በማድረግ ጠንከር ያሉ ወቀሳዎችን አስከተለ፡፡ ነገር ግን በሚስቱ በከዲጃ እና በአጎቱ በአቡ ጣሊብ በኩል ሁለትዮሻዊ መከላከያ ስለነበረው ማዕበሉን ለማብረድ ችሎ ነበር፡፡ ሁለቱም በከተማይቱ ውስጥ የመሪነት ደረጃ ላይ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም አቡ ጣሊብ ከግንባር ቀደም ሽማግሌዎች መካከል አንዱ እና በመካ ውስጥም ባለ ስልጣን ነበር፡፡ ያለ እርሱ ፍቃድ ማንም መሐመድን ሊጎዳ አይችልም፡፡ የመሐመድ አጎት አቡ ጣሊብ የፈለገውን መናገር ይችል ዘንድ በአደባባይ ድጋፉን የቸረው ሲሆን  ነገር ግን በግል መልዕክቱን እንዲያለዝብ ነግሮት ነበር፡፡

በ620 የመሐመድ አጎት እና ሚስቱ ከዲጃ በአጭር ጊዜ ልዩነት ተከታትለው ሞቱ፡፡ ሙስሊም ሊቃውንት አስር ቀን ነው ወይንስ ሦስት ወር በሚለው ላይ ልዩነት አላቸው፡፡ መሐመድ ለጥቃት የተጋለጠ ሲሆን ጠላቶቹም እርሱን ለማሰር፣ ለመግደል ወይንም

ከሃገር እንዲወጣ ለማድረግ ሥውር እቅዶችን ይዘው ተነሱ፡፡ መሐመድ አላህ እንደገለጠለት የተናገረ ቢሆንም ነገር ግን ይህ በአደባባይ የተነገረ ዜና ነበር፡

> ሱራ 8፡30 እነዚያም የካዱት ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም (ከመካ) ሊያወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ይመክራሉም አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል፡፡ አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው፡፡

ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ የተነሳ መሐመድ በፍጥነት መንቀሳቀስ ነበረበት ስለዚህ ከቁረይሾች ከለላን ለማግኘት አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ የጎሳ መሪዎችን አነጋገረ፡፡ ሁሉም አልተቀበሉትም፡፡ መሐመድም እርሱን ያልተቀበሉበት ምክንያት የቁረይሾች ተባባሪዎች ስለሆኑ እና ኑሯቸውም በእነርሱ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ገባው፡፡

ስለዚህም የምንጮች ከተማ ወደ ሆነች ከመካ ብዙም ርቃ ወደማትገኝ ታኢፍ ወደተባለች ከተማ ለመሰደድ ወሰነ፡፡ ታኢፍ የአይሁዶች እና የአረቦች ከተማ ነበረች፡፡ ታኪፍ/ሳኪፍ ትልቅ የአረብ ጎሳ ሲሆኑ መሐመድ በንግድ ላይ በተሰማራባቸው ጊዜያት ከእነርሱ ጋር ግንኙነት የነበረው እና የሚያውቃቸው ይመስላል፡፡ መሐመድ ከማደጎ ልጁ ዚያድ ኢብን ሐሪት ጋር በመሆን ወደ ታኢፍ ያቀና ሲሆን ነገር ግን በጭካኔ ስለተባረረ ወደ መካ ከመመለስ ውጪ አማራጭ አልነበረውም፡፡ መሐመድ ከታኢፍ

የተባረረበት ምክንያት ለፀጥታ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ከቁረይሽ ዋና ጠያታት መካከል አንዷ የሆነችው የአላት መገኛ ከተማ ስለሆነችም ጭምር ነበር፡፡ ቋሚ የሆነ የተጓዦች ፍሰት ነበር፡፡ ታኢፍም ለፍራ ፍሬ ምርት የሚመች ጥሩ የአየር ፀባይ ነበራት፡፡ ስለዚህም በሞቃት የበጋ ወራት የብዙ ኃብታም የመካ ነዋሪዎች መዳረሻ ነበረች፡፡ መሐመድን በከተማቸው ውስጥ የሚያስጠልሉ ከሆነ ብዙ ነገር እንደሚያጡ ነበር፡፡

የእርሱ ኦፊሴላዊ ግለ ታሪኮች እንደሚናገሩት ለቁረይሾች እንዳይነግሩ የለመናቸው ቢሆንም ነገር ግን እነርሱ ስለተናገሩ እርሱ ወደ መካ በደረሰ ጊዜ ወሬው ከእርሱ ቀድሞ በመድረሱ ምክንያት ለሕይወቱ ስለ ሰጋ ወደ ከተማይቱ ሊገባ አልቻለም ነበር፡፡ ነገር ግን የግለ ታሪኮቹ ጸሐፍት በማስከተል እንደጻፉት ከሆነ ከመካ ከተማ መሪዎች አንዱ እና የሽማግሌዎች ኮሚቴ አባል ወደ ነበረው ሙ'ተዒኣም ቢን አዲ እንዲያስጠልለው የልመና መልዕክት ልኮ ነበር፡፡ ኢብን አዲ ከለላ ሊያደርግለት በመስማማቱ ምክንያት ያንን ሌሊት በእርሱ ቤት አሳለፈ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት መሐመድ በኢብን አዲ ጥበቃ ስር በመሆኑ ምክንያት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ከቁረይሾች ጉዳት እንደማይደርስበት ሁሉም ሰው ማየት እንዲችል አስተናጋጁ እና እንግዳው አብረው ወደ ውጪ ወጡ፡፡

በተለያዩ ሙስሊም ሊቃውንት የተዘጋጁትን የተለያዩ ሲራዎችን ወይንም ደግሞ የመሐመድ ሕይወት ዘገባዎችን በጥንቃቄ

በመመልከት መርምረናል፡፡ ከእነርሱም ያገኘናቸው አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮች አሉ፡

1. መሐመድ ወደ ታኢፍ ያደረገው ጉዞ ጥብቅ በሆነ ምስጢር የተደረገ ነበር፡፡ ከሙስሊም ማሕበረሰብ መካከል ሐሳቡንና እቅዱን ያወቀ አልነበረም፡፡
2. መሐመድ ምስጢራዊ የሆኑ የመረጃ አቀባዮች መረብን መፍጠር ችሎ ነበር፡፡ እነዚህም *በሲራዎቹ* ወይንም ደግሞ በግለ ታሪኮቹ ውስጥ አል-ዑዩን[50] ወይንም "ክትትል የሚያደርጉ ዐይኖች" በመባል ተጠርተዋል፡፡ ለመሐመድ ደግሞ ጥቅም ይኑራቸውም አይኑራቸውም ሁሉንም ነገር ይዘግቡ ነበር፡፡ የመሐመድን ሲራ የሚያጠኑ ሙስሊም ሊቃውንት ከእነዚህ አል ዑዩን መካከል አንዳንዶቹን ይጠቅሳሉ፡፡ እነርሱም፡ ሰዐድ ቢን መዐዝ፣ ሰዐድ ቢን ኢባዳ፣ አብዱላህ ቢን ሩዋሀ፣ ኸዋት ቢን ጁቢዐር ነበሩ፡፡
3. በሙስሊም ማሕበረሰብ እና በሌሎች ደጋፊዎች መካከል ከሚገኙ ምንጮች ጋር የሚገናኝ ምስጢራዊ የመረጃ መረብ ፈጥሮ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መሐመድ በታኢፍ በተጎዳ ጊዜ እና የማንቂያ ምልክት መስጠት በቻለ ጊዜ ከመልዕክተኞቹ አንዱ የሆነው ኸዚም ወደ ኢብን አዲ

[50] አንዋር ፊ ሲራት ዐነቢ አል ሙኽታር በሱሌይማን ቢን መሐመድ አል ሊሂመድ http://www.almotaqeen.net/ ሰዐድ ቢን መዐዝ፣ ሰዐድ ቢን ኢባዳ፣ አብዱላህ ቢን ሩዋሀ፣ ኸዋት ቢን ጁቢዐር፣ እነዚህ አል ዑዩን ነበሩ

በመሄድ እርዳታ ጠይቆ ነበር፡፡ የተቀረው የተምታታ እንቅስቃሴ ቀደም ሲል የተባለውን ነጥብ የሚያብራራ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ባይኖሩ ኖሮ እንደዛ ባለ ፍጥነት መንቀሳቀስ ባልቻለም ነበር፡፡

4. ይህ ማለት ከተለያዩ ጉዳዮች አኳያ መሐመድ ነገሮችን እንዳጤነ እና ለተለያዩ ውጤቶችም አማራጭ የሆኑ እቅዶችን በማስቀመጡ የተነሳ በተባረረ ጊዜ “የእርዳታ” እቅዱን ተግባራዊ እንዳደረገ እናያለን፡፡
5. በሌላ አባባል ከውጪ ሲታይ የተደራጀ የመንግሥት ስርኣት ለመጀመርያ ጊዜ በመዲና ተግባራዊ የተደረገ ቢመስልም ነገር ግን እውነታው ረቂቅ በሆነ መልኩ ቀደም ሲል የተቀመጠ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ እና ከሌሎች አጋጣሚዎች ግልፅ እንደሆነው መሐመድ የመረጃ አቀባዮችን፣ የግል ጥበቃን፣ የመረጃ መስመሮችን፣ የአቅርቦት መንገዶችን፣ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪዎችን፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ድብቅ ስርኣቶች ነበሩት፡፡

ግልፅ የሆነው ነገር ኢብን አዲ እንደ ካፊር፣ ሙስሊም እንዳልሆነ ሰው ኖሮ የሞተ ሲሆን ነገር ግን ለመሐመድ ጥበቃን ማድረጉ ነው፡፡ የአመለካከት ልዩነቶች አሉ ነገር ግን የጥበቃ አቅርቦት በጋራ “ጥቅሞች” ምክንያት የሚደረግ ነው፡፡ ሁለቱም ወገኖች የሚያገኙት ጥቅም አለ፡፡ ስለዚህ ኢብን አዲ ከመሐመድ በሚያገኘው እርዳታ

ምክንያት ነው ጥበቃን ያደረገለት፡፡ አንዳንዶች የተጠቀሱ ቢሆኑም እንኳ ከምንጮቹ መካከል አንዳቸውም ተዓማኒነት ያላቸው ባለመሆናቸው ምክንያት እነርሱን ማመን ተገቢ አይደለም፡፡ ማስተዋል የሚገባን አስፈላጊው ነገር *የደሩርዓን* (የግድ አስፈላጊ የሆነ ነገር) እና *የታይሲርን* (ሸክምን ማቃለል) መርህን መጠቀሙ ነው፡፡

በአረማዊነት ላይ የተመሰረተውን የኢብን አዲን አለማመን በቸልተኝነት ለማለፍ መሐመድ ዝግጁ ነበር፡፡ የአጎቱ የአቡ ጣሊብንም አለማመን በቸልተኝነት አልፎ ነበር፣ አሁንም *የደሩርዓ* መርህ! ይህ መርህ አብዛኞቹ ሰዎች ከሚያስተውሉት በላይ የጠለቀ ነው፡፡ መሐመድ በታኢፍ ጥገኝነትን ይፈልግ በነበረበት ጊዜ ከአንድ *የካፊር* (ከሃዲ አረማውያን) ቡድን ወደ ሌላው መሸሹ አስገራሚ ነው፡፡ (ይህንን መርህ ኋላ ላይ በድጋሜ የምናየው ይሆናል፡፡) ይህ በሃገራቸው ተፈላጊ አሸባሪዎች ለሆኑት ለዛሬዎቹ *ሙጃሂዲን* ጠቃሚ መርህ ሆኗል፡፡ ከእነዚህ *ካፊሮች* በመሸሽ በአውሮፓ ወይንም በምዕራባውያን *ካፊሮች* መካከል በጥገኝነት ይኖራሉ፡፡ ይህ እንግዲህ በአውሮፓ ምቾት ውስጥ በመቀመጥ የገዛ ሃገራቸውን እና አዲሱ ሃገራቸውን ለማጥቃት በመወሰን ነው፡፡

ምን ነበር የሆነው? መሐመድ በመካ እንዴት ነበር የኖረው? ወደ መዲና እስከ ተሰደደበት ጊዜ ድረስስ ከቁረይሾች ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ነበር?

ይህ በመሐመድ ህይወት ውስጥ በጣም የተጣበበው ጊዜ እንደነበር ይታሰባል፡፡ መጀመርያ መሐመድ ወደ አቢሲንያ ከተሰደዱ ሙስሊሞች መካከል የአንዱ ሚስት የነበረችዋን ሰዐወዳ የተባለችን ባልቴት አገባ፡፡ በመቀጠልም ያኔ ገና 6 ዓመት ልጅ የነበረችዋን የጓደኛው የአቡበከርን ልጅ አይሻን አገባ፡፡ ይህ ማለት በማሕበራዊ ግንባር የተረጋጋ እና ባለጠጋ እንደ ነበረ ያሳያል ምክንያቱም ንግዱ ቀጥሎ ነበረና፡፡ በእርግጥ የከዲጃ ንግድ ትርፍ አስደማሚ ነበር፡፡ የእርሷ ንግድ ወርሃዊ ትርፍ ከቁረይሽ ጎሳ አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ጋር እኩል እንደነበር ይነገራል፡፡ ምናልባትም ትርፉ ቀንሶ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ለእርሱ ምቾትን ለመስጠት በቂ ነበረ፡፡ ባይሆን ኖሮ ስለ ሕይወቱ እጅግ በጣም ይጨነቅ ነበር፡፡ ስደቱን በተመለከተ ሙስሊም የግለ ታሪክ ጸሐፍት ከሆነው በላይ ነገሩን በማጋነን ጽፈው ሊሆን ይችላል፡፡

ከመሐመድ ሂጅራ በፊት ስለነበሩት ሁለቱ ዓመታት ማወቅ የሚገባን በጣም አስፈላጊው ገፅታ መሐመድ በቀጣይነት ሊሄድባት ስለነበረችዋ ስለ ያስሪብ ከተማ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንዴት እንዳሳለፈ ነው፡፡ ይህችንም ከተማ መዲናቱ አል ነቢ ወይንም “የነቢዩ ከተማ” በማለት ስሟን ለውጧል፡፡ በብዙዎች ዘንድም መዲና በሚለው ስሟ ትታወቃለች፡፡

# በያስሪብ የነበረው ሁኔታ

ያስሪብ የተለየች የአይሁድ ከተማ ነበረች፡፡ አውስ እና ኸዝራጅ በመባል የሚታወቁ ሁለት የአረብ ጎሳዎች ነበሩ፡፡ ኸዝራጅ በእናቱ በአሚና በኩል የመሐመድ የአክስት ልጆች ከሆኑት እና እንዲሁም በአያቱ በአብደል ሙጠሊብ በኩል ከሚዛመዱት ከበኑ አል ነጃር ጋር ዝምድና ነበራቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ መሐመድ ከአይሁድ ከተማ ከያስሪብ ጋር ጠንከር ያለ ቤተሰባዊ ትስስር ነበረው፡፡ በእርግጥ አይሁዶች ያስሪብን ስለቆረቆሯት የአይሁድ ከተማ እንደሆነች ነበር የሚያስቡት፡፡ ነገር ግን የአረብ ጎሳዎች የሆኑት አውስ እና ኸዝራጅ ከተማይቱን የራሳቸው ለማድረግ ይፈልጉ ነበር፡፡ አውስ እና ኸዝራጅ ሥልጣን ለመያዝ እና ከተማይቱን ለመቆጣጠር በመካከላቸው ከነበረው ትግል የተነሳ ግልፅ የሆነ የስልጣን ተዋረድ ከነበራቸው ከተለያዩ የአይሁድ ጎሳዎች ጋር በተናጠል ወዳጅነት መስርተው ነበር፡፡

መሐመድን በጣም እንደሳበው የሚታሰብ አንድ ነገር ቢኖር የያስሪብ ሰዎች በቁረይሾች ላይ የነበራቸው ቁርሾ ነበር፡፡ ያስሪብ የአረብያ ዋነኛ የንግድ ከተማ ነበረች ነገር ግን የዘምዘም ውኃ በተገኘ ጊዜ እና ውኃ ችግር መሆኑ በቀረ ጊዜ መካ እንደ ማረፍያ እና ትንፋሽ መሰብሰብያ ጣብያ ዋነኛ የሲራራ ነጋዴዎች መንገድ

ሆነች፡፡ አውስ እና ኸርጅ በያስሪብ ውስጥ የነበረውን የአይሁድን የበላይ ነት እና ቁረይሾች በርቀት ሆነው የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ የመስበር ብርቱ መሻት ነበራቸው፡፡

## ከ15 የአረብ[51] ጎሳዎች ጋር ወዳጅነትን መፈለግ

የመሐመድ ተዓማኒ የግለ ታሪክ ጸሐፍት እንደሆኑ የሚታሰቡት ኢብን ሒሻም እና ኢብን ከሢር እንደተናገሩት መሐመድ 15 የአረብ[52] ጎሳዎች ጥገኝኝት እንዲሰጡት ጠይቆ ነበር ነገር ግን ከቁረይሽ ጋር ከነበራቸው ትስስር የተነሳ አንዳቸውም ፍቃደኞች አልሆኑም ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ዐይኖቹን በያስሪብ ላይ በማድረግ ያንን አማራጭ በምን መልኩ መቅረብ እንዳለበት ማጥናት ጀመረ፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር ከአውስ ጎሳ የሆኑ ስድስት ሰዎች ኻዝራጆችን ለመቋቋም ከቁረይሾች ጋር ወዳጅነትን ለመፍጠር በ620 ዓ.ም. ወደ መካ የመጡት፡፡ መሐመድ እነርሱ ወደ መካ መምጣታቸውን ባወቀ ጊዜ ፈልጎ በማግኘት ያንን ወዳጅነት እንዳይመሰርቱ ተፅዕኖ በማሳደር አቅጣጫ እዲለውጡ ማድረግ ችሎ ነበር፡፡ ስድቱ ሰዎችም በእናቱ በኩል የመሐመድ የሩቅ ዘመዶች ሆነው ተገኝተው ነበር፡፡

[51] አብካር አል ሳካፍ ዐዲን ፊ አል ጀዚራ አል አረብያ ባብ አረድ ዐነቢ ነፍሰሁ አለ ከባኢል
[52] ةو عد دمحم ضعب لئابقلا يلإ هتوعد

በ621 ዓ.ም. ወደ 12 የሚሆኑ ሰዎች (6 ከአውስ እና 6 ከኻዝራጅ) በአቃባ ሸለቆ[53] ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ፣ ይህም "የአቃባ ኪዳን" በመባል ይታወቃል፡፡ መሐመድም ከሥርኣት አልበኝነት ተቆጥበው በቁርኣን እንዲኖሩ መመርያን ሰጣቸው፡፡

በ622 ዓ.ም. 75 የሚያክሉ ከአውስ እና ከኻዝራጅ የሆኑ ተጨማሪ ሰዎች መጡ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት ሁለተኛውን የአቃባ ቃል ኪዳን ያደረጉት 72 ወንዶች እና 3 ሴቶች ነበሩ ይላሉ፡፡ አሁን መሐመድ እና ተከታዮቹ በዘዴ መካን በመልቀቅ ወደ መዲና መሰደድ እንዲችሉ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

መሐመድ በኢብን አዲ ጥበቃ ስር በመሆን ባሳለፋቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ ከተከታዮቹ መካከል ቁልፍ የሆኑትን ወደ መዲና/ያስሪብ ልኮ ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች ሁኔታዎችን እንዲቃኙ እና መረጃም ደግሞ እንዲሰበስቡ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን የተገለጠውን ያህል ከቁርአን ለሰለሙት አዳዲስ ሰዎች ያስተምሩ ነበር፡፡ መሐመድ በሁሉም አቅጣጫዎች የረቀቀ ስሌት ሲያሰላ ሳለ ተከታዮቹ በፀጥታ ሆነው በሁለቱ መካከል ወዲያና ወዲህ ይመላለሱ ነበር፡፡ ከሥልጣን ተዋረድ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ሁኔታዎችን እና ስለመዲና ማሕበረሰቦች መሰብሰብ የሚችላቸውን መረጃዎች በሙሉ ይመረምር ነበር፡፡

---

53 http://www.al-eman.com/Islamlib/viewchp.asp?BID=251&CID=42#s4

ሙሳዐብ በመካከል ወዲያና ወዲህ ይሄዱ ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ በመዲና ውስጥ ፀሎትን ጨምሮ ሁሉም ኃይማኖታዊ ግዴታዎች ህጋዊ ስለተደረጉ አላህ መሐመድን እንደ መጨረሻ ነቢይ መላኩን ከማስተማር በስተቀር ብዙ ማስተማር አላስፈለገም ነበር፡፡ ነገር ግን በመመርያ የሚፈፀሙ ልማዶችን በተመለከተ የተገለጠ ነገር አልነበረም፡፡ ሁሉም ግዴታዎች ወይንም የእስልምና አዕማዶች የሚባሉት ኋላ ላይ በመዲና የተገለጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ዋናው ጥረት መሐመድን ብቃት እንዳለው መሪ ማስቀመጥ ነበር፡፡ በእርግጥ ሊነገር የሚችል ተዓምራትም ስላልነበረ ሰዎችን አንድ የማድረጊያ መሰረቱ የሚያጠነጥነው በቁረይሽ ጠላትነት እና ለመሐመድ ድጋፍ በማድረግ ላይ ነበር፡፡[54]

በተመሳሳይ ጊዜም በቁረይሾች ላይ የሚሰነዝረውን ውግዘት በከፋ ሁኔታ ቀጠለበት፡፡ ከዚህም በላይ መሐመድ ስለ አይሁዶች ጥሩ የሆኑ መገለጦችን መናገር ጀመረ፡፡ ይህ ከቁርአን ግልፅ ይሆናል ምክንያቱም ስለ አይሁዶች በጎ በጎውን የሚናገሩ መገለጦች ሁሉ ከዚህ ዘመን የሆኑ ናቸውና፡፡ መሐመድ ስለ ስደቱ እቅድ ማውጣቱን በቀጠለ ቁጥር ለአይሁድ የሚያደሉ መገለጦቹም እየተጠናከሩ መጡ፡፡ እነዚህ መገለጦች አይሁዶች ምንም ነገር ሊፈሩ እንደማይገባቸው ወደ ማሳመን ተቃርበው ነበር፡፡ በአውስ

[54] ሲራት ኢብን ከሢር ቅፅ 2 ገፅ 352፣ የአቃባ ቃል ኪዳን ክፍል 1 እና 2፣ ሲራት ኢብን ሂሻም፣ ቅፅ 2 ገፅ 454፣ በያት አል አቃባ ወ ሪጃሌህ

እና በኻዝራጅ ግብዣ መሰረት የሚመጣ ቢሆንም ከአስተናጋጆቹ በተለየ ሁኔታ በእነርሱ ቅዱሳት መጻሕፍት (በቶራህ እና መዝሙራት) እንደሚያምን ለአይሁዶች ምልክቶችን ይሰጥ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ የተቀሩት ሙስሊሞች የእርሱን እምነት እንደሚከተሉ አይሁዶች አምነውና ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ በእርሱ አመራር ስር የኃይል ሚዛኑ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀጥል መሐመድ አይሁዶችን አሳምኖ ነበር፡፡ በእርግጥ የእርሱ መገለጦች አይሁዶች ከሁሉም በላይ የተመረጡ መሆናቸውን ስለሚናገሩ ተሰሚነታቸው እንደሚጨምር አስበው ነበር፡፡ እንደ ተመረጡ ሕዝቦች ደግሞ ሁሉም ነቢያት ከእነርሱ ነው የተገኙት፣ ወዘተ. ቁርአንም ደግሞ እነርሱ የያዙት ነገር የአረብኛ ቅጂ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ መሐመድ አይሁዶች የታኢፍ ሕዝቦች እንዳደረጉት ከቁረይሾች ጋር በማበር እንቢ እንዳይሉት ለአይሁዶች የሐሰት የደህንነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርግ የማታለል እቅድን አስቀመጠ፡፡

መሐመድ በምንም ሁኔታ ውስጥ የቁረይሽ የንግድ ሸሪኮች የሆኑት የያስሪብ አይሁዶች እርሱን አሳልፎ ለመስጠት ማለም እንኳ እንደሌለባቸው ወስኖ ነበር፡፡ ታኢፍ በምንም ዓይነት መደገም የለበትም፡፡ በሌላ አባባል የአይሁዶችን እርዳታና ድጋፍ ለማግኘት እያንዳንዱን ቀዳዳ እየደፈነ ነበር፡፡

ይህ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ሽርክና ነበር፡፡ አይሁዶች ባለጠጎች፣ ግልፅ የሆነ ኃይማኖች ያላቸው እና የተገለጠ መጽሐፍ ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት አረቦች ይቀኑባቸው ነበር፡፡ አይሁዶች ያላቸው ነገር በሙሉ አረቦች የሚመኙትን ከፍታ ሰጥቷቸው ነበር፡፡ አረቦች ነቢይ አልነበሯቸውም፣ መጽሐፍ አልነበራቸውም፣ የተጨበጠ ኃይማኖትም አልነበራቸውም ነገር ግን በመሐመድ በኩል የሚፈልጉትን ከፍታ ማግኘት እንደሚችሉ አስበው ነበር፡፡ አውስ እና ኻዝራጅ በማያቋርጥ ሁኔታ እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩ ቢሆኑም ነገር ግን የአይሁዶችን የበላይነት ለመስበር መስማማትን ይፈልጉ ነበር፡፡ ነገር ግን ያንን የማድረግ ችሎታ አልነበራቸውም፡፡

መሐመድ የአይሁዶች ተፅዕኖ ከያስሪብ ባሻገር የተዘረጋ እንደሆነ ያውቅ ስለነበር በእርሱ እና በአይሁዶች መካከል መንገድን ለመጥረግ *የሙደራት / ታቂያ እና የደሩርዐን* አስተምህሮ አስቀመጠ፡፡

## *ሙደራት*[55] مداراة

*ሙደራት* የሱኒ የአታላይነት አስተምህሮ ነው፡፡ *የታቂያ* ሌላኛውም ስም ነው፡፡ *ከሉላማ* ወይንም ደግሞ ከእስልምና ሊቃውንት ክበብ ውጪ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ስለዚህ አስተምህሮ አያውቁም፡፡

55 http://www.islamadvice.com/nasiha/nasiha160.htm

ሙደራት ማለት ማደናነቅ፣ የግብዝነት አድናቆት፣ ማታለል፣ ቆዳን ማስወደድ፣ ማጭበርበር፣ እኩል መራመድ፣ መሸፈን፣ መደበቅ ወይንም መሰወር ማለት ነው፡፡ ይህ የማታለል ጠባይ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሰዓት ሁሉ በማንም ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን የሱኒ ምሑራን በቋሚነት የሙደራት ዒላማ ውስጥ መግባት አለባቸው ያሏቸውን አሥር ዓይነት ሰዎች ለይተው አስቀምጠዋል፡

1. ካፊር (ሙስሊም ያልሆነ ሰው)
2. ክፉ የሆነ መሪ
3. ልባቸው በቅርቡ ከእስልምና ጋር የታረቀ ሰዎች (አዲስ የሰለሙ)
4. ከእስልምና ልቡ ያፈነገጠውን ሰው ወደ እስልምና ለመመለስ
5. አማኞች ያልሆኑትን በመምሰል የሳተ ሙስሊም
6. የተማረን ሰው ወይንም ሳይንቲስት ከዕውቀቱ ለመጠቀም
7. ጓደኛ
8. ጠላቶች
9. የትዳር አጋር
10. የታመመ ሰው (ለምሳሌ ያህል ደህና እንደሚሆን ወይንም ደህና መምሰሉን በመንገር)

የሱኒ ሊቃውንት ይህንን አመለካከት ለማፅደቅ በተለያዩ የቁርአን ጥቅሶች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ዋና ዋና ምሳሌዎቻቸው በመዋሸት

ሙደራትን የተለማመዱት ሁሉም ነቢያት ናቸው፡፡ እንደ ኢብራሂም (አብረሃም)፣ መርየም (የኢየሱስ እናት ማርያም)፣ ሹአይብ (አረባዊ ነቢይ) እና የእስልምናው ነቢይ መሐመድ ማለት ነው፡፡

በሱራ 21፡51-66 መሰረት ኢብራሂም ዋሽቷል፡

> ለኢብራሂምም ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው፡፡ እኛም በእርሱ (ተገቢነት) ዐዋቂዎች ነበርን፡፡
>
> ለአባቱና ለሕዝቦቹ «ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የኾናችሁት ምንድን ናት?» ባለ ጊዜ (መራነው)፡፡
>
> «አባቶቻችንን ለእርሷ ተገዢዎች ኾነው አገኘን» አሉት፡፡
>
> «እናንተም አባቶቻችሁም በእርግጥ በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበራችሁ» አላቸው፡፡
>
> «በምሩ መጣህልን? ወይንስ አንተ ከሚቀልዱት ነህ?» አሉት፡፡
>
> «አይደለም ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ የፈጠራቸው ነው፡፡ እኔም በዚህ ላይ ከመስካሪዎቹ ነኝ» አለ፡፡
>
> «በአላህም እምላለሁ ዞሪዎች ኾናችሁ ከሄዳችሁ በኋላ ጣዖቶቻችሁን ተንኮል እሠራባቸዋለሁ» (አለ)፡፡

(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮችም አደረጋቸው፡፡ ለእነሱ የኾነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)፡፡

«በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው? እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው» አሉ፡፡

«ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል» ተባባሉ፡፡

«ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎቹ ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት» አሉ፡፡

«ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ አንተ ነህን?» አሉት፡፡

«አይደለም ይህ ታላቃቸው ሠራው፡፡ ይናገሩም እንደ ኾነ ጠይቋቸው» አለ፡፡

ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ፡፡ «እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮቹ እናንተው ናችሁም» ተባባሉ፡፡

ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ፡፡ «እነዚህ የሚናገሩ አለመኾናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤» (አሉ)፡፡

«ታዲያ ለእናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር ከአላህ ሌላ ትገዛላችሁን?» አላቸው፡፡

በሱራ 19፡25-26 መሰረት መርየም (ማርያም) ውሸትን ተናግራለች

> «የዘምባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዢት ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና፡፡
> «ብይም፣ ጠጭም፣ ተደሰችም፡፡ እኔ ለአልረሕማን ዝምታን ተስያለሁ፤ ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም» በይ፡፡

በሐዲስ ቁጥር 5780 ላይ ቡኻሪ እንደ ዘገበው ነቢዩ እንዲህ አለ፡ "ጠላቶቻችንን በፊታችን እየሳቅን በልባችን እየተራገምን ልናስተናግዳቸው ይገባል፡፡"

መሐመድ *"ጦርነት ሊታላይነት ነው"* እስከማለት ደርሷል፡፡ ይህ ማታለል በግል ደረጃ ወይንም ደግሞ በመሪዎቹ እና በተቋማቱ በኩል በማሕበረሰብ ደረጃ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ እባካችሁን *መስጊድ እና በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ሚና* (ነባራዊ ሁኔታን በመጠቀም ለመኖር የሚያስችል ታቂያን በተመለከተ ያለው ቁርአናዊ ትዕዛዝ) የሚለውን በነዚህ ደራሲያን የተጻፈውን መጽሐፍ ተመልከቱ፡፡

መሐመድ ለአይሁዶች የሚያደሉ መገለጦችን እንደተቀበለ በመናገር *ታቂያን* ተለማምዷል፡፡ በአላህ የተመረጡ ሕዝቦች መሆናቸውን ተናገረ፣ የእነርሱን ኃይማታዊ ቃላት በመጠቀም የአብዛኞቹን ነቢያቶቻቸውን ታሪኮች ተረከ ወዘተ. እርሱም ደግሞ በነዚህ ነቢያት መስመር ውስጥ ያለ ወደ አረቦች የተላከ ነቢይ መሆኑን

ተናገረ፡፡ ነገር ግን ለአይሁዶች የሚያደሉ እነዚህን መገለጦች ሁሉ ይናገር በነበረበት ጊዜ የልቡ ፍላጎት የተለየ ነበር፡፡ ይህም ደግሞ ከአውስ እና ኻዝራጅ ጋር ባደረገው ውል ይዘት ውስጥ ተገልጧል፡፡ ምክንያቱም ለአይሁዶች በአስመሳይነት ናገራቸው ከነበራቸው ነገሮች ጋር ሁሉ መሰረታዊ በሆነ መንገድ ይቃረን ነበርና፡፡

ኢብን ኢስሐቅ[56] በሲራው ውስት እንደዘገበው በሰባ አምስቱ ሰዎች የተደረገው የታማኝነት ቃል ኪዳን በጣም ልዩ ነበር፡፡ የመሐመድን መልዕክት ለመስበክ እና ለመወጅ የተደረገ ኃይማኖታዊ የታማኝነት ቃል ኪዳን አልነበረም ነገር ግን "ቀዮችን እና ጥቁሮችን" ለመዋጋት፣ ለመግደል ወይንም ለማስገዛት የተደረገ ወታደራዊ ቃል ኪዳን ነበረና፡፡ መሐመድ እንደተናገረው ቀዮች አይሁድ ሲሆኑ ጥቁሮች ደግሞ ቁረይሽ ናቸው፡፡

## *የጦርነት ቃል ኪዳን*

በቃል ኪዳኑ ምሽት በጣም ሚስጢራዊ በሆነ ሁኔታ መሐመድ ከአጎቱ ከአባስ ቢን አብዱል ሙጠሊብ ጋር በመሆን ከመካ ወጣ፡፡ አባስ ይህ ወዳጅነት የጦርነት ወዳጅነት እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ አውስ እና ኻዝራጅ የታማኝነት ቃል ኪዳኑን ለመፈፀም በተሰበሰቡ

---

56 http://www.al-eman.com/Islamlib/viewchp.asp?BID=249&CID=30 and http://sirah.al-islam.com/Display.asp?f=msr10064

ጊዜ አባስ (የመሐመድ አጎት) መጀመርያ ተናገረ፡፡ ምን እንደሚረዱ እና የታማኝነት ቃል ኪዳን የሚገቡት ለምን እንደሆነ ያውቁ እንደሆን ጠየቃቸው፡፡ ምን እንደሚረዱ እንደሚያውቁ ነገሩት፡፡ የመሐመድም አጎት ቀዮችን (አይሁድን) እና ጥቁሮችን (የመካን ከሃዲዎች ማለትም ቁረይሾችን እና ሌሎች የመካን ጎሳዎች ሁሉ) ለመዋጋት የታማኝነት ቃልኪዳን እንደሚገቡ ነገራቸው፡፡ እንዲህም አላቸው "ስለዚህ ንብረታችሁን እና ሽማግሌዎቻችሁ ያለ አግባብ እንዲገደሉ ለአደጋ ያጋለጣችሁ ከመሰላችሁ አሳልፋችሁ ስጡት፡፡ ይህንን ካደረጋችሁ በአላህ ይህ ለዘለዓለም አሳፋሪ የሆነ ነገር ነው የሚሆነው፡፡ ነገር ግን ለአላህ ታማኞች በመሆን ብልጥግናን ለመካፈል፣ ክቡራን የተባሉትን ለመግደል ይህንን የጦርነት ቃልኪዳን ማድረግ እንደሚጠበቅባችሁ ከገባችሁ በዚህ እና በመጪው ዓለም እናንተ ምርጦቹ ናችሁ፡፡"

ምን ሊሰሩ እንደሆነ አባስ ካሳወቃቸው በኋላ መሐመድ እነርሱ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዳያደርጉ የሚከለክሏቸውን ነገሮች እንደማያደርግ ተናገረ፡፡ ስለዚህ ከልዑካኑ መካከል አንዱ የሆነው አል በራ የመሐመድን እጅ በመያዝ እንዲህ አለ፡

አንተን እንደ ነቢይ በላከህ በእርሱ እምላለሁ የራሳችን የሆኑቱ እንዳያደርጉ የምንከለክላቸውን አንተንም እንከለክልሃለን የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ቃል ኪዳን እንገባልሃለን ነገር ግን እና የጦርነት

ልጆች ነን፣ እርስ በርሳቸው የሚዋጉ ጎሳዎች ቤተሰቦችም ነን፣ ይህንን ከትውልድ ወደ ትውልድ ወርሰነዋል፡፡”

በዚህ ጊዜ አቡ አይሣም ጣልቃ በመግባት እንዲህ አለ፡

“የአላህ መልዕክተኛ ሆይ በኛና በአይሁድ መካከል ገመዶች አሉ (ማለትም ትስስር አለ) እናም እኛ እነዚህን ልንቆርጣቸው ነው፣ ያንን ካደረግን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ያለንን ስምምነት አልታዘዝንም ማለት ነው እናም አላህ ወደ ሕዝቦችህ ተመልሰህ እንድትመጣ ያሳይህ ይሆን?”

ይህ ለእርሱ በጣም ግልፅ ነበር፣ እርሱ በግልፅ እንደ ተናገረው ገመዶቹን ሊበጥሱ ነው - ማለትም ከአይሁድ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት፡፡ ለአይሁዶች የሚያደሉት አዳዲስ መገለጦች ተብዬዎቹ ሁሉ ደባ ወይንም የማጥመጃ ዘዴ መሆኑን ሁላቸውም አውቀውት ይሆናል ነገር ግን እርግጠኛ መሆን መፈለጋቸው አልቀረም፡፡ አቡ አይሣም እያለ ያለው ከአይሁዶች ጋር ጠላት መሆናቸው አግባብነት ከሌለው የአላህ መልዕክተኛ ሐሳቡን በመለወጥ ወደ መካ መመለስ እንዳለበት ነው! ያ ከሆነ ደግሞ አውስ እና ኻዝራጅ ድርብ ኪሳራ ይደርስባቸዋል ምክንያቱም መሐመድን በከተማቸው ውስጥ በስደተኝነት በማስተናገዳቸው ምክንያት ከአይሁዶች እና ከቁረይሽ ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት ያጣሉና፡፡

መሐመድ ፈገግ በማለት እንዲህ አለ “ደም፣ ደም ጥፋት፣ ጥፋት”፡፡ ይህ ማለት የጦርነት አዋጅ እና መግደል እንዲሁም ማጥፋት ማለት

ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እነሆ የአይሁዶችን ፍፃሜ ወስኛለሁ ማለት ነው፡፡ እነርሱ ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳሉ ከቁረይሾችም እገላገላለሁ፡፡ አሮጌው ሥርአት ይወገድና አዲስ ሥርአት እመሰርታለሁ… በማስከተል ያለውን ስሙ፡

“እኔ ከናንተ ነኝ እናንተም ከኔ ናችሁ፣ እናንተ የምትዋጓቸውን እዋጋቸዋለሁ፣ እናንተ ሰላምን ከምታደርጉባቸው ጋር ሰላም አደርጋለሁ፡፡ ተመልከቱ እኔ ከናንተ ነኝ እናንተም ከኔ ናችሁ፣ ጠላቶቻችሁ ጠላቶቼ ናቸው እዋጋቸውማለሁ፣ ሰላምንም ከምታደርጉባቸው ጋር ሰላምን አደርጋለሁ፡፡”

በሚገርም ሁኔታ መሐመድ ነቢይ መሆኑን ቢናገርም በዚህ ስምምነት ዙርያ ከአላህ ዘንድ የመጡ ምንም ዓይነት መርሆች፣ ሁኔታዎች፣ መገለጦች እና ትዕዛዛትን አላስቀመጠም፡፡ በአንፃሩ ግን አይሁዶችን እና ቁረይሾችን ማስወገድ የሚለውን ዕቅድ ተከትሎ ሄደ፡፡ ይህም ሽርክናው እና ስደቱ በፖለቲካ ላይ የተመሰረተ እና ፖለቲካዊ ግብ አለው የሚለውን ነጥብ ያረጋግጣል፡፡ ለጥቃቅን ነገሮች እንኳ ከአላህ መገለጥን እንደተቀበለ ይናገር የነበረው መሐመድ ምንም የሚለው ነገር አልነበረውም፡፡ ያደረገው ብቸኛው ነገር ቢኖር በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን እቅድ ተቀብሎ መጓዝ

ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህ አል-በር እና የተቀሩት[57] በታላቅ ደስታ ለመሐመድ ቃል ገቡለት፡፡

ከአቃባ ቃል ኪዳን አነጋገር ግልፅ እንደሆነው ሙሉ በሙሉ እምነታቸውን እንዲቀይሩ ወይንም እንዲገዙ በማድረግ አላማ ቁረይሾችንና አይሁዶች ለመዋጋት ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡ ስለዚህ መሐመድ ያስሪብ ከመድረሱ ከረጅም ጊዜ በፊት የአይሁዶችን እጣ ፈንታ ወስኖ ነበር ማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ለመጀመርያ ጊዜ ያስሪብ በደረሰ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ዞሮ በመስገድ እና አብሯቸው በመፆም ወደ አይሁዶች የመቅረብ እና እነርሱን የመወዳጀት ሁኔታን በአደባባይ አሳየ፡፡ በአውስ ካዝራጅ እና የመካ አዳዲስ ስደተኞች መካከል የወንድማማችነት መተሳሰብ እንዲኖር በሚናገረው የመዲና የመጀመርያው ቻርተር ውስጥ እንኳ እንዲካተቱ አድርጎ ነበር፡፡ ህገወጦች መሆናቸውን በመናገር ከቁረይሾች ጋር ጠላትነትን አወጀ፡፡ በቻርተሩ ውስጥ አይሁዶችን ማካተቱ ትክክለኛ ድብቅ ዓላማውን ሳይገልጥ ከጎኑ እንዲያሰልፋቸው ረድቶታል፡፡ በሚገርም ሁኔታ የዛሬዎቹ ሙስሊም አቀንቃኞች እና ሊቃውንት የመዲናን ቻርተር እንደ እስልምና ሕብረ ብሔራዊነት ብዙሃነት እና ሙስሊም

---

[57] http://www.al-eman.com/Islamlib/viewchp.asp?BID=249&CID=30 and http://sirah.al-islam.com/Display.asp?f=msr10064

ያልሆኑ ሰዎች በመካከላቸው ተቀባይነት የማግኘታቸው ማሳያ አድርገው ይጠቀሙታል፡፡

የአይሁድ ሽማግሌዎች ቻርተሩን በአደባባይ መደገፋቸው ከቁረይሾች ጋር ጠላትነት ውስጥ መግባታቸውን ያመለክታል፡፡ ያ ሳይሆን ቢቀር ግን መንታ የሆነ ሕይወት ይኖራቸው ነበር ምክንያቱም ካልሆነ ይሆናል/ካልሆነ ግን የሚል አይነት ሁኔታ ነበርና፡፡ ኋላ ላይ ግን በንግዳቸው እና በሌሎች ስልታዊ ጥቅሞቻቸው ምክንያት ከቁረይሽ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለማደስ ይገደዳሉ ወይንም ደግሞ ለመተጋገዝ የነበራቸውን ስምምነት ይመልሳሉ፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ በመሐመድ ስር ከሙስሊሞች የደረሰባቸውን የጭካኔ ተግባር ለማፅደቅ ሊውል ነው፡፡ ይህ አንዳቸውን ከሌላቸው በማከታተል በአይሁድ ጎሳዎች ላይ የደረሰ ነገር ነበር፡፡

ግልፅ የነበረው እውነታ መሐመድ ገና ያስሪብ ከመድረሱ በፊት የአይሁዶች እጣ ፈንታ የተወሰነ መሆኑ ነበር፡፡ ይህ የመሐመድ “ምሳሌ” ማለትም የእርሱ ሱና  የሙስሊም ስደተኞቹ አቅም በጎለበተ መጠን እስላማዊ ያልሆኑ አስተናጋጅ ማሕበረሰቦችን የሚጠብቃቸውን እጣ ፈንታ ወስኖ ያስቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡ የጊዜ ጉዳይ ሊለያይ ይችላል ነገር ግን የመጨረሻ ግቡ የታወቀ ነው፡፡

***ግቦቹን ማስቀመጥ***

እንደምንመለከተው በመካ ሳለ ተልዕኮውና የተከታዮቹ እምቅ አቅም እንደተገደበ ለመሐመድ ግልፅ ሆኖለት ነበር፡፡ እስላማዊ ከሆነ መንግሥት እስላማዊ ማሕበረሰብ በማቋቋም እነዚህ ሁለቱ ነገሮች የተፅዕኖ አድማሱን ማስፋት ወደሚያስችሉበት አካባቢ መሄድ አስፈልጎት ነበር፡፡ የያስሪብን ስልታዊ አቀማመጥ በውስጧ የሚገኙትን አይሁዶች እና ያካበቷቸውንም ኃብቶች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ነበር፡፡ ያስሪብን የሚቆጣጠራት ከሆነ ተልዕኮውን ያፋጥንለታል፡፡ ስለዚህ በውጪ ለአይሁዶች ዋስትናን ሲሰጥ ነበር በውስጥ ግን ጥፋታቸውን ሲያቅድ ነበር፡፡ ለሀይሣም እና ከያስሪብ ለመጡት ልዑካን ስለ ታማኝነቱ ቃሉን በሰጠ ጊዜ ይህ ነጥብ ግልፅ ሆኗል፡፡

## *ተቃርኖዎቹ እንዳሉ ሆነው ሥልጣኑን ለማደላደል የተጠቀመባቸው ስልቶች*

በዚህ ጊዜ መሐመድ መገለጥ ርምደታዊ መሆኑን ለተከታዮቹ ማሳመን ችሎ ነበር፡፡ ምንም ትርጉም የማይሰጡ ሁለት አስተምህሮዎችንም ማስተዋወቅ ችሎ ነበር፡ መገለጥን በመገለጥ መሻር እና *ታቂያ/ ሙደራት፡፡* በነዚህም አስተምህሮዎች በመጠቀም ተከታዮቹን ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው ማንቀሳቀስ ችሎ ነበር፡ አይሁድ የተመረጡ ህዝቦች እና የመጽሐፉ ሰዎች ናቸው ከሚለው የጥጃ አምላኪዎች እና በሙሴ ላይ ያመፁ ናቸው ወደሚለው፡፡ ስለዚህ አሁን አይሁዶች ከአላህ ጋር በጠላትነት ውስጥ ነው ያሉት

ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬ እንኳ ሁሉም አይሁዶች ልክ እንደ አባቶቻቸው ተቆጥረዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የአላህ እና የመልእክተኛው ጠላቶች በመሆናቸው የአማኞች የግል ጠላቶች ናቸው ማለት ነው፡፡ በሙስሊም አስተሳሰብ መሰረት አይሁዶችን መዋጋት ግድ ነው እነርሱን ሙሉ በሙሉ ከመደምሰስ ውጪም ሌላ አማራጭ የለም፡፡

## *ጠንካራ መሰረተ ልማቶችን መመስረት*

የመስጊዶችን አስፈላጊነት ለማሳየት መሐመድ ልክ እንደ ደረሰ የገዛ ቤቱን እንኳ ሳይሰራ አንድ መስጊድ ሰራ፡፡ በሚገርም ሁኔታ በመካ አገልግሎቱ ለ 13 ዓመታት ያህል ቢዘልቅም ነገር ግን በዚያ አንድም መስጊድ አልገነባም፡፡ ይህ አዲስ ነገር ነበር፡ የሥልጣን አዋጅ ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መስጊድ ለፀሎት እና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለብዙ አገልግሎቶች ሊውል አለው፡፡ መስጊድ፡

1. ለሙስሊም ማህበረሰብ ማዕከላዊ ነገር ነው፡፡
2. ማህበራዊ እንዲሁም ኃይማኖታዊ ሕንፃ ነው፡፡
3. ፍርድ ቤት እንዲሁም የመማርያ ክፍል ነው፡፡
4. ወታደራዊ እንዲሁም የሚስዮን ጣብያ ነው፡፡
5. የሹመት እንዲሁም የፍርድ ቦታ ነው፡፡

በእርግጥ መሐመድ የመዲናን መስጊድ በመገንባት ኋላ ላይ ባመጣው መገለጥ የፀሎት መጥሪያ ቀንደ መለከቶቻቸውንና የቤተ

ክርስቲያን ደውሎቻቸውን ዝም በማሰኘት አይሁዶችና ክርስቲያኖችን የማዋረጃ መሳርያ የሆነውን የፀሎት ጥሪን አስተዋውቆ ነበር፡፡

ዛሬ መስጊዶች በሁሉም ትልልቅ ከተሞች፣ ትንንሽ ከተሞች እና መንደሮች ውስጥ ብቅ ብቅ በማለታቸው ሳብያ የአውሮፓ፣ የሰሜንና የደቡብ አሜሪካ መልክዓ ምድራዊ ገፅታዎች በፍጥነት እየተለወጡ ናቸው፡፡ መስጊዶች በተለይም የእስላማዊ ሥነ ሕንፃ የሚባለውን ተከትለው አንዴ ከተገነቡ የእስላማዊ *ታምኪን* (ማደራጀት) እና ዲዳድ (መባዛት) አካል ይሆናሉ፡፡ የዝግጅት ውጤት የሆነው የቁጥራቸው መበራከት ተጨባጭ እውነታ ነው!

የመሐመድን አደራ ምሌነት መከተል በእስልምና የበላይነት የሚደመደሙ አምስቱን መርሆች መከተል ነው፡፡ ይህም የሚሆነው በመሰባሰብ፣ በማዳመጥ፣ በመታዘዝ፣ በመሰደድ እና *በጂሃድ* ነው፡፡ በነዚህ አምስት መርሆች ወይንም መንገዶች እስልምና በአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መስረፅ ይችላል፡፡

# *ከመሐመድ ስደት የተወሰዱ የተምኪን እና የኢዳድ ትምህርቶች*

የእስልምናን ስደት እና ተያያዥ የሆኑ ልዩ ልዩ ትምህርቶችን (*ተምኪን፣ ዒዳድ፣ ተይሲር፣ ደሩረዐ* እና *ታቂያ* ወይንም *ሙደራትን* የመሳሰሉትን) ከግምት ውስጥ ካስገባንና ከተረዳን እንዲሁም መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረገውን ስደት፣ የመረጃ አስተላላፊዎቹን አደረጃጀት እና ከአይሁዶች ጋር ያደረገውን ቀድሞ የታሰበበት ውል ከተመለከትን ዘንዳ  አሁን ያሉትን የሙስሊም ማሕበረሰቦች እና በምድረ አውሮፓ ልብ *በሸሪኣ* የሚመራ እስላማዊ ሕብረተሰብ ለመመስረት እያደረጉ ያሉትን ጥረት

ለማነፃፀር ዝግጁዎች ነን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ስደት የመጨረሻ ግቡ ወረራ እንጂ ስደት አይደለም፡፡

### *መስጊዶች*

በሕዝባዊ አመለካከት መሰረት መስጊድ እንደ አምልኮ ቦታ ብቻ ይታያል ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እንደዚያ እንዳልሆነ አይታወቅም፡፡ መስጊዶች ብዙ ጊዜ በመኖርያ ቤት ውስጥ ይጀመራሉ ከዚያም ወደ መጋዘን ወይንም አንዳንዴ ምናልባት ወደ ኪራይ ቤት ይሸጋገራሉ፡፡ ከዚያም ሕጋዊ ፈቃድ ያለውን ሕንፃ እንደ መስጊድ ለመጠቀም ፈቃድ ይጠየቃል፡፡ ከዚያም ለመስጊድ ተብሎ የተሰራ ሕንፃ ይከተላል፡፡ አንዴ መስጊድ ከተገነባ ከዚያም መስጊዶች እንደ እንጉዳይ መብቀላቸውን ይቀጥላሉ እናም በዲሞክራሲያዊ ማሕበረሰብ መካከል ያንን የማስቆምያ መንገድ የለም፡፡ መስጊዶች በማሕበረሰቡ ውስጥ ዋና ነገሮች ናቸው፡፡ ለየትኛውም የሙስሊም ማሕበረሰብ እድገት መስጊዶች እጅግ ወሳኝ መሰረተ ልማቶች ናቸው፡፡ መስጊድን መገንባት የመሐመድን ምሳሌነት የመከተያ ስልት ነው፡፡

በእርግጥ ህልውናውን ለማስቀጠል ሙስሊሞች እንዲሰበሰቡ እና በቋሚነት እንዲታደሙ ይጠየቃሉ፡፡ በአቅራቢያውም እንዲኖሩ ይበረታታሉ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ማሕበረሰቡ ይስፋፋል፣ መንገዱንም ተከትሎ ጥቂት ማይሎችን ይዘረጋል፡፡ ከተማው በሙሉ እስላማዊ እስኪሆን ድረስ ተመሳሳይ ዘዴን ይጠቀማሉ፡፡

### *የምግብ ሥርኣቶች*

ብዙ ጊዜ ምግብ ከግምት ውስጥ እንዲገባ ማመልከቻ ይቀርባል፡፡ የምግብ ሥርኣቶችም ሁለቴ ሳይታሰብባቸው በበጎ መልኩ ይታያሉ፡፡ ስለዚህ ለቤተ ሰብ ወይንም ለግል ፍጆታ የሐላል ሥጋ ጥያቄ ይቀርባል፡፡ የአካባቢ እና የማዕከላዊ አስተዳዳሪዎች ብዙ ጊዜ የማይረዱት ነገር ቢኖር የሙስሊም አመጋገብ የግል ምርጫ ሳይሆን *በኢባዳት* (ኃይማኖታዊ ደንቦችና ሥርኣቶች) ስር የሚመመደብ *የሸሪኣ* አካል መሆኑን ነው፡፡ መስጊድም *በኢባዳት* ስር ይመደባል፡፡ *ሂጃብ* እና *ጂሃድም* እንዲሁ፡፡

ነገር ግን ፍቃድ የሚሰጠው የአዲሱን ማሕበረሰብ የምክንያታዊነት፣ የመቻቻል እና ለሕግ የመታዘዝ ባሕርይ ለማሳየት እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ሊቃውንቱ እስላማዊ ጥያቄዎችን ጠለቅ ባለ መልኩ ቢመለከተቱት ኖሮ በቁርአናዊ መመሪያዎች መሰረት ***ሐላል ሥጋ የማያስፈልግ መሆኑን*** ማወቅ ይችሉ ነበር፡፡ ምክንያቱም በሱራ 5፡3 መሰረት የመጽሐፉ ሰዎች ሥጋ ለሙስሊሞች የተፈቀደ ነውና፡

> ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፡፡ የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፡፡ ከምእመናት ጥብቆቹም ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና (ዝሙተኞች) የምስጢር ወዳጅ ያዝዎች ሳትኾኑ ጥብቆች ኾናችሁ መህሮቻቸውን

> በሰጣችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡ ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ፡፡ በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር ይህ የቁርአን ቃል ክርስቲያኖች እና አይሁዶች ያረዱት ሥጋ ለሙስሊሞች እንደተፈቀደ ይናገራል፣ ስለዚህ በሱራ 5፡3 የኛ ሥጋ ለእነርሱ ሐላል የመሆኑን እውነታ ያረጋግጣል፡፡ ኢማሞቻቸው እና ሊቃውንቶቻቸው ይህንን ተመልክተውት ይሆን በማለት የሚደነቅ ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ በእርግጥ አይተውታል፣ ያውቁታልም፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው ሆነ ብለው ችላ ይሉታል፡፡ አሁንም በድጋሜ የተምኪን አስተምህሮ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ውስጥም እስላማዊውን መገለጫ የማስረግ ሥራ ቀስ በቀስ ይሰራል፡፡

ከዒዳድ የዕይታ ነጥብ አኳያ የሐላል ሥጋ ጥያቄ ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ በማሕበራዊ ደረጃ ድምፃቸው እንዲሰማ የሚያደርግ ሲሆን በመንግሥት እና በምግብ ባለሥልጣን ዘንድም እውቅና እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡ በሕጋዊ እና ሃገራዊ ደረጃ ይህ እውቅና ለውጪው ማሕበረሰብ ዝግ መሆንን በማጠናከር በተዘዋዋሪ ራስን የመነጠላቸውን ሁኔታ ያባብሳል፡፡ በእርግጥ የአካባቢው የገበያ አዳራሾች በሐላል ሥጋ አቅርቦት ላይ ነዋያቸውን ቢያፈሱ ለእስላማዊ መገለጫ መንገድ በመጥረግ ሸሪኣ ተቀባይነትን እንዲያገኝ በኋላ በኩል በር ይከፈትለታል!

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ከሙስሊሞች የግል ፍላጎት ወደ ሕዝብ አደባባዮች ይንቀሳቀሳል - ለምሳሌ ያህል ለትምህርት ቤቶች ምግብ የተለያየ *ሥጋ* ማቅረብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሙስሊሞችም ጥያቄዎቻቸውን ከፍ ባለ ድምፅ ባሰሙ ቁጥር ተሰሚነትን ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ቁጥራቸው እየጨመረ ከሚሄዱት የሙስሊም ልጆች የተነሳ የትምህርት ቤቱ የምግብ አዳራሾች ወደ *ሐላልነት* ይቀየራሉ፡፡ እነዚህ የምግብ አዳራሾች በውጪያዊ የምግብ አቅራቢ ካምፓኒ የሚተዳደሩ ከሆነ ሙስሊሞች ያናግሯቸዋል ስለዚህ ለአካባቢው ሆስፒታል፣ ለአካባቢው ማረምያ ቤት እና የአዛውንቶችን ቤቶች ለመሳሰሉት ሕዝባዊ ተቋማት *ሐላል* ምግብ ቢያቀርቡ ከጥቅማቸው ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል፡፡ ለንግድ ተቋማት ትርፍ ቀዳሚው ነገር ነው፡፡

## *ሒጃብ*

ልክ እንደ *ሐላል* ምግብ ሁሉ *ሒጃብም በኢባዳት* ወይንም በኃይማኖታዊ ደንቦች *ሥር* የሚመደብ በመሆኑ በሙስሊም ሊቃውንት እንደታወጀው የእስላማዊው *ሸሪኣ* አካል ነው፡፡ *የሐላል ሥጋ* ውስጣዊ ሲሆን *ሒጃብ* ግን ውጫዊ “በፊት ላይ የሚታይ” የእስላማዊ ማሕበረሰብ አካል ነው፡፡ በእርግጥ *ተምኪን* እና *ጂሃድ* እዚህም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

የሒጃብ ተግባራዊነት ሁል ጊዜም በቀስታ የሚደረግ ነበር፡፡ መጀመርያ እንደ ጭንቅላት መሸፈኛ ይጀምርና ከዚያ የጭንቅላት

መሸፈኛ እና ሰውነትን በሙሉ ወደሚሸፍን ሙሉ ልብስ ይቀየራል፡፡ ከዚያም ሒጃብ መልበስ እና በመጨረሻም ኒቃብ መልበስ ይሆናል፡፡ (ኒቃብ ለዐይን ሁለት ቀዳዳዎች ብቻ ሲቀሩ ፊትን በሙሉ መሸፈን ነው፡፡) ኒቃብ የመልበስ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ሕብረተሰቡ በእርሱ ከመታሰሩ የተነሳ ምንም ዓይነት ተቃውሞ የሚያሰማ ሰው አይኖርም፡፡

### *ሸሪኣ*

መስጊዶች አንዴ ከቆሙ፣ የዳዕዋ ማዕከላት ተቋቁመው መስራት ከጀመሩ፣ የቁርአን ትምህርት ቤቶች *ሥራ* ከጀመሩ፣ *የሐላል* ምግቦች በትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ማረምያ ቤቶች እና በሌሎች ሕዝባዊ ቦታዎች የሚቀርቡ ከሆነ፣ *ሒጃብ* ቦታ ካገኛ ይህ ማለት *የሸሪኣ* ህግ ሙሉ በሙሉ እየተንቀሳቀሰ ነው ማለት ነው፡፡ በሙስሊሙ ማሕበረሰብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን አስተናጋጁንም ማሕበረሰብ በቀጥታ ተፅዕኖ እንዲያሳድርበት ታልሞ የሚሰራ ነው (አባሪ ሁለትን ተመልከቱ)፡፡

የሙስሊሞች ዓመት በኣላት እና ሌሎች በኣሎች በሕዝባዊ የቀን መቁጠርያ ላይ በበዙ ቁጥር የሙስሊሙን ማሕበረሰብ ጥንካሬ ለማሳየት እና መለያቸውን ለማወጅ የአደባባይ ፀሎቶች ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ተግባራት መሐመድ በመዲና ደረገውን ምሳሌነት የሚከተሉ እንደ መሆናቸው መጠን የግድ መደረግ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ይህ እስልምና በፀጥታ የሚጫንበት እና አስተናጋጁን

ማሕበረሰብ ከእስላማዊ ሥነ ሕንፃ፣ አለባበስ እና አመጋገብ ጋር እንዲላመድ የማስገደድ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም ደግሞ አካባቢያቸው መቀየሩን እንኳ ማንም ሰው ሳያስብ የሚደረግ ነው፡፡ ሲጠቀለልም በሸሪአ ስር የሚደረገውን እስላማዊ አስተዳደር ለመመስረት ተግባራዊ ለሚሆነው ኃይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ሥልት ማሕበረሰቡ ግዴለሽ ይሆናል፡፡ ያ የመሐመድ ወረራ ነበረ ዛሬም ደግሞ በሙስሊም ስደተኞች በሁሉም የዓለም ክፍሎች ተግባራዊ የሚደረግ ነው፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጥያቄዎች ማለቂያ አይኖራቸውም፡፡ የእስልምና አቀንቃኞች ለሰላማዊ ሰልፎች መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮችን ይፈልጋሉ፡፡ ጉዳዮቹ ምንም ያህል ከቁብ የማይቆጠሩ ቢሆኑም ነገር ግን ከልክ በላይ ተለጥጠው ሃገራዊ ጉዳዮች ይደረጋሉ፡፡ ይህ ሥልት በብልሃት ስለሚቀነባበር ከአካባቢያዊ እና ሃገራዊ የፖለቲካ መሪዎች እና ፓርቲዎች ዘንድ ድጋፍ ይቸራቸዋል፡፡ በምላሹም የሚሰልሙ የምርጫ ድምፅ እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባላቸዋል፣ ወዘተ.

እያንዳንዱ የአስተናጋጁ ማሕበረሰብ አካባቢያዊ ልማድ የሚፈርስባቸው መንገዶች እና በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለመገዳደር የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በጥልቀት እና በጥንቃቄ ይጠናሉ፡፡ ሙስሊሞች በውስጡ ለመሳተፍ እምቢተኛ ይሆናሉ ወይንም ደግሞ የሙስሊሙን ማሕበረሰብ ልዩነት እና መነጠል ለማሳየት በግልፅ አድማ ይመቱበታል፡፡

በውጪ ሲታይ ነገሩ በእነርሱ ኪሳራ የሚደመደም ቢመስልም ነገር ግን የሚሆነው ተቃራኒው ነው፡ ፍላጎታቸውን ጥንካሬ ባለው መንገድ በማስከበር ይደመድማሉ፡፡

በሁኔታዎች የታሰሩ በቂ ሰዎች ከተገኙ በኋላ መሐመድ ያስሪብን መዲና (የነቢዩ ከተማ) በማለት ስሟን ለወጠ፡፡ ስለዚህ በተለያዩ አካባቢዎች አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ለመለወጥ የተለያዩ እቅዶች ይነደፋሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የመንገዶች ወይንም ደግሞ የዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች ሥሞች አዲስ ሥም ይሰጣቸዋል ማሕበረሰቡም እነዚህን አዲስ ሥሞች እንዲጠቀም ይነገረዋል፡፡ እነዚህ ኦፊሴላዊ አድራሻዎች ከሆኑ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ቅቡል ይሆናሉ፡፡

ቁርአናዊ ትምህርት ቤቶች፣ መስጊዶች እና *የዳዕዋ* ማዕከላት ብቅ ብቅ ሲሉ እስላማዊ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊዎች እንዳልሆኑ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን “ኃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች” የሚባሉቱ እስላማዊውን መለያ በአዲሱ ትውልድ ልብ እና አዕምሮ ውስጥ የሚያሰርፁ ፖለቲካዊ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ህፃናት እና ወጣቶች እንደ ነገ መሪዎች የሚያድጉባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ለማዋል በትምህርት በኩል ራስን መነጠል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

### *ትልቅ ፍንዳታን የሚያስከትል እምቅ አቅም ያላቸው ጉዳት አልባ ለውጦች*

“ሰይጣናዊ ጥቅሶች” በመባል የሚታወቀውን ክስተት ለመቆጣጠር መሐመድ “መገለጥን በመገለጥ የመሻር አስተምህሮን” አምጥቶ ነበር፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው ያስሪብ/መዲና በደረሰ ጊዜ ለአይሁዶች የደህንነትን ስሜት ለመስጠት ፆምን እና ወደ ኢየሩሳሌም ዞሮ መስገድን የመሳሰሉ ኃይማኖታዊ ልምምዶችን ተግብሮ ነበር፡፡

መሐመድ የራሱን መለያ በቦታው ለማቆም አቅምን ባገኘ ጊዜ የአይሁድ ጎሳዎችን ማጥፋቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ የፀሎት አቅጣጫን እንዲሁም ፆምን ከጥቂት ቀናት ወደ ሙሉ የረመዳን ወር ቀይሮ ነበር፡፡ ከላይ ሲታይ ይህ ምንም ጉዳት የሌለው የኃይማኖት ዶግማን ብቻ የሚነካ ጉዳይ ይመስል ነበር፡፡ እውነታው ግን የግንኙነት ለውጥ ማድረግ እና ባለፈው ዘመን ከቁረይሽ ይልቅ ከአይሁድ ጋር ተመሳሳይ መሰረት እንዳለ ያስመሰለውን የማሕበረሰቡን መለያ መለወጥ ነበር፡፡

አዲሱ የሙስሊም ማሕበረሰብ ካዕባ እና አካባቢው የተቀደሰ እስላማዊ አካባቢ መሆኑን ማወቁ የአላህ እና የመልዕክተኛው የመሐመድ ጠላቶች ከሆኑት ከአረማውያን ቁረይሾች እጅ ነፃ ለማውጣት ይበልጥ እንዲነሳሳ አድርጎታል፡፡ አስተናጋጁ ማሕበረሰብ በአረማውያን እንደ ቅዱስ ቦታዎች የሚቆጠሩትን የአረብ አካባቢዎች መቀበል ጀምሯል፡፡ ስለዚህ የፀሎት አቅጣጫን መለወጥ ድብቅ ለሆነ ግብ የተደረገ ውስጣዊ ዝግጅት እና

ከአይሁዶች ጋር ውስጣዊ መለያየት ነበር፡፡ የእነርሱ ቂብላ ወይንም ወደ ኢየሩሳሌም የሆነው የፀሎት አቅጣጫቸው ጊዜያዊ እንደሆነ ከታወቀ በኋላ ከሃዲዎች መሆናቸው ታወጀ፡፡ መሐመድም መካ እውነተኛው አቅጣጫ እንደሆነ አወጀ ምክንያቱም አላህ እራሱ ለአይሁድ በመጻሕፍቶቻቸው ውስጥ ገልጦላቸው ነበርና፡፡ ካዕባን በአላህ ተመርቶ በልጁ በእስማኤል በመታገዝ የገነባው አብርሃም እራሱ ነበር፡

> ሱራ 2፡227 “ኢብራሂምና ኢስማኢልም «ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል፡፡ አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና» የሚሉ ሲኾኑ ከቤቱ መሠረቶቹን ከፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ)፡፡”

በሱራ 2፡125-126 መሰረት በመካ የሚገኘውን ይህንን ቤት ካዕባን እንዲሰራ የእምነት አባት የሆነው አብርሃም እንደተገለጠለት እና እንደታዘዘ መሐመድ ተናግሯል፡

> “ቤቱንም ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ፡፡ ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን፡፡ ኢብራሂም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ጌታዬ ሆይ! ይህንን ጸጥተኛ አገር አድርግ፡፡ ቤተሰቦቹንም ከነሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ሰው ከፍሬዎች ስጠው፡፡ (አላህም) የካደውንም ሰው፤ (እሰጠዋለሁ)፡፡ ጥቂትም

እጠቅመዋለሁ፤ ከዚያም ወደ እሳት ቅጣት አስጠጋዋለሁ፤ ምን ትከፋም መመለሻ! (አለ)፡፡”

ስለዚህ ይህ ለውጥ ትንሽዬ የኃይማኖታዊ ዶግማ ለውጥ አይደለም ነገር ግን መሐመድ በልቡ ውስጥ ባስቀመጠው ነገር ሁሉ ተግባራዊነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድርበት መንገድ ነው፡፡ ይኸውም አይሁዶችን እና ቁረይሾችን በመጨፍለቅ እስልምናን ሙሉ በሙሉ የበላይ ማድረግ ነበር፡፡

እነዚህን ለውጦች ካስተዋወቀ በኋላ በማስከተል የመጣው የበድር ጦርነት ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህ የዝግጅት ሂደት ነበር በአስተምህሮ ማጥመቁም ስኬታማ ነበር፡፡ አሁን የትግበራ ጊዜ ነው፡፡

በአዲስ አካባቢ እና አዲስ ሙስሊም ያልሆነ ማሕበረሰብ መካከል የተለያዩ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ እነዚህ ምናልባት ባሕላዊ ልማዶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ምናልባት በንግግር የማይገለፁ በባሕሉ ውስጥ ጠልቀው የሰረፁ እሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በጣም ቅንነትን የተሞላ በሚመስል መንገድ አንድ በአንድ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል ነገር ግን ይህ የሚሆነው አስተናጋጁን ማሕበረሰብ ከስሩ ለመመንገል እና እስላማዊው ማሕበረሰብ ተረጋግቶ የበለጠ አቅም በማግኘት በአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ላይ የበላይ እንዲሆን የማድረግ ጠንካራ ዓላማ ተይዞ ነው፡፡

***ዒህቲራዝ፡ የቅድመ ጥንቃቄ መርህ***

*ዒህቲራዝ* ማለት መጠንቀቅ፣ በአንክሮ ማጤን እና የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ማለት ነው፡፡ ይህ መርህ ከእምነት ጀምሮ በፀሎት ጊዜ እንኳ ከጠላት የግል ደህንነትን እስከ መጠበቅ ድረስ በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ ላይ የሚተገበር ነው፡፡

> ሱራ 4፡102 "በውስጣቸውም በኾንክና ሶላትን ለእነርሱ ባስገደድካቸው ጊዜ ከእነሱ አንዲት ጭፍራ ካንተ ጋር ትቁም፡፡ መሣሪያዎቻቸውንም ይያዙ፡፡ በግንባራቸውም በተደፉ ጊዜ ከስተኋላችሁ ይኹኑ፡፡ (እነዚህ ይኺዱና) ያልሰገዱትም ሌሎቹ ጭፍሮች ይምጡ፡፡ ከአንተም ጋር ይስገዱ፡፡ ጥንቃቄያቸውንና መሣሪያዎቻቸውንም ይያዙ፡፡ እነዚያ የካዱት ከመሣሪያዎቻችሁና ከጓዞቻችሁ ብትዘነጉና በእናንተ ላይ አንዲትን መዘንበል ቢዘነበሉ ተመኙ፡፡ ከዝናብም የኾነ ችግር በእናንተ ቢኖር ወይም ሕመምተኞች ብትኾኑ መሣሪያዎቻችሁን ብታስቀምጡ በናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ ጥንቃቄያችሁንም ያዙ፡፡ አላህ ለከሓዲዎች አዋራጅን ቅጣት አዘጋጀ፡፡"

ወይንም ደግሞ የሚስትን አመፅ በመጠርጠር ጊዜ፡

> ሱራ 4፡34 "ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፡፡ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን

> ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እነዚያንም ማመጸቸውን የምትፈሩትን ገስጹዋቸው፡፡ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው፡፡ (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዟችሁም (ለመጨቆን) በእነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፤ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡”

ወይንም ደግሞ ከጠላት ጋር በውጊያ ውስጥ ያሉ ሰዎች

> ሱራ 8፡58 “ከሕዝቦችም ክዳትን ብትፈራ (የኪዳኑን መፍረስ በማወቅ) በመተካከል ላይ ኾናችሁ ኪዳናቸውን ወደነሱ ጣልላቸው፡፡ አላህ ከዳተኞችን አይወድምና፡፡”

መሐመድ የትኛውም ተቃውሞ ጠንከር ከማለቱ በፊት በማስወገድ ረገድ በጣም ጠንቃቃ ነበር፡፡ ይህ ሁሉንም ዓይነት ተቃውሞዎች በኃይል የማስወገድ ሁኔታ በቁርአናዊ አስተምህሮ የተደነገገ አካሄድ ነው፡፡ ማንም ሰው እርሱን ቢተች ወይንም ደግሞ ስለ ነቢይነቱ ጥያቄ ቢያነሳ ወይንም ደግሞ በምንም መልኩ ስለ እርሱ ሐሜትን ቢያወራ ቅጣቱ ሞት ነበር፡፡ በእርግጥ ኋላ ላይ ማንም ሰው ነቢዩን እንዳያስቀይም ወይንም ደግሞ ድምፁን ከእርሱ ድምፅ በላይ ከፍ እንዳያደርግ በቁርአን ተደንግጓል፡

> ሱራ 49፡2 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጾቻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ፡፡ ከፊላችሁም ለከፊሉ እንደሚጮህ በንግግር ለርሱ አትጩሁ፡፡ እናንተ የማታውቁ ስትኾኑ ሥራዎቻችሁ እንዳይበላሹ (ተከልከሉ)፡፡”

ነገር ግን በያስሪብ ራሱን ያመቻች በነበረባቸው የመጀመርያዎቹ ጊዜያት መሐመድ ሙሉ ስልጣን ስላልነበረው ጠላቶቹን በፀጥታ ሆኖ በማስወገድ ላይ አተኩሮ ነበር፡፡ ይህንንም ያደርግ የነበረው ጠላቶቹን በአደባባይ የሚገድሉትን ሰዎች በመሸለም ነበር፡፡

## *ተቃዋሚዎችን ማስወገድ*

ኡማኢር ቢን አዲ የተባለን ዐይነ ስውር ሰው በማስጠለል በየዕለቱ የምትመግብ አስማ ቢንት ማርዋን የተባለች አይሁዳዊት ነበረች፡፡ በዐኒሳኢ እና አቡ ዳውድ መሰረት የፍቅር ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን ሁለት ልጆችም ነበሯቸው፡፡ ይህም ሰው ወደ እስልምና ተለወጠ ሴቲቱም መሐመድን ትሰድበው ነበር፡፡ እንደርሱ እንዳታደርግ ቢነግራትም ነገር ግን እርሷ ያንን ማድረግ ስላልተወች ኡማኢር እንድትገደል ፈቀደ፡፡ ስለዚህ አንድ ምሽት በአልጋ ላይ ሆና ልጇን እያጠባች ሳለች ኡማኢር በመምጣት በጀርባዋ እስኪወጣ ድረስ በጦር ሆዷ ላይ ወጋት፡፡ ልጇም እግሯ ስር ወደቀ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ኡማኢር ያደረገውን ለመሐመድ ሲነግረው መሐመድ በአደባባይ አመሰገነው (በኢብን ተይሚያ ገፅ 95-96 ላይ የተዘገበ ሰሪም አል መስሉል ፊ ሰሃቲም ዐረሱል)፡፡

ከዚያም የ80 ዓመት ዕድሜ ባለጠጋ የሆነች ትክክለኛ ስሟ ፋጢማ ቢንት ሩቢያዐ የተሰኘ ኡም ቀረፌ የምትባል ሴት ነበረች፡፡ መሐመድን የሚተች ግጥም በማዘጋጀት ትደግም ነበር፡፡ 13 ወንዶች ልጆች የነበሯት ሲሆን ሁሉም ኀልማሶች እና የአይሁድ ጎሳ መሪዎች

ነበሩ፡፡ መሐመድን በመተቸቷ ምክንያት እግሮቿ በሁለት ግመሎች ላይ ታስሮ እስክትሰነጠቅ ድረስ  በተቃራኒ አቅጣጫዎች እንዲሁዱ ተደረገ፡፡ ይህ ቅጣት በዘይድ ቢን ሐሪት ትዕዛዝ መሰረት በቀይስ ቢን አል ሙሻር ነበር ተግባራዊ የተደረገው (ትራጁም አል አምዐል ባብ ወፈያት፣ ፋታህ አል ባሪ ቢ ሻራህ ቢ ሳሂህ አል ቡኻሪ ኪታብ አል መግሃዚ፣ ባብ ጋዛዋት ዘይድ ቢን አል ሐሪት)፡፡

የ120 ዕድሜ ባለጠጋ የነበረው አቡ አፋቅ በኑ ቁናይቃ የተባለው የአይሁድ ጎሳ መሪ ነበር፡፡ መሐመድ እና ተከታዮቹ ቁረይሾችን እንዴት እንደገደሉ በሰማ ጊዜ ዘመዳሞች አንዳቸው በሌላቸው ላይ ይህንን የሚያደርጉ ከሆነ በሕይወት ውስጥ የቀረ ምንም መልካም ነገር የለም በማለት አስተያየት ሰጥቶ ነበር፡፡ አስተያየቱም መሐመድን እንደመተቸት ተቆጥሮ እጣ ፈንታው ተወሰነ፡፡ አንድ ቀን ምሽትም ተኝቶ ሳለ ሰሊም ቢን ኡማኢር በሰይፍ ወግቶ ገደለው፡፡

በአል ቡኻሪ ፈትህ አል በሪዕ ቅፅ 7 ገፅ 345 ላይ እንደተዘገበው ኢብን አቢ ሐቂካ በአቡ ረፈዓ የተገደለ ሌላ አይሁዳዊ ነበር፡፡ በዚህ ዘገባ መሰረት የተገደሉት ሌሎች ሰዎች ዐነዲር ቢን አል ሐሪዝ፣ ኢቃባ ቢን አቢ ሙዒት፣ አል ሑሪያት ቢን ነቂዝ፣ ኢብን አል ዙባሪ፣ ቀይስ ቢን ዐነመዐን፣ ከዓብ በኒ አል አሽራፍ፣ እያለ መሐመድ እንዲገደሉ የወሰነባቸው ሰዎች ዝርዝር ይቀጥላል፡፡

የቴዎ ቫን ጎስ እና  የሰይጣን ጥቅሶች ተርጓሚዎች ግድያ የጊርት ዊልደርስ እና ሌሎች ሰዎች የግድያ ማስፈራርያ የእስልምናን ተቺዎች እና በዚህ ዘመን ያሉትን ማናቸውንም ተቃውሞዎች ዝም የማሰኘት ትክክለኛ አካል ናቸው፡፡

ጠላት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ሊፈራ አይችልም፡፡ እርሱን ወይንም እርሷን ለማስፈራራት የተወሰነ ቅርበት ያስፈልገዋል፡፡ ስደት ደግሞ ያንን ችግር ይፈታዋል፡፡

ቁረይሾችን በትንንሽ ትንኮሳዎች የማበሳጨት ከዚያም በአቡ ሱፍያን የተመራ ጥቃት በነጋዴዎቻቸው ላይ የመፈፀም ውጤቱ የበድር ጦርነት ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የታሸገው ወረቀት ከዚያ በላይ መሄድ እስከማይችል ድረስ ወደ ውስጥ እየተገፋ እየተገፋ ይሄዳል፤ አስተናጋጁ ማሕበረሰብ ሙሉ በሙሉ በሩን እጅ ይሰጣል ወይንም ደግሞ በማሕበረሰቡ ውስጥ ግጭት ይፈጠራል፡፡

## *የሙስሊም ስደት እና የመሐመድ ምሳሌነት*

መሐመድ በመካ የጀመረውን ለመፈፀም እና ከዳር ለማድረስ ወሰነ፡፡ እነዚህም ተከታዮቹን ጠንከር ባለ እና ፅንፈኛ በማድረግ ማስታጠቅ፣ አዲሱን ኃይማኖቱን አረባዊ መልክ እንዲኖረው ማድረግ፣ አይሁድ ጠላቶቻቸው እንደሆኑ እንዲያስቡ ማድረግ እና ይህም ደግሞ መለኮታዊ ውሳኔ የሆነ ግዴታ መሆኑን ማሳወቅ (*የተምኪን* አስተምህሮ) ናቸው፡፡ አንዴ ከሰፈሩ በኋላ እርሱ እና ተከታዮቹ የመጀመርያዎቹን *የተምኪን* ደረጃዎች ማሰብ ጀመሩ፡፡

ይህ ማሕበረሰቡን የማረጋጋት እና የማስታጠቅ ሁኔታ በቁጥራቸው ቶሎ የማደግ እና በዙርያቸው የሚገኙትን ጠላቶች በረድ እንዲሉ የማድረግ ሁኔታን ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ከቁረይሽ ጋር መጀመርያ በመግጠም በበድር ጦርነት ድልን ካስመዘገበ በኋላ ብዙዎች ተቀላቅለውታል፡፡ ከዝያን ጊዜ ጀምሮ መሐመድ ቁረይሾችን እና ተባባሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ እቅዶችን ማውጣት ጀመረ፡፡

መሐመድ የሥልጣን ተቀረዶችን፣ ጠባቂዎችን፣ ተዋጊዎችን እና ጦርነቶቹን በገንዘብ ለመደገፍ *ዘካትን* አስተዋወቀ፡፡ የጦር ዘረፋዎችን እንደ ምርኮ እና በድንገት የሚመጡትን ጉርሻዎች አዲስ የሰለሙትን ሰዎች ለማስፈንደቅ ይጠቀምባቸው ነበር፡፡ አይሁዶችን አቅም አልባ ወደመሆን አወረዳቸው፡፡ አውስ እና ኻዝራጅም የቀድሞ ጠላታቸው በመዋረዳቸው ምክንያት ደስ አላቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደ ምርጦች እና የአላህ ልጆች ራሳቸውን በመቁጠር ሲኩራሩ የነበሩትን አይሁዶች መሐመድ የዝንጀሮ እና የአሳማ ልጆች እንደሆኑ አወጀ፡፡

> ሱራ 5፡60 “አላህ ዘንድ ቅጣቱ ከዚህ የከፋ ነገር ልንገራችሁን» በላቸው፡፡ (እርሱም) «አላህ የረገመው ሰው በእርሱም ላይ ተቆጣበት፡፡ ከእነርሱም ዝንጀሮዎችንና ከርከሮዎችን ያደረገው ጣዖትንም የተገዛ ሰው (ሃይማኖት) ነው፡፡ እነዚያ በጣም በከፋ

ስፍራ ናቸው፡፡» ከቀጥተኛውም መንገድ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፡፡"

የሙስሊም ማሕበረሰቦች መሐመድን በግላቸውም ሆነ በጋራ እንደ ምሳሌ ለመከተል በሞከሩ ቁጥር ጥያቄዎቻቸው በሙሉ መጀመርያ እንደ ምክንያታዊ ጥያቄዎች ይቀርባሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ የአስተናጋጁን ማሕበረሰብ እሴቶች ለማጣጣል እና እነዚህን እሴቶች ቀስ በቀስ ነገር ግን ስውር በሆነ መንገድ በእስላማዊ እሴቶች ለመተካት ታልሞ የሚደረግ ነው፡፡

# *የስደት አስተምህሮ ታሪካዊ እና ዘመናዊ አተገባበር - የእስላማዊ ጠባይ የሂደት መስመሮች ትንቢያ*

ከላይ የተባለው በመሐመድ የተቀየሰውን እና የተተገበረውን አካሄድ ለአንባቢው ግልፅ ለማድረግ ያህል ነው፡፡ ከታሪክ አንፃር ኋላ ላይ "አላህ የገለጠው" ግዴታ ተደርጎ የተወሰደው የስደት አስተምህሮ በጣም ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ተሰርቶበታል፡፡ ይህም አስቀድሞ በመሐመድ የመጀመርያው ስደት ሲሆን ኋላ ላይም በጣም ወሳኝ በሆኑ አጋጣሚዎች ላይ ነው፡፡ ጥቂት ምሳሌዎች እነሆ፡

1. ከመካ ወደ **አቢሲንያ** (ኢትዮጵያ) በተደረገው ስደት የመጀመርያዎቹ ሙስሊም ስደተኞች መልዕክቱን ወደዚያች ሃገር ይዘው እንዲሄዱ መሐመድ አስታጥቋቸው ነበር፡፡ መጀመርያ ወደዚያ የሄዱት በስደት ምክንያት ሲሆን ጥገኝነት ፍለጋ ነበር፡፡ እኛ ዛሬ "የፖለቲካ ጥገኝነት" የምንለውን ካገኙ በኋላ እነርሱና ልጆቻቸው የራሳቸውን ይዞታ አጠናከረዋል፡፡ እስላማዊ ምንጮች እንደሚናገሩት ንጉሡ፣ የአቢሲንያ ንጉሥ ሰልሟል፡፡ ይህ ግን ማረጋገጫ የለውም፡፡ በዚያች ሃገር ውስጥ የነበረው የሙስሊም ይዞታ ኋላ ላይ ወደ ሰሃራ እና ከሰሃራ በታች ወዳለው አፍሪካ ተስፋፍቷል፡፡ ወደ ቻድ እና አጎራባች ክልሎች መዝለቁም እንደ ትልቅ ምሳሌ ሊነሳ ይችላል፡፡ የቲምቡክቱ ከተማ

ዋና እስላማዊ ማዕከል ሆናለች፡፡[58] በ16ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ የአፍሪካ ክፍሎች በዋናነት በንግድ ምክንያት ሰልመዋል፡፡[59] እስላማዊ ተቋማት በቅኝ ግዛት ዘመን እና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ዛሬ እስልምና በአፍሪካ ውስጥ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየተስፋፋ የሚገኝ ኃይማኖት ነው፡፡ ከ 36 የናይጀርያ ግዛቶች መካከል 12ቱ ሸሪኣን እንደ ህግ የተቀበሉት ሲሆን ሌሎች ግዛቶችም ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ቀስ በቀስ ግፊት እያሳደሩ ናቸው፡፡ በነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የሒጅራ አካሄዶች በጥንቃቄ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የሆነው ሆኖ ሸብር እንዲደረግ ጥሪ ሲቀርብ ሙስሊም ታጣቂዎች ሙስሊም ያልሆኑ አካባቢዎችን በተለይም ደግሞ የክርስቲያን አካባቢዎችን ለማጥቃት ዝግጁዎች ናቸው፡፡ በናይጀርያ እና በሌሎች ሃገራት ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡ እድሎች በሰፉ ቁጥር ስደት (ሒጅራ) እና ጂሃድ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

---

[58] ስለ ቲምቡክቱ የሚያወራውን ይህንን የኢንተርኔት ገፅ ይመልከቱ http://www.islamonline.net/servlet/Satellite?c=Article_C&cid=1201957622312&pagename=Zone-English-News/NWELayout

[59] http://www.islamonline.net/English/In_Depth/MuslimAfrica/articles/2005/04/article01.shtml

2. ማሌዥያን ማስለም መሐመድ ከሞተ ከ42 ዓመታት በኋላ ነበር የተጀመረው፡፡[60] የመጀመርያው የኡመያድ ካሊፋ የሆነው ሙአዊያ ልዑካንን ልኮ ነበር፡፡ ከዚያም ሌሎች ተከትለዋቸዋል፡፡ በግርጌ ማስታወሻነት ከተቀመጠው ድህረ ገፅ ቀንጨብ አድርገን እንጠቅሳለን፡

"እስልምና መጀመርያ ከገባ በኋላ እምነቱ በአካባቢው የእስልምና ሊቃውንት ወይንም ኡላማ ነበር ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ የተስፋፋው፡፡ የተለመደው ልምምዳቸው ለተማሪዎች የማደርያ ጣብያዎች የሆኑ ፖንዶክ ወይንም ጎጆ በመባል የሚታወቁ ኃይማኖታዊ ማሰልጠኛ ጣብያዎችን መክፈት ነበር ... ከተመረቁ በኋላ ተማሪዎቹ ብዙ ጊዜ በሃገሪቱ ሩቅ አካባቢዎች ወደሚገኙ የትውልድ ቀዬአቸው ይመለሳሉ በአንዱና በሌላው ኡላማ መካከል የግንኙነት መስመርም ይፈጥራሉ፡፡"

እዚህ ጋ እንግዲህ እስልምናን ለማስፋፋት በዋናው የእስልምና ኡላማ ቁጥጥር ስር የሚገኙ የእስላማዊ ማዕከላት ትስስር እንዴት እንደተፈጠረ እና ተምኪን እና ሂዳድ ጎን ለጎን እንዴት ተግባራዊ እንደተደረጉ ልብ በሉ፡፡ ማሌዥያ መሐመድ በሞተ በ200 ዓመታት ውስጥ በዋናነት የሙስሊም ምድር ሆነች፡፡ ሙሉ በሙሉ

[60] http://www.cyberistan.org/islamic/mmalay.htm

የሒጅራን አካሄዶች እና አስተምህሮዎች ተግባራዊ በማድረግ ነበር ይህ የሆነው፡፡

3. **ኢንዶኔዥያን** የማስለም እንቅስቃሴ ይህች ሃገር ከ200 ሚሊዮን በላይ ሙስሊሞችን የያዘች 90% ሙስሊም የሆነ ሕዝብ የሚኖርባት ቁጥር አንድ ሙስሊም የበዛባት ሃገር እንድትሆን ምክንያት ነበር፡፡[61] በተጠቀሱት ማጣቀሻዎች ውስጥ የሚገኙ አካሄዶች ድጋፍ ሰጪ በሆኑ ብዙ ጥልቅ ጉዳዮች የሒጅራን አስተምህሮ የተከተሉ ናቸው፡፡ ደራሲው በደቡብ ምስራቅ ኢስያ ያለውን የማስለም እንቅስቃሴ የመጨረሻ ውጤት "ሙሉ በሙሉ ማስለም" በማለት ይገልፀዋል፡፡ ይህም ማለት በፖለቲካ፣ በባሕል፣ በኢኮኖሚ እና በወታደራዊ ረገድ ሙሉ በሙሉ እስላማዊ ማድረግ ማለት ነው፡፡ የተጀመረው በማሌዥያ የሚገኙ የሰለሙ ማሕበረሰቦች እና በምዕራብ ቻይና የሚገኙ ስደተኛ ሙስሊሞች በ13ኛው እና 14ኛው ክፍለ ዘመናት ተሰደው በሄዱ ጊዜ ነበር፡፡ በነዚህ ሁሉ እድገቶች ውስጥ የሚገኙ ቁልፎች ሊተነበዩ የሚችሉ ቅደም ተከተሎችን የያዙ ናቸው፡

[61] R. Michael Feener and Anna M. Gade, "Patterns Of Islamization in Indonesia: A
Curriculum Unit For Post-Secondary Level Educators," Cornell University Southeast
Asia Outreach Program, 1998

**ሀ.** መስጊድ፣ ኢማሞች እና የኃይማኖት መምህራን ያሉትን የእስላማዊ ማሕበረሰብ እምብርት ማቋቋም

**ለ.** የአካባቢውን ማሕበረሰቦች ተፎካካሪ ጎሳዎችን አንድ እንደሚያደርጉ ተስፋን በመስጠት መሳብ ነገር ግን በስተ መጨረሻ በፖለቲካም ሆነ በኃይማኖት ረገድ የሰለሙ የጎሳ መሪዎች ማሕበረሰቡን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሩት ማድረግ

**ሐ.** ወጣቱን ማሕበረሰብ እስላማዊ ትምህርት ቤቶችን (መድረሳዎችን) በማቋቋም ማስተማር፡፡ ይህም የሚያተኩረው ቁርአንን በመሸምደድ፣ አረብኛን በመማር እና አረብኛን የአካባቢው የንግድ እና *በሸሪአ* ላይ የተመሰረቱ ሌሎች ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ቋንቋ በማድረግ ላይ ነው፡፡

**መ.** በኢንዶኔዥያ ደሴት ላይ የሚገኘው የሁሉም እምብርት የሆነው ትንሽ ማሕበረሰብ ዝግጁ ከሆነ በኋላ በተቀረው ማሕበረሰብ ላይ የሸሪአን ህግ ይጭናል እንዲሁም *የጂዝያን* ታክስ ይጥልበታል፡፡ ይህንን የሚቃወም ካለም ኃይልን በመጠቀም ይወገዳል፡፡

**ሠ.** የተረጋጉት የሰለሙት ደሴቶች በሌሎች ደሴቶች ላይ ተመሳሳይ የሆነን አካሄድ ይደጋግማሉ፡፡ የዚህም ውጤት በኢንዶኔዥያ ደሴቶች ላይ የሚኖሩ በሺዎች የመቆጠሩ

ማሕበረሰቦች ሙሉ በሙሉ እስላማዊ እንዲሆኑ አደርጓቸዋል፡፡

**ረ.** በ17ኛው ክፍለ ዘመን ሙሉ በሙሉ የሰለሙት ጃቫን የመሳሰሉት ደሴቶች እጅግ ብዙ የሆኑትን ደሴቶች ወደ እስልምና ለማምጣት ሙሉ የሆነ ወታደራዊ አካሄድን ተጠቅመዋል፡፡

አር ኤም ፊነር እና ኤ ኤም ጌድ (የግርጌ ማስታወሻ 62ን ይመልከቱ) የነዚህን ሁሉ ደረጃዎች ግልፅ የሆነ ገላፃ ሰጥተዋል፡፡ ኢብን ባቱታ ከተባለው ታዋቂ ሙስሊም አሳሽ የተገኘ ዘገባም አቅርበዋል፡፡ በአንደኛው ድምዳሜ ጸሐፍቱ እንዲህ ይላሉ፡

“እስልምና በጣም ብዙ ወደሆኑት የደቡብ ምስራቅ ኢስያ የማላይ ደሴቶች መጥቷል፡፡ በሌሎች የሙስሊም ዓለማት የሚገኙ ሕዝቦች እንደሆኑት ሁሉ አብዛኞቹ ነዋሪዎችም በመስለም ለየት ያለ የሙስሊም ባሕል አካሄዶችን አዳብረዋል፡፡”

4. ዛሬ **በአውሮፓ፣ ካናዳ፣ ዩ ኤስ ኤ እና ላቲን አሜሪካ** ውስጥ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የማስለም ጥረቶችን እየታዘብን እንገኛለን፡፡ እነዚህ ሁሉ ዋነኛ የክርስትና አምባዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ቅንነትን የተሞሉ ከሚመስሉት ቀስ በቀስ ሸሪአን የማስተዋወቅ አካሄዶች ውጪ (ሂጃብ፣ ምግቦች፣ ለሙስሊሞች በትምህርት ቤቶች እና በሥራ ቦታዎች የተለዩ

መመርያዎች፣ የቤተ ሰብ ህግ ወዘተ.) ጥንቃቄን በሚሹ ተቋማት ውስጥ የተምኪንን ትግበራ እየታዘብን ነው፡

(i) በምዕራብ የሚገኙ ከሞላ ጎደል ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሙስሊም ተማሪዎች ማሕበር (ሙተማ) አላቸው፡፡ የሙተማ ድርሻ አዲስ ገቢ ለሆኑት ተማሪዎች "ከቤታቸው ርቀው አዲስ ቤት" የሚያገኙበትን እድል ማመቻቸት ነው፡፡ ከሙስሊም ሃገራት የሚመጡት ብዙ ተማሪዎች የስም ሙስሊም ናቸው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በእስላማዊ አስተምህሮዎች ይጠመቃሉ፡፡ ከዚያም ብዙም ሳይቆዩ በኃይማኖታዊ ውይይቶች እና በዳዕዋ ውስጥ የሚሳተፉ ዋነኛ አቀንቃኞች ይሆናሉ፡፡ ከጊዜ በኋላም ከአካባቢው መስጊዶች ጋር በመተባበር አንዳንድ ተማሪዎች የነውጥ ተግባራትን ጨምሮ የበለጠ ከረር ላሉ ጉዳዮች ይመለመላሉ፡፡ ይህንንም ለማድረግ የማሕበረሰቡ አደራጅ ኢዳድን መተግበር ይኖርበታል ስለዚህ እነዚህን የነውጥ ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችሉ መንገዶች ዝግጁዎች ናቸው እቅዱም አስቀድሞ የተነደፈ ነው፡፡

(ii) በሁሉም ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚገኙ የእስልምና ጥናቶች በኢስላሚስቶች ወይንም

ደግሞ ጠንካራ የሆነ እስላማዊ ስሜት ባላቸው ምሁራን ቁጥጥር ውስጥ ገብተዋል፡፡ ይህም ደግሞ የተሳካው ሊቀ መናብርት ፕሮፌሰሮችን እና የጥናት መርሐ ግብሮችን በገንዘብ በመደጎም ነው፡፡ አሁንም ይህ የተምኪን አካል ነው፡፡ በመሰረቱ ዛሬ የትኛውም የማስተርስ ወይንም የፒ ኤች ዲ የጥናት ወረቀት ከተወሰኑ መመርያዎች ጋር የሚጣጣም መሆን ያስፈልገዋል፡፡ ዛሬ በትምህርቱ ዓለም የቁርአን ጽሑፋዊ ምርመራ እና ነውጠኛ በሆነው እስልምና ላይ የተሰራ ትክክለኛ ዳሰሳን የመሳሰሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለማጥናት የተደረገ ምንም ዓይነት ጥረት አለመኖሩ የሚያስገርም ነገር ነውን? በእርግጥ መርሐ ግብሮቻቸው 100% በሙስሊም ሃገራት የገንዘብ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ምሁራን እየተመለከትን ያለነው በእስልምና ስም እየተደረገ ያለውን ማፅደቅ እና በእርግጥም የትኛውንም መሰረታዊ የሆነ የእስልምና አስተምህሮ ሳያመቻምቹ እስልምና በምዕራባዊ አዕምሮ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማስተዋወቅ ነው፡፡ በእስልምና ላይ ምንም ዓይነት ከረር ያለ የጥናት ሥራ እንዳይሰራ ምሁራዊ የሆነ ከለላ አላ፡፡ ይህም በእነዚህ መርሐ

ግብሮች በኩል እርሱን በማስፋፋት እና በማስተዋወቅ ጥረት የታገዘ ነው፡፡

5. በኢኮኖሚው ክበብ በ 1960ዎቹ እስላማዊ አሳቢዎች አዲስ የሆነ "የእስላማዊ ባንክ እና ፋይናንስ" ሥርኣት መዘርጋት እንደሚቻል ተረዱ፡፡ ይህም ደግሞ ሙሉ በሙሉ "ኡሱሪ"ን በሚከለክል የሸሪኣ ህግ የሚመራ ነው፡፡ "ኡሱሪ" የሚለው ቃል በብድር ጊዜ የሚከፈልን ወለድ የሚከለክል ተደርጎ ይተረጎማል፡፡ በዓለም ዙርያ እንዳለው እንደ ማንኛውም የባንክ ሥርኣት ሁሉም ዋና ዋና የሙስሊም ሃገራት የወለድ፣ ብድር እና ተቀማጭ ሥርኣትን የተከተለ የባንክ ሥርኣት ቢኖራቸውም "እስላማዊ የባንክ ሥርኣት" በከፍተኛ ሁኔት መጥቆ እየወጣ መሆኑን እያየን ነው፡፡ ከተግባራዊ እይታ አኳያ የእስላማዊ ባንክ ሥርኣት መሃንዲሶች አንዳንድ ለየት ያሉ ነገሮችን ቢጨምሩም ነገር ግን መደበኛ የሆነውን የባንክ ሥርኣት ቀድተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው መኪና ለመግዛት ብድር መውሰድ ቢፈልግ እስላማዊው ባንክ መኪና ለመግዛት ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ይህ እንዲሁ ሲታይ "ብድር" ሳይሆን የጋራ ባለቤትነት ነው፡፡ የገዢው የባለቤትነት መጠን ለባንኩ በየወሩ የአቅርቦት ክፍያ በፈፀመ ቁጥር ከፍ እያለ ይመጣል፡፡ አጠቃላይ የአቅርቦት ክፍያው ከመጀመርያው ግዢ ዋጋ መጠን ጋር እኩል

ሲሆን ባንኩ የሚያስከፍለው ኪራይ ደግሞ በመደበኛነት ከሚከፈለው ወለድ ጋር እኩል ነው። ክፍያው ሳይፈፀም ቢቀር ደግሞ ባንኩ መኪናውን ይይዘዋል። ማለትም ገዢው ሙሉ ክፍያውን እና "ኪራዩን" ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ በመኪናው ላይ መብት የለውም ማለት ነው። ነገር ግን እዚህ ጋ ዋናው ጉዳይ ይህ አይደለም። ዋናው ጉዳይ ከእስላማዊ ባንክ ሥርአት ተቋማት ጋር የሚደረጉ ልውውጦች በሙሉ ከእስላማዊ ሸሪኣ ጋር የሚስማሙ እንዲሆኑ የሚፈለግባቸው መሆኑ ነው። ይህም ማለት፡

"እስላማዊ የባንክ ሥርአት በእስልምና ተቀባይነት ባላቸው ሐሳቦች የተገደበ ነው። ይህም አልኮልን፣ የአሳማ ሥጋን፣ ቁማርን፣ ወዘተ. ያጠቃልላል። ስለዚህ ግብረ ገባዊ የሆነ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት ተቀባይነት ያለው ብቸኛው የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት ነው፤ እንዲሁም ግብረገባዊ ግዢም ይበረታታል።"[62]

በግልፅ እንደሚታየው ሙስሊም ስደተኞች እስላማዊ ባንኮችን እንዲጠቀሙ ጫና በተደረገባቸው ቁጥር የተለያዩ እስላማዊ የፋይናንስ መንገዶች ሰፊ የሆነ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ጫና እያሳደሩ ነው። እነዚህን መሳርያዎች

62 http://en.wikipedia.org/wiki/Islamic_banking#History_of_Islamic_banking

መጠቀም የሚፈልጉ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ለአጠቃላዩ የእስልምና ሥርአት የይለፍ ቃል ለሆነው “የእስልምና ግብረ ገብነት” እየተገዙ እንደ ሆነ አያውቁም። ይህም ማለት ለጠቅላላው አስተሳሰብ በንግድ ልውውጥ አውድ ውስጥ በመሆን እየተገዙ ነው ማለት ነው። ብዙ ጊዜ በእስላማዊ የውል ወረቀት ላይ ከድንጋጌው መውጣት የከፋ ቅጣት እንደሚያስከትል ይሰፍራል። በአጭር ቃል ሙስሊም ያልሆኑት ባለ ኃብቶች መሐመድ በ630 ዓ.ም. ለቢዛንታይኑ ንጉሥ ሄራክሊዮስ  የነገረው ነገር በስውር አነጋር ይነገራቸዋል ማለት ነው፡ “እጅ ስጥ (ሙስሊም የመሆን የሚስጥር ቃል) ደህንነትህም የተጠበቀ ይሁን (በአረብኛ *አስለም ቲስለም*)።” እስከ ህዳር 2008 ድረስ የእስላማዊ ሸሪኣ የፋይናንስ ስርኣት 4 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያህል ደርሶ ነበር።

6. በፖለቲካው ክበብ ስደተኞች የሂጅራን አስተምህሮ በተለያዩ መንገዶች ተግባራዊ አድርገዋል። *ተምኪንን* ተግባራዊ በማድረግ “ክፍት የተነጠሉ የከተማ ቦታዎች” (እነርሱ ብቻ የሚገቡባቸው) ብለን የምንጠራቸውን መፍጠር ችለዋል። እነዚህ እስላማዊ የተነጠሉ አካባቢዎች “ክፍት” የተባሉበት ምክንያት ከእነርሱ ሌላ ማንም እንዲገባባቸው የማይፈቅዱ ሆነው ሳሉ እነርሱ ግን ወደ ሌላው ህብረተ ሰብ ለመድረስ ነፃነት ስላላቸው ነው።

ከዚህ አንፃር እነዚህ ቦታዎች እየሰፉ የሚሄዱ ናቸው (በማሌዥያ የሆነውን የሚናገረውን ማጣቀሻችንን ልብ በሉ)፡፡ የበለጠ የተማሩት እና ባለ ፀጋ የሆኑት ሙስሊም ስደተኞች እነዚህን የተከለሉ ቦታዎች ያሰፋሉ ነገር ግን ይህንን የሚያደርጉት ከአስተናጋጁ ማሕበረ ሰብ ጋር የግንኙነት መስመሮችን ለመፍጠር ነው፡፡ እነዚህ የግንኙነት መስመሮች በሙብት አስከባሪ ድርጅቶች፣ በምርምር፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በኃይማኖት ማሕበራት ድርጅቶች፣ ወዘተ. መልክ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሒዳይ በአብዛኛው ተፈፃሚ የሚሆነው በአብዛኛ በተከለለው ቦታ ነው፡፡ ይህም የመስጊዶች መረብ እና እስላማዊ ማዕከላት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ እና የተለያዩ የነውጥ ተግባራትን እንዲፈፅሙ በአስተምህሮ የተጠመቁ ቡድኖችን የሚያስታጥቁበት ቦታ ነው፡፡ በማስለም ሂደቱ ውስጥ እዚህ ደረጃ ላይ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያነጣጥረው በሁለት ግቦች ላይ ነው፡ (1) ከሙስሊሞች እና ሙስሊም ካልሆኑት በእስልምና ላይ የሚነሳን ማንኛውንም ዓይነት ሂስ ዝም ማሰኘት እና (2) የሸሪኣን ህግ በዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በገንዘብ እና በትምህርት ሴክተሮች የሚደረግ የድጋፍ ሂደት እነዚህን ግቦች ለመምታት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡

# ማጠቃለያ

እስልምና በምዕራቡ ዓለም እንዳለው መረዳት መሰረት ኃይማኖትም እምነትም አይደለም፡፡ በኃይማኖት ካባ የተሸፈነ የተከታዮቹን ሁሉንም የሕይወት ገፅታ የሚነካ ሁሉን አቀፍ የሆነ ፖለቲካዊ ሥርኣት ነው፡፡

ስለዚህ ሙስሊም ስደተኞች የሃገሬውን ሰው መምሰልን እምቢ ሲሉ እና መቀላቀልን ሲቃወሙ በኃይማኖት መልክ የሚገለጥ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉንም ጥያቄዎች ከማሕበረዊ-ፖለቲካዊ አቅጣጫ መመርመር ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ አንፃር አስፈላጊ ነው፡፡ ምክያቱም እያንዳንዱ እስላማዊ አስተምህሮ ነባር የሆነውን ሥርኣት በመቀልበስ በሁሉም ረገድ ለመቆጣጠር፣ ለመግዛት እና የበላይ ለመሆን የታለመ ፖለቲካዊ መመርያ ነውና፡፡

ሁሉም ስደተኞች በተለይም ሙስሊሞች የሚከተሉትን ነገሮች ለመፈፀም ቅጣት እና ተጠያቂነትን የሚያስከትል የግዴታ ቃል የመፈረም ግዴታ ሊጣልባቸው ይገባል፡

**ሀ.** በሃገሪቱ ህግ ለመተዳደር

**ለ.** ከአስተናጋጁ ማሕበረሰብ ጋር ለመቀላቀል እና ለመመሳሰል የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ

**ሐ.** ኃይማኖትን በነፃ ፈቃድ ላይ እንደተመሰረተ የግል ጉዳይ ለመቁጠር

**መ.** በሁሉም አቅጣጫ ፆታዊ እኩልነትን ለመቀበል

**ሠ.** አድኋዊ እና ነውጠኛ የሆኑት የሸሪአ አስተምህሮዎች በዚህ ዘመን ተግባራዊ ሊደረጉ የማይችሉ እና የማይሰሩ መሆናቸውን ለመቀበል እና በዚያ መልኩ ለማየት

**ረ.** የሁሉንም ሙስሊሞች እና ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እኩልነት ለመቀበል

**ሰ.** የመንግሥት እና የኃይማኖትን ልዩነት ለመቀበል

**ሸ.** ማንኛውም ሰው ከዘመዶቹ ወይንም በውልደትም ሆነ በማንኛውም መንገድ አባል ከሆነበት ማሕበረሰብ የተለየ ኃይማኖት የመምረጥ መብቱን ለማክበር እና ለመቀበል፡፡

# አባሪ – ሀ

## እስላም ጥያቄና መልስ

በሚከተሉት ገፆች ውስጥ ስመ ጥር ከሆነው www.islamQA.com ከተሰኘ እስላማዊ ድህረ ገፅ ላይ የተወሰዱ ጥያቄና መልሶችን እንዘረዝራለን፡፡ ይህ ድህረ ገፅ ዋና ዋና ከሆኑት እስላማዊ ሊቃውንት (ኡላማ) መልስ በሚሹ ሙስሊሞች በተደጋጋሚ ይጎበኛል፡፡ እዚህ ጋ የተጠቀሱት ነገሮች ቀደም ሲል ለማብራራት ከሞከርነው *የሂጅራ* አስተምህሮ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል በድህረ ገፁ ላይ በተቀመጠው ሁኔታ ዋናውን ጭብጥ እናስቀምጥና ከጭብጡ ጋር በተያያዘው አስተምህሮ ላይ የተሰጠውን የኛን አስተያየት እናስከትላለን፡፡

islam Question & Answer

www.islamQA.com

***ጭብጥ 1፡ ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት መቼ ነው የሚፈቀደው? የግድ አስፈላጊ በሆነ ሰዓት ነው ከተባለ የግድ አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንዴት ነው የምንተረጉመው?***

የኛ አስተያየት፡ ይህ ጭብጥ ከደሩርአ አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

የአንባቢ ጥያቄዎች፡ ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት ትክክል የሚሆነው መቼ ነው? የግድ አስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ከሆነ በዚህ ሁኔታ የግድ አስፈላጊ የሆነ ነገር እንዴት ነው የሚተረጎመው?

በእስልምና ሊቅ የተሰጠ መልስ፡

*ተውሪያህ* የሚለው የአረብኛ ቃል [እዚህ ጋ ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት ተብሎ የተተረጎመው] ማለት አንድን ነገር መሸሸግ ማለት ነው፡፡

አላህ እንዲህ አለ፡

“የወንድሙንም ሬሳ እንዴት እንደሚሸሽግ ያሳየው ዘንድ አላህ መሬትን የሚጭር ቁራን ላከለት፡፡ «ወይ እኔ የወንድሜን ሬሳ እሸሽግ ዘንድ እንደዚህ ቁራ ብጤ መኾን አቃተኝን?» አለ፡፡ ከጸጸተኞችም ኾነ፡፡” አል ማኢዳ 5፡31

“የአዳም ልጆች ሆይ! ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፡፡ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው፡፡ ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው፡፡ ይገሠጹ ዘንድ (አወረደላቸው)፡፡” አል አዕራፍ 7፡26

ለምሳሌ አንድ ሰው “ዲርሃም በኪሴ ውስጥ የለኝም” ቢል ምንም ገንዘብ የሌለው ተደርጎ ይወሰዳል ነገር ግን እርሱ ያለው ከዚያ የተለየ ነው፡፡ ይህም በሸሪኣ አባባል አንድ ሰው ለአድማጩ ሊናገረው የፈለገው ሌላ ሆኖ አድማጩ ግን በተለየ መንገድ የሚረዳው ንግግር ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሰውየው ዲርሃም ሊኖረው ይችላል ነገር ግን አነጋገሩ ምንም ዲርሃም የሌለው ያስመስለዋል፡፡ ይህ አሻሚነት ወይንም ግልፅነት ማጣት ይባላል፡፡

አንድ ሰው እራሱን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቢያገኝ ለምሳሌ የሆነ ነገር ተጠይቆ እውነቱን መናገር ባይፈልግ እና መዋሸትም ደግሞ ባይፈልግ ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት የተፈቀደ ነው፡፡

ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት ለሸሪኣ የሚጠቅም ከሆነ የተፈቀደ ነው ነገር ግን እንደ ልማድ ሁል ጊዜ መጠቀም ወይንም ደግሞ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይንም ደግሞ አንድን ሰው መብቱን ለማሳጣት ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፡፡

አል ናዋዊ እንዲህ አለ፡

ሊቃውንት እንደሚናገሩት ከምናታልለው ሰው የበለጠ ትክክለኛ የሆነን የሸሪኣ ጥቅም የሚያገለግል ከሆነ ወይንም ደግሞ ያለ ውሸት ሊገኝ ለማይችል ነገር ከሆነ ሆን ብሎ አሻሚ መሆን ምንም ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን ምንም ጥቅም ከሌለው *መክሩህ* ነው ነገር ግን *ሀራም* አይደለም፡፡ ያልተገባን ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ወይንም ደግሞ የአንድን ሰው መብት ለመከልከል ከሆነ *ሀራም* ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው መመርያ ይህ ነው፡፡ አል-አድህካር ገፅ 380

አንዳንድ ምሁራን ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት ያለምክንያት የሚደረግ ከሆነ *ሀራም* ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡ ይህ በሼኽ አል-ኢስላም በኢብን ተይሚያ ድጋፍ የተቸረው አመለካከት ነው (አላህ በእርሱ ላይ ምህረት ያድርግና)፡፡ አል-ኢክህቲያራት ገፅ 563 ተመልከቱ

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላም እና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነትን እንድንጠቀም የፈቀደባቸው ሁኔታዎች አሉ፤ ለምሳሌ ያህል፡ አንድ ሰው በሕዝብ መካከል እየፀለየ እያለ የራሱን *ውዱ* ከዘለለ በእንዲህ ዓይነት አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ ማድረግ ያለበት ነገር ምንድነው? መልሱ በእጁ አፍንጫውን በመያዝ መውጣት ነው፡፡

የዚህ ማስረጃ በአይሻ የተዘገበው ቃል ነው (አላህ በእርሷ ይደሰትና)፡ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላም እና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ “ከእናንተ መካከል አንዱ በፀሎት ሰዓት

የራሱን ውዱ ከሰበረ አፍንጫውን በመያዝ ይውጣ፡፡” ሱናን አቡ ዳውድ፣ 1114፡፡ እንዲሁም ሳሂህ ሱና አቡ ዳውድ 985 ተመልከቱ፡፡

አል-ቲቢ፡ አፍንጫውን ይያዝ የሚለው ትዕዛዝ አፍንጫው እየደማ እንዳለ በማስመሰል ማለት ነው፡፡ ይህ ውሸት አይደለም፣ ነገር ግን አሻሚነት ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተፈቀደበት ምክንያት በሰዎች ፊት የመዋረድ ስሜት ስለተሰማው ሰይጣን እንዲቀመጥ እንዳያታልለው ነው፡፡ ሚርቃህ አል-መፋቲህ ሻርህ ሚሽካት አል-መሰቢህ 3/18

ይህ ዓይነቱ አሻሚነት የተፈቀደው የሚያዩት ሰዎች አፍንጫው የደማ መስሏቸው እፍረትን ለማስወገድ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሙስሊም ራሱን ወይንም ንፁህ የሆነን ሰው ለመጠበቅ የግድ እውነት ያልሆነን ነገር እንዲናገር የሚያስገድደው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከገባ ከሁኔታው ለማምለጥ ሳይዋሽ ወይንም ኃጢአት ሳይሰራ የሚያመልጥበት መንገድ ይኖራልን?

አዎን፣ አስፈላጊ ከሆነ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ህጋዊ እና የተፈቀደ መንገድ አለ፡፡ ይህም አመሳስሎ መናገር ወይንም በተዘዋዋሪ መንገድ መናገር ነው፡፡ ኢማም አል ቡኻሪ (አላህ በእርሱ ላይ ምህረት ያውርድና) የራሱን ሳሂህ ምዕራፍ “በተዘዋዋሪ መንገድ መናገር ውሸትን ለማስወገድ ጥሩ መንገድ ነው” በማለት ሰይሞታል፡፡ (ሳሂህ አል ቡኻሪ፣ ኪታብ አል አደብ (የሥነ ሥርኣት መጽሐፍ) ምዕራፍ 116)፡፡

አመሳስሎ መናገር ማለት አድማጩ የሚረዳው የተጠጋጋ ትርጉም ያለው ሆኖ ሳለ ነገር ግን ደግሞ በንግግር ደረጃ ትክክል የሆነ እና ደግሞም ከተባለው ነገር እጅግ የራቀ ትርጉም ያለው ማለት ነው፡፡ የሚከተሉት በሰለፍ እና በቀደምት ኢማሞች ጥቅም ላይ የዋሉ እና በኢማም ኢብን አል-ቀይም ኢግሀሣት አል-ለህፋን በሚለው መጽሐፉ ውስጥ የተሰበሰቡ የዚህ ዓይነቶቹ ንግግሮች ምሳሌዎች ናቸው፡

ስለ መሀመድ (አላህ ምህረቱን በእርሱ ላይ ያውርድና) የሚከተለው ተዘግቧል፡ አብሮት መሆን የማይፈልገው አንድ ሰው ቢመጣ ልክ የታመመ በመስመሰል "ጥርሴን፣ ጥርሴን!" ይላል፤ ብሮት መሆንን የማይፈልገው ያ አሰልቺ ሰውም ለብቻው ይተወዋል፡፡

ኢማም ሱፊያን አል-ሠውሪ ወደ ካሊፋህ አል መህዲ ተወስዶ ነበር፡፡ እርሱም ወደደው ነገር ግን መሄድ ፈለገ፤ ካሊፋውም መቆየት እንዳለበት ነገረው፡፡ አል-ሠውሪም ተመልሶ እንደሚመጣ ማለ፡፡ ከዚያም ጫማውን በር ላይ በመተው ሄደ፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላም ተመልሶ በመምጣት ጫማውን ወስዶ ሄደ፡፡ ካሊፋውም ስለ እርሱ በጠየቀ ጊዜ ተመልሶ ለመምጣት በማለው መሰረት ተመልሶ በመምጣት ጫማውን እንደ ወሰደ ተነገረው፡፡

ኢማም አህመድ በቤቱ ውስጥ ተቀምጦ ነበር፡፡ አል-ሚርዋዚን ጨምሮ ጥቂት ተማሪዎቹ ከእርሱ ጋር ተቀምጠው ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች በመምጣት ከቤቱ ውጪ ሆነው አል-ሚርዋዚ ስለ መኖሩ

ጠየቁ ነገር ግን ኢማም አህመድ እንዲወጣ ስላልፈለገ እንዲህ አለ፡ “አል-ሚርዋዲ እዚህ የለም፤ እርሱ እዚህ ምን ይሰራል?” ይህንንም ሲናገር ጣቱን በሌላኛው እጁ መዳፍ ላይ አስቀምጦ ነበር፤ ውጪ የነበረውም ሰው እርሱ እያደረገ ያለውን ነገር አያይም ነበር፡፡

አመሳስሎ የመናገር ወይንም በተዘዋዋሪ የመናገር ሌሎች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡

አንድ ሰው እገሌን አይተሃል ወይ ብሎ ቢጠይቃችሁ እና እናንተም ማየታችሁን ከተናገራችሁ ጉዳት እንደሚያስከትል ከተሰማችሁ “ማ ራዐይቱሁ” ብላችሁ መመለስ ትችላላችሁ፡፡ “ማ ራዐይቱሁ” ማለት በአረብኛ “አላየሁትም” ማለትም ሊሆን ይችላል ወይንም ደግሞ “ሳምባውን አልቆረጥኩትም” ማለትም ሊሆን ይችላል፡፡ ከፈለጋችሁ ደግሞ በልባችሁ ውስጥ እርሱን ያላያችሁበትን ጊዜ እያሰባችሁ እንዳላያችሁት መናገር ትችላላችሁ፡፡ አንድ ሰው እገሌን እንዳታናግሩት ቢያስምላችሁ “ወላሂ ላነ ኡከሉሙሁ” ማለትም አላቆስለውም በማለት መመለስ ትችላላችሁ ምክንያቱም “ከለም” ማለት በአረብኛ “ቁስል” ማለትም ሊሆን ይችላል እንዲሁም “ንግግር” ማለትም ሊሆን ይችላልና፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው የኩፍርን ቃል እንዲናገር ቢገደድ እና አላህን እንዲክድ ቢነገረው “ከፈርቱ ቢል-ላሂ” ማለትም “አጫዋቹን ልጅ እክደዋለሁ” በማለት እንዲናገር ተፈቅዶለታል፡፡ ይህ አባባል “አላህን እክደዋለሁ” ከሚለው አነጋገር ጋር ይመሳሰላል፡፡ (ኢግሃሣት አል-

ለሀፋን በኢብን አል-ቀይም፣ 1/381፣ 2/106-107፡፡ እንዲሁም አመሳስሎ መናገር (መዐሪድ) የሚለውን ክፍል በኢብን ሙፍሊህ የተጻፈውን አል-አደብ አል-ሸርኢያህ ይመልከቱ፣ 1/14)፡፡

ነገር ግን አንድ ሰው እንደዚህ አይነቶቹን ንግግሮች በትልቅ ችግር ጊዜ ብቻ መጠቀም አለበት፡፡ ከልክ በላይ መጠቀም ግን ወደ መዋሸት ሊመራ ይችላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ነገር የተነገረው ሰው እውነቱ እንደርሱ እንዳልሆነ እና ሰውየው ሆን ብሎ አሻሚ እንደሆነ እና አመሳስሎ መናገርን እንደተጠቀመ ካወቀ እንደ ውሸታም ሊቆጥረው ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የአንድን ሰው ተኣማኒነት አጠራጣሪ በማድረግ የግል ክብርን ከመጠበቅ መርህ ጋር ይጣረሳል፡፡

## *ጭብጥ 2፡ አንዲት ሴት እውቀትን ለማግኘት ፊቷን መግለጥ የተፈቀደ ነውን?*

የኛ አስተያየት፡ ይህም ከደሩርዐ አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ ሴቶች ወይንም ልጃገረዶች እውቀትን ለማግኘት ፊታቸውን መግለጥ እንደሚችሉ በቲቪ ላይ ሰምቼ ነበር፡፡ ይህ የትኛው *መድሃብ* እንደሆነ አላስታውስም ነገር ግን ተናጋሪው እንደተናገረው ከሆነ መልእክተኛው (የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ "በእኔ *ኡማህ ፉቀሃ* መካከል ያለው የሐሳብ መለያየት ምህረት ነው፡፡" በተለይ እኔ ተገልጦ ከመሄድ *ሂጃብ* እና *ጀልባብ* ወደ መልበስ መመለስ ከባድ ሆኖ ስላገኘሁት እባካችሁን እንድከተለው ትክክል የሆነውን ንገሩኝ፡፡

በእስልምና ሊቅ የተሰጠ መልስ፡

መጀመርያ፡ "በእኔ *ኡማህ ፉቀሃ* መካከል ያለው የሐሳብ መለያየት ምህረት ነው፡፡" የሚለው ሐዲስ በአስራር አል-መርፉአህ 506 እና ተንዚህ አል-ሽሪአህ 2/402 ላይ እንደተባለው የፈጠራ ሐዲስ ነው፡፡

ሼኽ አል-አልባኒ በአል-ሲልሲላህ አል-ዳኢፍ ዋአል-መውዱህ (ሐዲስ ቁጥር 57) ላይ እንደተናገሩት፡ ምንም መሰረት የለውም፣ ሙሐዲሶች (የሐዲስ ሊቃውንት) ኢስናድ ሊያገኙለት ሞክረው ነበር ነገር ግን አልተሳካላቸውም፡፡

አል-መናዊ እንደዘገበው አል-ሱብኪ እንዲህ ብሏል፡ *በሙሐዲሱን አይታወቅም፤ እኔም ሳሂህ፣ ዳኢፍ ወይንም መውዱ መሆኑን* የሚያሳይ ምንም ዓይነት ኢስናድ ላገኘለት አልቻልኩኝም፡፡

*መህራም* ባልሆኑ ወንዶች ፊት ፊቷን መግለጥ የግድ አስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ለሴት የተፈቀደ አይደለም፡፡ ይህም ሴት ዶክተር ከሌለች ብቸዋን ካልሆነች በወንድ ዶክተር ፊት፣ ወይንም ጋብቻ ሲታቀድ፣ ወይንም በቃዲ (ዳኛ) ፊት ስትመሰክር እና በመሳሰሉት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ አስፈላጊ በሁነው ነገር ብቻ የተገደበ መሆን አለበት፡፡

የሴት ልጅ ሂጃብ ወይንም ኒቃብ እውቀት እንዳታገኝ እንቅፋት አይሆኑባትም፡፡ በመሸፈን እና እውቀትን በመፈለግ መካከል ግጭት እንዳለ ማሰብ ትክክል አይደለም፡፡ በኃጢአት እና ሴት ልጅ ከስርኣት በመውጣት የምታገኘውን እውቀት አላህ አይባርከው፡፡ ሂጃብ በመልበስ የተሸፈኑ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሳይደባለቁ ወይንም ፊታቸውን ሳይገልጡ ዲግሪዎችን እና ሰርተፊኬቶችን ሲያገኙ አይተናል፡፡ ነገር ግን በሰውነታቸው ላይ ትንሽ ልብስ የለበሱ ሴቶች እውቀት ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ አይተናል፡፡ ሥርኣት ማጣት እውቀት የሚያስገኘው እና ሂጃብ ደግሞ እውቀት የሚከለክለው ከመቼ ወዲህ ነው?

ፊትን መሸፈን ለደረሰች ሙስሊም ሴት ግዴታዋ ነው፡፡ ለጥያቄ ቁ. 12525 በተሰጠው ማብራርያ ውስጥ ፊት *ዐውራህ* መሆኑን ታገኚያለሽ፡፡

እውቀትን ለማግኘት ሴት ልጅ ፊቷን መግለጥ ትችላለች የሚለው አመለካከት ትክክል አይደለም፡፡ አላህ የሚስደስተውን ማድረግ ትችይ ዘንድ እንዲረዳሽ እንለምነዋለን፡፡ ጥያቄ በመጠየቅሽ እና ለማወቅ ላደረግሽው ጥረት እንዲባርክሽ እንለምነዋለን፡፡ እኛ የምንሰጥሽ ምክር መቀላቀል ካለባቸው አላስፈላጊ ቦታዎች ራስሽን ጠብቂ የሚል ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ከተናገረው ጥሩ ዜና እንሰጥሻለን፡ “ለአላህ ብሎ ነገሮችን የተወ ሰው አላህ ከእርሱ በተሻለ ነገር ይክሰዋል፡፡” የመጀመርዎቹ ሙስሊም ሴቶች የቀደመውን ኃማኖታቸውን፣ ባሎቻቸውን እና ሃገራቸውን ለእስልምና ብለው ትተዋል፡፡ ሂጃብ መልበስ እነዚህ ሴቶች ካደረጉት ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው፡፡ አንቺ ደስተኛ እንድትሆኚ ለማይፈልጉ ክፉ እና ብልሹ ወንዶች እና ሴቶች ትኩረት አትስጪ፡፡ ትክክለናውን የደስታ እና የሽልማት መንገድ አያውቁምና፡፡

አላህ የበለጠ ያውቃል፡፡

### ጭብጥ 3፡ ወንዶችን በፀሎት ስለምትመራ ሴት የተሰጠ ውሳኔ

የኛ አስተያየት፡ ይህ ከደሩርዐ ጋር የተያያዘ ነው፤ በብዙ ምክንያቶች ሴቶች ወንዶችን በፀሎት እንዲመሩ የማይጠበቅ ቢሆንምን ነገር ግን ሊቃውንት ሴቶች በተለየ ሁኔታ ውስጥ ያንን ማድረግ እንዲችሉ መንገዶችን አድርገዋል፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ ሴቶች በጁምአ እና በሌሎች ጊዜያት ወንዶችን በፀሎት መምራታቸውን በተመለከተ ያለው ውሳኔ ምንድነው?

መጀመርያ፡

አላህ ለወንዶች ልዩ የሆነን ችሎታ ሰጥቷቸዋል፤ ለሴቶችም የተለየ ችሎታን ሰጥቷቸዋል፡፡ ለሴቶች ብቻ የተሰጠውን መፈለግ ለወንድ የተፈቀደ አይደለም፤ ለወንዶች ብቻ የተሰጠውንም መፈለግ ለሴቶች የተፈቀደ አይደለም፡፡ ይህ አይነቱ ፍላጎት አላህ ያስቀመጣቸውን ህግጋት እና ደንቦች መቃወም ነው፡፡

አላህ እንዲህ አለ፡ "አላህም ከፊላችሁን በከፊሉ ላይ በእርሱ ያበለጠበትን ጸጋ አትመኙ፡፡ ለወንዶች ከሠሩት ሥራ እድል አላቸው፡፡ ለሴቶችም ከሠሩት ሥራ ዕድል አላቸው፡፡ አላህንም ከችሮታው ለምኑት፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡" አል ኒሳ 4:32

አል ሰዒዲ (አላህ ምህረት ያርግለትና) እንዲህ አለ፡ አላህ ለሌሎቹ ያደረገውን ነገር እንዳይመኙ አማኞችን ከልክሏቸዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚቻሉ ወይንም ደግሞ የማይቻሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሴቶች በተለየ ሁኔታ ለወንዶች የተሰጠውን ነገር ማለትም አላህ ወንዶችን ከሴቶች ያስበለጠበትን ነገር መመኘት የለባቸውም፡፡ ድኻ የሆነ ሰው ወይንም እጥረት ያለበት ሰው ኃብታም የሆነውን ወይንም ደግሞ ፍፁም የሆነውን ሰው ደረጃ መመኘት የለበትም ምክንያቱም ይህ አጥፊ የሆነው ቅንኣት (ሃሳድ) መገለጫ ነውና… ያም ደግሞ በአላህ ውሳኔ አለመደሰትን ያመለክታልና፡፡

አካላዊ ጥንካሬን በሚፈልጉ እንደ ጂሃድ ወይንም ደግሞ ፀሎትን መምራትን በመሳሰሉ የመሪነት ቦታዎች ላይ መቀመጥን ወዘተ. አላህ ለወንዶች ነው የሰጠው፡፡ እነዚህ የወንዶች ብቻ ስለሆኑ ሴቶች አይመለከታቸውም፡፡

ይህ የሚከተለውን በመሳሰሉ ብዙ ማስረጃዎች ተመልክቷል፡

1. አላህ እንዲህ አለ፡ “ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፡፡ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች ናቸው፡፡” አል ኒሳ 4፡34

አል-ሻፊዒ በአል-ኡም ውስጥ እንዲህ አለ (1/191)፡ ሴት ወንዶችን፣ ሴቶችን እና ወጣት ወንዶችን በፀሎት የምትመራ ከሆነ የወንዶቹ እና የወጣት ወንዶቹ ፀሎት ተቀባይነት አይኖረውም ምክንያቱም አላህ ወንዶችን የሴቶች ጠባቂዎች እና ተቆጣጣሪዎች አድርጓቸዋልና፡፡ የኃላፊነት ቦታ ላይ እንዲቀመጡ አልፈቀደላቸውም ስለዚህ በምንም ሁኔታ ውስጥ መቼም ቢሆን ሴት ልጅ ወንድን በፀሎት እንድትመራ የተፈቀደ አይደለም፡፡

አል ሰዕዲ (አላህ ምህረትን ድርግለትና) እንዲህ አለ፡ ወንዶች በብዙ መንገዶች በሴቶች ላይ ብልጫ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ መሪነት እና ነቢይነት ለወንዶች ብቻ ነው፣ ጂሃድ፣ የዒድ ፀሎትን መምራት እና የጁምዐን ፀሎት መምራትን የመሳሰሉ ብዙ የፀሎት ተግባራት ለወንዶች ብቻ ናቸው፡፡ አለህ በዕውቀት፣ ጥበብ፣ ትዕግሥት እና ታታሪነት አስበልጧቸዋል፡፡ ሴቶች የእነዚህ ነገሮች ተካፋዮች አይደሉም፡፡

2. አላህ እንዲህ አለ፡ “ለእነርሱም (ለሴቶች) የዚያ በእነርሱ ላይ ያለባቸው (ግዳጅ) ብጤ በመልካም አኑዋኑዋር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው፡፡ ለወንዶችም (ጣጣቸውን ስለሚሸከሙ) በእነሱ ላይ ብልጫ አላቸው፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡” አል-በቀራ 2፡228

አል ሰዓዲ (አላህ ምህረትን ያርግለትና) እንዲህ አለ፡ “ ነገር ግን ወንዶች በእነርሱ ላይ ብልጫ አላቸው” ማለት የበላይነት እና መሪነት እንዲሁም በእነርሱ ላይ የበለጡ መብቶች ማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ “ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚ አሳዳሪዎች ናቸው”፡፡ የነቢይነት እና የዳኝነት፣ ፀሎትን መምራት እና ሃገርን መምራት፣ እንዲሁም ሁሉም የሥልጣን ደረጃዎች በወንዶች የተገደቡ ናቸው፡፡

3. አል ቡኻሪ እንደዘገበው (4425) አቡ ባክራህ (አላህ በእርሱ ደስ ይሰኝና) እንዲህ አለ፡ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላም እና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ “ሴትን እንደ መሪ የሚሾም የትኛውም ሕዝብ አይሳካለትም፡፡”

   ይህ ሐዲስ የሚያመለክተው ለሴት የሕዝብን ስልጣን እንድትይዝ እንደማይፈቀድላት እና የአደባባይ ፀሎቶችን መምራት እንደማይፈቀድላት ነው፡፡

4. አቡ ዳውድ (576) እና አህመድ (5445) እንደዘገቡት ኢብን ዑመር (አላህ በእርሱ ደስ ይሰኝና) እንዲህ አለ፡ “ቤቶቻቸው ለእነርሱ የተሻሉ ቢሆኑም ሴቶቻችሁን ወደ መስጊድ ከመሄድ አትከልክሉ፡፡” በሱናን አቡ ዳውድ ውስጥ በአል ባኒ እንደ ሳሂህ ተመድቧል፡፡

   በዐውን አል-መዐቡድ ውስጥ እንዲህ ይላል፡ “ቤቶቻቸውለእነርሱ የተሻሉ ቢሆኑም” ማለት፡ ቢያውቁ

ኖሮ በቤታቸው የሚፀልዩት ፀሎት በመስጊድ ከሚፀልዩት የተሻለ ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ስለማያውቁ ወደ መስጊድ ለመሄድ ፍቃድ ይጠይቃሉ ምክንያቱም በመስጊድ መፀለይ ሽልማቱ የተሻለ እንደሆነ ያስባሉና፡፡ በቤታቸው መፀለይ ለእነርሱ የተሻለ የሆነበት ምክንያት የፊትና አደጋ ስለሌለው ነው፡፡ ያ ሴቶች ጌጣጌጦችን መልበስ ከጀመሩ በኋላ ተረጋግጧል፡፡

5. ሙስሊም (440) እንደዘገበው አቡ ሁራይራ (አላህ በእርሱ ደስ ይሰኝና) እንዲህ አለ፡ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላም እና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ "ለወንዶች የተሻሉት መስመሮች የፊተኞቹ ሲሆኑ የከፉት ደግሞ የኋለኞቹ ናቸው፡፡ ለሴቶች ደግሞ የተሻሉት መስመሮች የኋለኞቹ ሲሆኑ የከፉት ደግሞ የፊተኞቹ ናቸው፡፡"

አል ናዋዊ እንዲህ አለ፡

"የወንዶች መስመር" የሚለው ሐረግ ከእነርሱ መካከል የተሻሉቱ ከፊት የሚሆኑ እና ከእነርሱ መካከል ደግሞ አነስተኞቹ ከኋላ የሚሆኑት ናቸው በሚለው ሊተረጎም ይገባል፡፡ ሁል ጊዜ ደግሞ እንደዚያው ነው፡፡ የሴቶች መስመር በተመለከተ ይህ ሐዲስ የሚናገረው ከወንዶች ጋር ስለሚፀልዩት ሴቶች ነው፡፡ ነገር ግን ሴቶች ከወንዶች ተለይተው ለብቻቸው የሚፀልዩ ከሆነ ለከ እንደ ወንዶቹ

የተሻሉቱ ከፊት የሚቁሙት ሲሆኑ ዝቅተኞቹ ደግሞ ከኋላ የሚቆሙት ናቸው፡፡ ለወንዶችም ለሴቶችም ዝቅተኛው መስመር ማለት የሚያገኙት ዋጋ ዝቅተኛ እንደሆነ፣ በደረጃም ዝቅ ያሉ እና በሸሪኣ ከእነርሱ ከሚፈለገው ነገር የራቁ መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው፡፡

ሴት በቤቷ እንድትፀልይ እና ከወንዶች እንድትርቅ ከተወሰነባት እንዲሁም ወደ ወንዶች በመቅረባቸው ምክንያት ለሴቶች የከፋው መስመር የፊተኛው ከሆነ ሴት ከወንዶች እንድትርቅ ግዴታ የተጣለባት ሲሆን እንደ ኢማም ፀሎት እንድትመራ መፍቀድ ከእስልምና ጋር እንዴት አብሮ ሊሄድ ይችላል?

6. አል ቡኻሪ (684) እና ሙስሊም (421) ሳህል ኢብን ሰዓድ አል ሰዒድ እንደዘገበው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለ፡ "በፀሎት ሰዓት የተዘለለ የሆነ ነገር መኖሩን ማንም ቢያስተውል *ተስቢህ* ይበል ምክንያቱም እንደርሱ ሲያደርግ ትኩረት ይስባልና፤ ማጨብጨብ ግን ለሴቶች ብቻ ነው፡፡"

አል ሐፊዝ እንደተናገረው፡ ሴቶች *ተስቢህ* እንዳይሉ የማይፈቀድላቸው ይመስላል ምክንያቱም በፀሎት ሰዓት ሁል ጊዜ ድምፃቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ ግዴታ ተጥሎቻቸዋልና፡፡ ይህም *ፊትናን* በመፍራት ነው፡፡

ሴቶች ኢማም ስህተት ቢሰራ ድምፃቸው ወንዶች ባሉበት እንዳይሰማ በመናገር እንዳያርሙት ከተከለከሉ እና ነገር ግን በዚያ ፋንታ እንዲያጨበጭቡ ከተፈቀደ በፀሎት እንዲመሩ እና ኩትባን እንዲያስተላልፉ እንዴት ሊፈቀድላቸው ይችላል?

7. ሙስሊም (658) አናስ ኢብን ማሊክ እንደዘገበው ከመልእክተኛው ኋላ ቆሞ ፀለየ፡፡ ከእርሱ ጋርም ሴት አያቱ እና አንድ ወላጅ አልባ ነበሩ፡፡ እንዲህ አለ፡ እኔ እና ወላጅ አልባው ከእርሱ በስተኋላ ቆምን፡፡ አሮጊቷም ሴት ከእኛ በስተጀርባ ቆመች፡፡

   አል ሐፊዝ ይህ የሚያመለክተው ሴት ከወንድ ጋር በአንድ ተርታ መቆም እንደማይገባት ነው፡፡ ይህም ፊትናን ከመፍራት የተነሳ ነው፡፡

8. ለአስራ አራት ክፍለ ዘመናት በዘለቀው የሙስሊሞች ተግባር ውስጥ ሴት ልጅ ጸሎት እንድትመራ ተፈቅዶላት አያውቅም፡፡ ባኣዒ አል-ሰናዒ 2/289

   ከዚህ መንገድ የሚወጣ ሰው የአማኞች መንገድ እየተከተለ አይደለም፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡ “ቅኑም መንገድ ለእርሱ ከተገለጸ በኋላ መልክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምእምኖቹ መንገድ ሌላ የኾነን የሚከተል ሰው (በዚህ ዓለም) በተሾመበት (ጥመት) ላይ እንሾመዋለን፤

ገሀነምንም እናገባዋለን፡፡ መመለሻይቱም ከፋች!” (አል ኒሳ 4፡115)

የሚከተሉት በሊቃውንት የተሰጡ የተወሰኑ አስተያየቶች ናቸው፡፡

በአል-መውሱዐ አል-ፊቅህያ (6/205)፡ ወንዶችን በፀሎት የሚመራ ኢማም ወንድ መሆን አለበት፡፡

ኢብን ሐምዝ በሙረቲብ አል ጃሚአ ገፅ 27 ላ- እንደተናገረው፡ ሴት መሆንዋ እስከታወቀ ድረስ ወንዶችን በፀሎት መምራት አትችልም፡፡ ሴት መሆንዋን ካወቁ ፀሎታቸው ዋጋ ያጣል፡፡

በአል-ሙሀላ (2፡67) ውስጥ እንዲህ ይላል፡ ሴት ወንዶችን በፀሎት መምራት አልተፈቀደም፡፡ በዚህ ላይ በምሑራን መካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ጽሑፉ እንደሚናገረው በፀሎት ሰዓት ሴት ልጅ በወንድ ፊት አቋርጣ የምታልፍ ከሆነ የወንዱ ፀሎት ዋጋ ያጣል፡፡

ሁለተኛ፡

በኢብን ዳውድ 591 እንደተዘገበው ነቢዩ ኡም ዋራቃ ለተባለችው ሴት ወንዶች ልጆችን ያካተተ ቤተሰቧን በፀሎት እንድትመራ ፍቃድ መስጠቱን በተመለከተ ሊቃውንት የተለያዩ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡

1. ሐዲሱ ዳኢፍ (ደካማ) ነው፡፡
   አል-ሐፊዝ በአል-አልኺስ ውስጥ እንደተናገረው (ገፅ 121)፡ ኢስናዱ ማንነቱ የማይታወቀውን አብድ አል-ረህማን ኢብን ኸላድን በውስጡ አኳቷል፡፡
2. ሐዲሱ ራሱ ሳሂህ ቢሆን ትርጉሙ በቤቷ ውስጥ ያሉትን ሴቶች በፀሎት ትመራ ነበር ነው፡፡
3. ያ ለኡም ዋራቃ ብቻ እንጂ ለሌሎች አይደለም፡፡
4. አንዳንድ ሊቃውንት ሴት ፀሎትን መምራት እንደምትችል ለማስረጃነት ይጠቅሱታል ግን የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ ሲባል ደግሞ አል ፈቲሃን በትክክል ማነብነብ የሚችል ወንድ ከሌለ ማለት ነው፡፡ ሀሺያት ኢብን ቃሲም 2/313፡፡ አል-ሙጊሂኒ 3/33 ተመልከቱ፡፡

## *አንድ ሰው ሂጅራን የሚፈፅምበት ምድር ሊኖረው የሚባቸው ለየት ያሉ ነገሮች*

የኛ አስተያየት፡ ይህ *ከተምኪን* (ማስታጠቅ) እና *ኢዳድ* (ዝግጅት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ አንዲት ሃገር እንደ *ደር አል ሀርብ* ወይንም *ደር ኩፍር* (ምቹ ያልሆነ ምድር ወይንም የኩፍር መገኛ) እንድትቆጠር ምን ለየት ያሉ ነገሮች ሊኖሯት ይገባል፡፡

በስልጣን ላይ ያሉ እና ገዢዎች አላህ ባስቀመጠላቸው ገደብ የሚኖሩ እና ሕዝባቸውን በእስላማዊ ሸሪኣ የሚመሩ እንዲሁም ሕዝቡም እስልምና ያስቀመጠባቸውን ግዴታ ከፍፃሜ ማድረስ የሚችሉባቸው ሃገራት እና ግዛቶች *ዳር ኢሰላም* (የእስልምና መገኛ) ናቸው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ምድሮች የሚኖሩ ሙስሊሞች መሪዎቻቸውን ትክክል በሆነው ነገር ሊታዘዙ እና ቅን ሊሆኑላቸው እዲሁም መንግሥታዊ ስራቸውን በትክክል መስራት እንዲችሉ የሞራል እና ተግበራዊ ድጋፍ ሊሰጧቸው ይገባል፡፡ እዚያው መኖር ይገባቸዋል፡፡ ለእነርሱ የተሻለ ወደሆነ የእስልምና አገዛዝ ወዳለበት ቦታ ካልሆነ በስተቀር መሄድ የለባቸውም፡፡ ይህ ከነቢዩ ስደት ጋር ይመሳሰላል፡፡

በስልጣን ላይ ያሉ እና ገዢዎች አላህ ባስቀመጠላቸው ገደብ የማይኖሩ እና ሕዝባቸውን በእስላማዊ ሸሪኣ የማይመሩ እንዲሁም ሕዝቡም እስልምና ያስቀመጠባቸውን ግዴታ ከፍፃሜ ማድረስ

የማይችሉባቸው ሃገራት እና ግዛቶች ደር አል ኩፍር (የክህደት መገኛ) ናቸው፡፡ ይህ ከድል በፊት እንደነበረችው መካ ማለት ነው፡፡ ሕዝቡ እስልምናን የሚከተል ሆኖ ነገር ግን መሪዎች ከአላህ ህግ በተለየ ህግ የሚመሯቸው እና ሙስሊሞች እስልማዊ ልማዶችን የማይፈፅሙባቸው ሃገራት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ግዴታቸው ለድርድር ወደማይቀርቡባቸው በሸሪአ ወደሚመሩ እስላማዊ ቦታዎች መሰደድ ይገባቸዋል፡፡ መሰደድ የማይችሉ ወንዶች፣ ሴቶች ወይንም ህፃናት ብቻ በይቅርታ ይታለፋሉ ነገር ግን በሌሎች ቦታዎች የሚኖሩ ሙስሊሞች ከካፊር ምድር ወደ ሙስሊም ምድር በማምጣት ሊያድኗቸው ይገባል፡፡

> “እነዚያ (ለእምንት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ?» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን?» አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች! ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃኖችም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይምመሩ ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም) እነዚያም አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል፡፡ አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው፡፡” (አል-ኒሳ 4፡79-99)

> “በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፡- «ጌታችን ሆይ! ከዚች ባለቤቶችዋ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን» የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ?”

ነገር ግን የእስልምናን ሥርኣቶች በቤተሰቡ መካከል መፈፀም የሚችል እና በሥልጣን ባሉት ላይ ማስረጃ በማቅረብ መንገዳቸውን በማስለወጥ ተሃድሶን ማምጣት የሚችል በመካከላቸው እንዲቀመጥ ተወስኗል፡፡ ምክንያቱም በመካከላቸው በመቀመጥ መልእክት ማስተላለፍ እና ማደስ ይችላል የሚል ተስፋ ስላለ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ከፈተና እና ከፊትና ነፃ እስከሆነ ድረስ ነው፡፡

አላህ የኃይል ምንጭ ነው፡፡ አላህ ነቢያችንን መሐመድን ይባርከው፡፡

ፈትዋ አል-ለጅናህ አል-ዳኢማህ 12/51

***ጭብጥ 5፡ በለንደን የቦምብ ጥቃት ሳብያ ከደረሰባት ትንኮሳ በኋላ ሂጃቧን ማውለቅ ይገባታልን?***

የኛ አስተያየት፡ ይህ *ከደሩርዐ* (የግድ አስፈላጊ የሆነ ነገር) ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ ሰኔ 7 የደረሱትን የቦምብ ጥቃቶች ተከትሎ ሙስሊም ሴቶች በፅንፈኞች እስከሞት ሊያደርስ በሚችል ሁኔታ ትንኮሳ እየደረሰባቸው ነው፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የምትኖር ሙስሊም ሴት ትንኮሳዎችን ለመከላከል *ሂጃቧን* ማውለቅ ትችላለችን?

በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ *ፈትዋን* ከማወጅ በፊት *ሐራም* የሆነውን ነገር ለመፍቀድ የሚያስችል አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ስለ ነባራዊው ሁኔታ የተሟላ ምስል ማግኘት ያስፈልገል፡፡

እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ አይመስልም፡፡ ነገር ግን ይህ የጥቂት ጅሎች እና ፅንፈኞች ተግባር ነው፡፡ በሃገሪቱ ውስጥም የተለመደ አይደለም፡፡ ከዚህም በመነሳት ሙስሊሞች የጥበቃ መብታቸውን መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡ በሌሎች ተግባርም መጠየቅ የለባቸውም ወይንም ደግሞ የእነርሱ የኩራት እና የመለያ ምልክት የሆነውን ኃይማኖታቸውን ማመቻመች የለባቸውም፡፡

*ሂጃብ* አላህ በሙስሊም ሴቶች ላይ ያስቀመጠው ግዴታ መሆኑን እና በቁርአን እንዲሁም *በሳሂህ ሱና* የተረጋገጠ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የተለያዩ መደቦች እና የአስተሳሰብ አሰላለፎች ቢኖሩም ነገር ግን ኡማ ተስማምቶበታል፡፡ ይህ የትኛውም መደብ የማይቃወመው ኡማው የተስማማበት ጉዳይ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡ "አንተ ነቢዩ ሆይ! ለሚስቶችህ፣ ለሴቶች ልጆችህም፣ ለምእምናን ሚስቶችም ከመከናነቢያዎቻቸው በላያቸው ላይ እንዲለቁ ንገራቸው፡፡ ይህ እንዲታወቁና (በባለጌዎች) እንዳይደፈሩ ለመኾን በጣም የቀረበ ነው፡፡ አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡" (አል-አህዛብ 33፡59)

"ጌጣቸውንም ከእርሷ ግልጽ ከኾነው በስተቀር አይግለጡ፡፡ ጉፍታዎቻቸውንም በአንገትጌዎቻቸው ላይ ያጣፉ፡፡" (አል-ኒሳ 24፡31)

በእምነቱ ትእዛዛት መሰረት ለመኖር ጥረት ማድረግ እና ትእዛዛቱን በመጠበቅ ጌታውን በመታዘዝ ለማስደሰት ጥረት ማድረግ የሙስሊም ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ ማንም በምንም መንገድ ያንን ከማድረግ ሊያስቆመው አይገባም፡፡

ትንኮሳ ስለደረሰባት *ሂጃቧን* ስለምታወልቅ ሴት በሚከተሉት ነጥቦች ጉዳዩን መጠቅለል እንችላለን፡

እምነቷን በግልፅ ልትለማመድበት የማትችልበት ሃገር ውስጥ መኖር ለሙስሊም ሴት የተፈቀደ አይደለም፡፡ ስለዚህም እምነቷን በግልፅ መለማመድ ከማትችልበት ከዝያ ቦታ በሙሉ ነፃነት እምነቷን ወደምትለማመድበት ቦት መሰደድ አለባት፡፡

መሰደድ ካልቻለች በቤቷ ትቀመጥ፡፡ በተለይም ደግሞ የሚንከባከባት ጠባቂ ካላት አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ከቤቷ አትውጣ፡፡

የሚረዳት ሰው ካለ ለመስራት እና ለመማር መውጣት አያስፈልጋትም፡፡ ትምህርቷንም እስከሚቀጥለው ሴሚስቴር ድረስ ማቋረጥ ትችላለች፡፡ ለስራዋም ፍቃድ መውሰድ ትችላለች፡፡ ይህም ሁኔታዎች እስኪረጋጉ ድረስ ነው፡፡

እንድትወጣ አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ እና ትንኮሳ እንደሚገጥማት ከፈራች ምን ዓይነት ትንኮሳ እንደሆነ መለየት ያስፈልጋታል፡፡ መታገስ የምትችለው እንደ ስድብ ወይንም ደግሞ ክፉ አስተያየት ዓይነት ትንኮሳ ከሆነ ሂጃቧን እንድታወልቅ ይፈቀድላታል ማለት አይደለም፡፡ ይህ የአማኝ ሴትን እምነት መፈተን በሚል ርእስ ስር የሚመደብ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡

“ሰዎቹ አምነናል በማለታቸው ብቻ እነሱ ሳይፈተኑ የሚተው መኾናቸውን ጠረጠሩን? እነዚያንም ከእነሱ በፊት የነበሩትን በእርግጥ ፈትነናል፡፡ እነዚያንም እውነት የተናገሩትን አላህ በእርግጥ ያውቃል፡፡ ውሸታሞቹንም ያውቃል፡፡” (አል-አንከቡት 29፡2-3)

ስለዚህ ምንም ዓይነት ትንኮሳ እና ስድብን ለአላህ ብላ መታገስ ይኖርባታል፡፡ ነቢዩ “በፊታችሁ በእስልምና የሚኖር ሰው የሃምሳ ሰማእታትን ሽልማት የሚያገኝበት የመታገስ ጊዜ አለ” በማለት እንደተናገረው አላህ በኃይማኖቱ የሚኖሩትን ሰዎች እንደሚሸልማቸው በልቧ ማሰብ ይገባታል፡፡

ሌላው ትንኮሳን የማሸነፍያ መንገድ ለብቻ ያለመውጣት ነው፡፡ ነገር ግን ጅሉ እንዳይተናኮላት ከጠባቂዋ (ዋሊ) ወይንም ከሰዎች ጋር በመሆን መውጣት አለባት፡፡

መመታት፣ መገደል ወይንም ደግሞ ክብሯን የሚገፍ አይነት ልትቋቋመው የማትችለው ትንኮሳ የሚገጥማት ከሆነ እና የግድ መውጣት ካለባት በዚህ ጊዜ ሂጃቧን መቀነስ (ለምሳሌ ያህል ራስን እና ፊትን ብቻ መሸፈን) የተፈቀደ ነው፡፡ ከአደጋ ሊጠብቃት የሚችለውን ያህል ብቻ ሂጃቧን መቀነስ አለባት ምክንያቱም አስገደጅ ሁኔታ መጋነን የለበትምና፡፡ ወይንም ደግሞ ሙስሊሟ ሴት የሰዎቹ የጥቃት ዒላማ እንዳትሆን ሰዎቹ የለመዱትን የሂጃብ ዓይነት ብቻ  መጠቀም ትችላለች፡፡ ሙስሊም ያልሆኑ ሴቶች በክረምት ጊዜ ከሚለብሷቸው ልብሶች መካከል በሸሪኣ የታዘዘውን የአካል ክፍል መሸፈን የሚችሉ ልብሶችም አሉ፡፡

ሂጃቧን በግድ የምትገፈፍ ከሆነ በፈተና ስላለፈች ትሸለማለች ነገር ግን ችግሩ ካለፈ በኋላ ትክክለኛ ልብሷን መልበስ ይገባታል፡፡

አጥባቂ ባልሆኑት ማሕበረሰቦች መካከል እስላማዊ መለያ እንዳይጠፋ እንዲህ ዓይነቱ ፈትዋ በጥንቃቄ እና እንደየሁኔታው ቀስ በቀስ ሊታወጅ ይገባዋል፡፡

### ***ጭብጥ 6፡ ወደ ካፊር ሃገር ተመልሶ በመሄድ መኖር ይገባዋልን?***

የኛ አስተያየት፡ ይህ እስላማዊ ባልሆነ ሃገር ውስጥ ከመኖር ጠቅላላ ሁኔታ ጋር እና ከሂጅራ ጋር ከተገናኙ ጉዳዮች ጋር ይያያዛል፡፡ እኛ ከተመለከትናቸው ከብዙ ጉዳዮች ጋር ይገናኛሉ፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ እስልምናን በሚያውቁ ብዙ ሙስሊሞች በካፊር ሃገር (አሜሪካ) ውስጥ እንዳልኖር ተመክሬአለሁ፡፡ እኔ በአሜሪካ ውስጥ እድሜ ልኬን የኖርኩ አረብ አሜሪካዊ ነኝ ነገር ግን ከጥቂት ወራት ወዲህ በአረብ ሃገር ውስጥ እየኖርኩ ነው፡፡ ሆኖም ግን እዚህ መኖር አስቸጋሪ እየሆነብኝ ነው (ገቢ ማጣት፣ ቤት ማጣት፣ ወዘተ.) ስለዚህ ወደ አሜሪካ ለመመለስ እያሰብኩ ነው፡፡ በተጨማሪም ሌላው አሳማኝ ምክንያት ለህመምተኛ ሚስቴ ህክምናው የተሻለ እና ነፃ መሆኑ ነው፡፡ እባካችሁን ከሐዲስ እና ከቁርአን የቻላችሁትን ያህል ዘርዘር ያለ መልስ ስጡኝ፡፡ እዚህ እየታገልኩ መኖር ወይንም ደግሞ ወደ አሜሪካ መመለስ ይኖርብኝ እንደሆን አላውቅምና፡፡

ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡

መሰረታዊው መርህ *ከሙሽሪኪን* ጋር በምድራቸው መኖር ክልክል ነው የሚል ነው፡፡ አላህ ለሙስሊም ከእንዲህ ዓይነቱ ሃገር ወደ ሙስሊም ሃገር መመለስን ቀላል ካደረገለት ተመልሶ እንዲሄድ የሚፈቅድለት ምክንያት ከሌለ የተሻለ ከሆነው ዝቅተኛ የሆነውን መምረጥ የለበትም፡፡

የእኛም ምክር ሌሎች እንዳሉህ ሁሉ በሙስሊም ሃገር የሌለን ህክምና ማግኘትን በመሰለ አስገዳጅ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ወደ *ካፊር ሃገር* ተመልሰህ በመሄድ መኖር የለብህም የሚል ነው፡፡

አስተውል፣ ለአላህ ብሎ ነገሮችን ለሚተው ሰው አላህ አላህ ከዝያ የተሻለ ሽልማት ይሰጣል፡፡ አተርፋለሁ ብሎ ለአደጋ ከመጋለጥ ያለንን ንብረት ማስቀመጥ የተሻለ መሆኑንም አስብ፡፡ የሙስሊም ገንዘቡ ኃይማኖቱ ነው፤ ስለዚህ አላፊ የሆነ ዓለማዊ ነገር ለማግኘት ብለህ ለአደጋ አታጋልጠው፡፡

ሼኽ ኢብን ዑሣይሚን (አላህ ምህረት ያድርግለትና) *በካፊር ሃገር* ውስጥ መኖርን በተመለከተ ዝርዝር ፈትዋ አውጀዋል፡፡ ቀጥሎ እንጠቅሰዋለን፡፡

ሼኽ ኢብን ዑሥየሚን እንዲህ አሉ፡

*በካፊር ሃገር መኖር በሙስሊም ኃይማኖታዊ መሰጠት፣ ሥነ ምግባር እና ፀባይ ላይ ትልቅ አደጋ ይጋርጣል፡፡ ብዙዎቻችን ወደዝያ ሄደው ሲመለሱ ከመንገድ ስተው እና ከሄዱበት ሁኔታ የተለየ ሆነው የመጡት ብዙ ሰዎችን እናውቃለን፡፡ ከፉ አድራጊ እና ኃይማኖታቸውን የካዱ ሆነው ተመልሰዋል፡፡ ስለዚህ ራሳችንን ከዝያ ለመጠበቅ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባናል፡፡ ወደ ጥፋት የሚመራውን ይህንን መንገድ እንዳይከተሉ ሰዎችን የሚከለክሉ ሁኔታዎችንም እናስቀምጣለን፡፡*

በካፊር ሃገራት ከመኖር በፊት ሊሟሉ የሚገባቸው ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡

የመጀመርያው ቅድመ ሁኔታ ሰውየው በእምነቱ የፀና፣ በቂ እውቀት ያለው፣ ከእምነቱ ዘንበል እንዳይል አቅም ያለው፣ ለካፊሮች የጠላትነት ስሜት ያለው፣ እነርሱን የሚጠላ እና ከእነርሱ ጋር ጓደኝነትን የማይፈጥር እንዲሁም እነርሱን የማይወድ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ከእነርሱ ጋር ጓደኛ መሆን እና እነርሱን መውደድ ከእምነት ጋር የሚጣረስ ነገር ነውና፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡

“በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡” (አል-ሙጃዲላህ 58፡22)

እንዲሁም እንዲህ አለ፡

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፡፡ አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም፡፡ እነዚያንም በልቦቻቸው ውስጥ (የንፍቅና) በሽታ ያለባቸውን ሰዎች «የጊዜ መለዋወጥ እንዳያገኘን እንፈራለን የሚሉ» ሲኾኑ በእነርሱ

(ለመረዳት) ሲቻኮሉ ታያቸዋለህ፡፡ አላህም ድል መንሳትን ወይም ከእርሱ ዘንድ የኾነን ነገር (ማጋለጥን) ሊያመጣ በነፍሶቻቸው ውስጥ በደበቁትም ነገር ተጸጻቾች ሲሆኑ ተረጋገጠ፡፡" (አል-ማኢዳህ 5፡51-52)

በሳሂህ ውስጥ እንደተዘገበው ነቢዩ (የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ "ሕዝቦችን የሚወድ ሰው ከእነርሱ እንደ አንዱ ነው፡፡" እንዲሁም "ሰው ከሚወደው ጋር ይሆናል፡፡"

የአላህን ጠላቶች መውደድ ለሙስሊሞች አደገኛ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ነው ምክንያቱም ነቢዩ "ሕዝቦችን የሚወድ ሰው ከእነርሱ እንደ አንዱ ነው፡፡" በማለት እንደተናገረው እነርሱን መውደድ አንድ ሰው ከእነርሱ ጋር መስማማቱን እና እነርሱን መከተሉን ያመለክታልና፡፡

ሁለተኛው የእስልምናን ደንቦች መጠበቅ እንዲችል ኃይማኖቱን በግልፅ መለማመድ መቻል አለበት፡፡ መደበኛውን ፀሎት ለማከናወን እና ጁምኣን ከሌሎች ጋር በመሆን ለመፀለይ መከልከል የለበትም፡፡ ዘካትንም ከመክፈል፣ ሐጅ ከማድረግ እና ሌሎች እስላማዊ ሥርኣቶችን ለመፈፀም መከልከል የለበትም፡፡ ያንን ማድረግ ካልቻለ እዚያ መቀመጥ አይፈቀድም ምክንያቱም በዚህ ሁኔታ መሰደድ (ሂጅራ) ግዴታ ነውና፡፡

ሼኽ ኢብን ዑሠየሚን ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት የሚኖሩትን ሰዎች ሲዘረዝሩ እንዲህ አሉ፡

አራተኛው ንግድ እና ህክምናን ለመሳሰሉ የግል ጉዳዮች የሚቀመጡ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ የሚያስፈልጋቸውን ያህል መቀመጥ የተፈቀደ ነው፡፡

ሼኹ በፈትዋው መጨረሻ ላይ እንዲህ አሉ፡

አንድ አማኝ የኩፉር ልማድ በግልፅ እየተፈፀመ እና ሥልጣን የአላህ እና የመልእክተኛው መሆኑ ቀርቶ የሌላ ሲሆን በዐይኑ እያየ እና በጆሮው እየሰማ እንዲሁም እየተስማማ እርሱ፣ ሚስቱ እና ልጆቹ በትልቅ አደጋ ውስጥ ሆነው ኃይማኖታዊ መሰጠታቸው እና ሥነ ምግባራቸው ለአደጋ ተጋልጠው እንዴት መኖር ይሆንለታል?

መጅሙ ፈትዋ አል-ሼኽ ኢብን ዑሠየሚን፣ ፈትዋ ቁ. 388፡፡

### ***ጭብጥ 7፡ ማሕበረሰብ ወይንም መስጊድ በሌለበት የካፊር ሃገር ውስጥ ስለመኖር***

የኛ አስተያየት፡ እንደገና ከሂጅራ አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ሲሆን "መውደድ እና መጥላት" *(አል-ወላዕ ወ አል-በራዕ)* የተሰኘ ተያያዥ አስተምህሮንም ይነካል፡፡

የአንባቢ ጥያቄ፡ አንድ ሙስሊም ለሥራ በሚቀመጥበት *የካፊር ሃገር* እምነቱን በግልፅ ማራመድ ከቻለ ነገር ግን መስጊድ ወይንም የሙስሊም ማሕበረሰብ ከሌለ እዚያ በመኖሩ ኃጢአት እየሰራ ነው ማለት ነው?

ለአላህ ምስጋና ይግባው፡፡

አንደኛ፡

ማስረጃው እንደሚያሳየው *በሙሽሪኪን* መካከል መኖር *ሐራም* ነው፡፡ ከተቻለ *ከካፊር* ሃገር ወደ ሙስሊም ሃገር መሰደድ ግዴታ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡

"እነዚያ (ለእምነት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ?» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን?»

አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች!” (አል-ኒሳ 4፡97)

ነቢዩ (የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) እንዲህ አለ፡ “*በሙሽሪኮች መካከል ከሚኖር ሙስሊም ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም፡፡*” አቡ ዳውድ ዘግቦታል (2645) እንዲሁም በሳሂህ አቢ ዳውድ ውስጥ በአል-ባ *ከሳሂህ* ተመድቧል፡፡

ይህ አጠቃላይ የሆነ መሰረታዊ መርህ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው እስልምናን መለማመድ እስከቻለ ድረስ ለንግድ፣ ለትምህርት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ ነገሮች መሄድ ይችላል፡፡

ነገር ግን እስልምናን በግልፅ ለመለማመድ የማይፈቀድ ከሆነ እዚያ መቆየት *ሐራም* ነው፡፡ ከተቻለ ከዚያ መሰደድ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛ፡

እስልምናን መለማመድ ማለት *ተውሂድን* ማወጅ፣ *ሺርክን* መቃወም እና የእስልምናን ምልክት ያለፍርሃት ማቋቋም ማለት ነው፡፡

ሼኽ መሐመድ ኢብን ኢብራሂም አል-ሼኽ (አላህ ምህረት ያድርግለትና) ስለሐዲሶቹ ትርጉም ተጠይቆ ሲመልስ እንዲህ አለ፡

“*በሙሽሪኮች* መካከል የሚኖር ሰው እንደ እነርሱ ነው” እና “*በሙሽሪኮች* መካከል ከሚኖር ሙስሊም ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም”፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሐዲሶች ከሙሽሪኮች ጋር መኖርን እና

ከእነርሱ ጋር መቀላቀልን አጥብቀው ይቃወማሉ እንዲሁም ያስጠነቅቃሉ፡፡ ከሺርክ ምድር ወደ ሙስሊም ምድር መሰደድም ግዴታ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ ይህ እምነቱን በግልፅ መለማመድ ያልቻለን ሰው ይመለከታል፡፡ እምነቱን በግልፅ ማራመድ የሚችል ሰው የመሰደድ ግዴታ የለበትም፡፡ ነገር ግን እርሱን በተመለከተ *ሙስተሃብ* ነው፡፡ ሆኖም በመካከላቸው የሚኖረው እነርሱን ወደ *ተውሂድ* እና ወደ *ሱና* ለመጥራት ከሆነ እና *ከሺርክ* እና *ከቢድኣ* ሊያስጠነቅቃቸው ከሆነ *ሙስተሃብ* አይደለም፡፡

*ኃይማኖትን* በግልፅ መለማመድ ማለት መፀለይ እና *ሪባ* እንዲሁም *ዚናን* ከመሳሰሉ ሐራም ከሆኑ ነገሮች መራቅን የመሳሰሉ ጥቃቅን *ኃይማኖታዊ* ነገሮችን መፈፀም ማለት ብቻ አይደለም፡፡ *ኃይማኖትን* በግልፅ መለማመድ ማለት *ተውሂድን* ማወጅ እና ከአላህ ጋር ሌሎችን መደበል እንዲሁም *የሙሽሪኮች* መንገድ የሆኑትን ሌሎች *ኩፋሮች* ሁሉ መቃወም መቻል ነው፡፡ ፈትዋ አል-ሼኽ መሐመድ ኢብን ኢብራሂም (1/77)

በዚህ ሁኔታ እምነትን በግልፅ መለማመድ በነዚህ ሃገራት ወይንም ጥቂት ሙስሊሞች ብቻ ባሉበት ለሚኖር ሰው ብዙ ጊዜ የሚቻል አይደለም፡፡

እምነትህን በግልፅ መለማመድ ትችላለህ ብለን እንኳ ብናስብ ከሙስሊሞች ተነጥሎ መኖር በራሱ ባንተ፣ በቤተሰብህ እና በልጆችህ ላይ መጥፎ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ *ኢድሃን* በማይሰማባቸው

እና በማሕበር መፀለይ በማይቻልባቸው ሙስሊሞች *በኩፋር* በሚከበቡባቸው በነዚህ ሃገራት ውስጥ ከመኖራቸው የተነሳ እምነታቸውን፣ ቋንቋቸውን እና እሴቶቻቸውን ያጡ የሙስሊም ትውልዶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡

ስለዚህ ስለ እምነትህ ስትል አካባቢውን እንድትለቅ እና ካንተ ጋር ያሉትን ሰዎች ለመጠበቅ ብዙ ሙስሊሞች ወዳሉበት እንድትንቀሳቀስ እንመክርሃለን፡፡

ከሼኽ ኢብን ባዝ (አላህ ምህረት ያድርግለትና) የተጻፈውን ከዚህ ርዕስ ጋር የተያያዘውን ምክር እናቀርብልሃለን፡፡ በጣልያን ሃገር ለሚኖር ሙስሊም በላከው ደብዳቤ ውስጥ እንዲህ አለ፡

በጣልያን ሃገር የምትኖር ሙስሊም ወጣት መሆንህን እና በመስቀል ጦረኞች ምኞት መሰረት ራሳቸውን ከእስልምና ትምህርት በማራቅ ከፉ ጠባይ እና መጥፎ ድርጊት ውስጥ የገቡ ብዙ ሙስሊም ወጣቶች መኖራቸውን በተመለከተ በደብዳቤህ ውስጥ ስለጠቀስካቸው ነገሮች...

ሺርክ እና ክርስትናን የመሳሰሉ የኩፋር እምነቶች በሚበዛበት ሃገር ውስጥ ለሥራ፣ ለንገድ፣ ለትምህርትም ሆነ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ መኖር የተከለከለ መሆኑን እነግርሃለሁ፡፡ ምክንያቱም አላህ እንዲህ ብሏልና፡

“እነዚያ (ለእምንት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ□» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን?» አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች!

ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃኖችም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይምመሩ ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም)

እነዚያም አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል፡፡ አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው፡፡”

ነቢዩም (የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁንና) “*በሙሽሪኮች* መካከል ከሚኖር ሙስሊም ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም” ብሏልና፡፡

የእስልምና ትክክለኛ ትርጉም የገባው፣ አላህ በሙስሊሞች ላይ የደነገገው ግዴታ የገባው እና በአላህ ጌትነት፣ በእስልምና ኃይማኖት እና በመሐመድ ነቢይነት (የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁን) ደስ የተሰኘ ሰው *በኩፋር* መካከል አይኖርም፡፡

«አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፣ መክሰሩዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልክተኛው በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደኾኑ አላህ ትእዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ» በላቸው፡፡ አላህም አመጸኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡" (አል-ተውባህ 9፡24) - ይህ የሚያሳያው ምድራዊ ጥቅሞችን መፈለግ ትክክለኛ የሸሪኣ ሰበብ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ ይልቁኑ ይህንን የሚያደርግ ሰው ፋሲቅ (አመፀኛ ክፉ አድራጊ) ነው፡፡ እነዚህ ነገሮ ከፊሎቹም ቢሆኑ ከአላህ፣ ከመልእክተኛው እና ከጂሃድ ይልቅ ለእርሱ የተወደዱ ቢሆኑ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንደማይመራ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶታል፡፡ አንተ እንደጠቀስካቸው ሙስሊም ተብዮዎች ሺርክን እና ሌሎች ክፋቶችን እያዩ ዝም ማለት እና እንዲያውም እነዚህ ነገሮች ማድረግ ምን መልካምነት አለው?

እዚያ የሚኖሩ እነዚህ ሙስሊሞች ትምህርት፣ ንግድ ወይንም ሥራን የመሳሰሉ ዓላማዎች ካሏቸው ይህ እንዲያውም ይብሳል፡፡

አላህ በመጽሐፉ ውስጥ መሰደድ አለመቻልን አስጠንቅቋል፡፡ ስለዚህ ወደ ካፊር ሃገር በመሄድ እዚያ ለመኖር ስምምነት የሚያደርገውስ ሰው? አንተ እንደጠቀስከው ሊቃውንት (አላህ ምህረት ያድርግላቸውና) ሙስሊሞች እምነታቸውን መለማመድ

ወደማይችሉበት ቦታ በመሄድ እንዳይኖሩ ከልክለዋል፡፡ ትምህርት፣ ለለንግድ ወይንም ለሥራ የሚሄዱትም መሰደድ የሚችሉ ከሆነ ተመሳሳይ ግዴታ አለባቸው፡፡

አንዳንዶች በሃገራቸው እየኖሩ እነርሱን መጥላታቸው እና መናቃቸው በቂ አይደለም፡፡ ነገር ግን በሚከተሉት እና በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ወደዚያ በመሄድ መኖር የተከለከለ ነው፡

1. አንድ ሰው ሙሉ ኃላፊነቱን መወጣት በማይችልበት ሁኔታ እምነቱን በግልፅ ማራመድ አይችልም፡፡
2. የሊቃውንት ንግግሮች እና ጽሑፎች በግልፅ እንደሚያሳዩት አንድ ሰው እምነቱን በማስረጃዎች አስደግፎ የማይረዳ ከሆነ እና *ከካፊሮች* የጥርጥር ክርክሮች መከላከል ካልቻለ ወደ ምድራቸው መሄድ ለእርሱ የተፈቀደ አይደለም፡፡
3. እዚያ ሄዶ መኖር የሚፈቀድበት አንዱ ሁኔታ አንድ ሰው ከእነርሱ የኃይል *ፊትና*፣ ቁጥጥር፣ የጥርጥር ክርክሮች እና ማማለል ነፃ ከሆነ እና እነዚህ ነገሮች ተፅዕኖ የማያሳድሩበት ከሆነ ነው፡፡
4. ወደ *ሺርክ* የሚመሩትን መንገዶች መዝጋት ከእስልምና አስፈላጊ መርሆች መካከል አንዱ ነው፡፡ ያለጥርጥር በሙስሊም ወጣቶች እንደደረሰባቸው በደብዳቤህ የጠቀስካቸው ነገሮች ሁሉ *በካፊር* ሃገር የመኖራቸው ውጤት ነው፡፡ ከሺርክ ምድር ወደ ሙስሊም ምድር

መሰደድ እስኪችሉ ድረስ በእምነታቸው ጠንካሮች፣ በግልፅ የሚለማመዱ፣ ትዕዛዛቱን የሚከተሉ፣ ክልከላዎቹን የሚከለከሉ እንዲሁም ሌሎችን ወደ እርሱ የሚጠሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡

አላህ ነገሮችንህን እንዲያቀና እና እምነቱን መረዳት እንድትችል እንዲሁም አትብቀህ እንድትከተለው እንዲረዳህ እንለምነዋለን፡፡ እርሱ የሚወደውን ነገር ማድረግ እንድንችል እና ወደ ስህተት ከሚመሩ ነገሮች እኛንም፣ አንተንም፣ ሙስሊሞችንም በሙሉ እንዲጠብቅ እንለምነዋለን፡፡ አላህ መልካም ነገሮችን እንድናደርግ ይርዳን፣ እምነቱንም ይደግፍ፣ ቃሉንም የበላይ ያድርግ፣ ሙስሊም መሪዎችን ያድሳቸው፣ እምነቱንም እንዲረዱ ይርዳቸው፣ በሸሪኣም ማስተዳደር እንዲችሉ ይርዳቸው፡፡ ሰላም፣ የአላህ እዝነት እና በረከት ባንተ ላይ ይሁን፡፡

መጅሙዕ ፈትዋ አል-ሼኽ ኢብን ባዝ (9/403)

አላህ እንዲመራህ፣ ነገሮችን እንዲያቀልልህ እና የትም ቢሆን ላንተ መልካም የሆነውን ማግኘት እንድትችል እንዲረዳህ እንጠይቀዋለን

አላህ የበለጠ ያውቃል፡፡

## ***ጭብጥ 8፡ በስደት ጊዜ ተምኪን እና ኢዳድን (ማስታጠቅ እና ዝግጅትን) የተመለከተ ኦፊሴላዊ ፈትዋ (በአረብኛ)***

የኛ አስተያየት፡ ይህ በሂጅራ ውስጥ ዝግጅትን እና ማስታጠቅን የተመለከተ ቁልፍ የሆነ የዘመናችን ፈትዋ (እስላማዊ ህጋዊ መመርያ) ነው፡፡ በዚህ ዋና ጉዳይ ላይ ከቁርአን እና ከሐዲስ በመጥቀስ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ በደራሲያኑ የተዘጋጀ ሙሉ ትርጉም ነው፡፡ www.islamweb.net ከሚል ድህረ ገፅ ላይ የተወሰደው ዋናው አረብኛ ቃል በቃል ተቀምጧል፡፡

ጥያቄ፡ የተከበሩ ሼኽ፣ ሙስሊሞች በወታደራዊ ዘመቻዎቻቸው ድልን ያገኙባቸውን ምክንያቶች የሚናገሩ ሐዲሶችን ወይንም የቁርአን *አያዎችን* (ቁጥሮችን) ግልፅ እንዲያደርጉ እፈልጋለሁ፡፡

የፈትዋ ርዕስ፡ ለሙስሊሞች ሁሉ ድል (ናስር) እና ማስታጠቅ (ተምኪን) የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፡፡

ፈትዋ ቁጥር 27216

ቀን፡ 6-ዝሁል-ቂዕዳ-1423 ሂጅሪ፡፡

ከተለመደው የአላህ፣ የመሐመድ እና የተከታዮቹ ምስጋና ቀጥሎ የሚገኘው የፈትዋ ጽሑፍ፡

በሱራ 24፡55 መሰረት ቅዱስ ቁርኣን ለድል እና ለማስታጠቅ (ናስር እና ተምኪን) የሚሆኑ ሁኔታዎች ሙሉ ማብራርያዎችን በውስጡ ይዟል

አላህ እንዲህ በማለት ቃል ገብቷል፡ አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ለይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፡፡ በእኔ ምንንም የማያጋሩ ኾነው ይግገዙኛል፡፡ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው እነዚያ እነርሱ አመጸኞች ናቸው፡፡

እንዲሁም ሱራ 22፡41

(እነርሱም) እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቸው ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፣ ዘካንም የሚሰጡ፣ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፣ ከመጥፎ ነገርም የሚከለክሉ ናቸው፡፡ የነገሮቹም ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ነው፡፡

ስለዚህ በመጀመርያው ሱራ መሰረት የማስታጠቅ (ተምኪን) መመርያዎች፡

1. በእስልምና፣ በትርጉሞቹ ሁሉ እና በአዕማዶቹ ሙሉ የሆነ ራስን የመስጠት እምነት
2. መልካም ሥራዎች
3. የአላህ ባርያ መሆንን መረዳት

4. “ሺርክን” (ክርስትናን ጨምሮ መድብለ አማልክታዊነትን) መዋጋት እና ከእርሱ እና እርሱን ከሚያምኑ ሰዎች እጅን መታጠብ፡፡
5. እስላማዊ የሥርአት ፀሎቶችን መፈፀም (በቀን አምስት ጊዜ)
6. ዘካት የሚባለውን እስላማዊ ታክስ መክፈል
7. ለመልእክተኛው መታዘዝ
8. ትክክል የሆነውን *(ማዐሩፍ)* ማዘዝ እና መጥፎ የሆነውን *(ሙንካር)* መከልከል {ትክክል እና መትፎ በእስልምና ከምዕራባውያን አመለካከት በጣም በተለየ ሁኔታ ነው የሚተረጎመው}

- *ሊዳድ* (በቁጥር እና በትግበራ መንገዶች መዘጋጀት) በሱራ 8፡60 መሰረት

ለእነሱም ከማንኛውም ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) የምታሸብሩበት ስትኾኑ አዘጋጁላቸው፡፡ ከማንኛውም ነገር በአላህ መንገድ የምትለግሱትም ምንዳው ወደናንተ በሙሉ ይሰጣል፡፡ እናንተም አትበደሉም፡፡

መልእክተኛው በተልእኮው *(ዳዕዋ)* ውስጥ እና በወታደራዊ ዘመቻዎቹ ውስጥ የተባሉትን በሙሉ እያንዳንዱን ጥቃቅን ነገር

ሳይቀር ተግብሯል፡፡ በሂጅራው ውስጥ (ከመካ ወደ መዲና ባደረገው ስደት) ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ነገር ኃላፊነትን ወስዶ ነበር፣ ለመንገዶች እና ለመንገድ መሪዎች፣ ለራሱ እና ለተከታዮቹ የመደበቂያ ቦታ ነገሮችን አመቻችቶ ነበር፡፡ ጥንቃቄን እና ሚስጥራዊነትንም ተጠቅሞ ነበር፡፡ ይህንን ሁሉ በድር፣ ኡሁድ፣ አሕዛብ እና በመሳሰሉት ወታደራዊ ዘመቻዎቹ ወቅት ተግብሮ ነበር፡፡

- *ዲኑን* (እስላማዊ *ሥርአት*) የማስፋፋት እና የጂሃድን ኃላፊነት የወሰዱ ሰዎች ኃይማኖታዊ ዝግጁነት *(ረባኒአህ)፣* መልእክተኛው ከተጠራበት ጊዜ ጀምሮ ለራሱ ዝግጁነት *(ኢዳድ)* የተጠቀመበት ነው፡፡ ተከታዮችን ጥንቃቄ በተሞላበት ኃይማኖታዊ መንገድ መሰረት በፀጥታ፣ ቀስ በቀስ እና በሚስጥር ያዘጋጃቸው ነበር፡፡ ሱራ 62፡2 እንዲህ ይላል፡

እርሱ ያ በመሃይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን) በእነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣ (ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልክተኛ (ሙሐመድን) ከእነርሱው ውስጥ የላከ ነው፡፡ እነርሱም ከእርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ፡፡

እንዲሁም ሱራ 18፡28 እንዲህ ይላል፡

ነፍስህንም፤ ከእነዚያ ጌታቸውን ፊቱን (ውዴታውን) የሚሹ ኾነው በጧትና በማታ ከሚግገዙት ጋር አስታግስ፡፡ የቅርቢቱንም ሕይወት

ሽልማት የምትሻ ሆነህ ዓይኖችህ ከእነሱ (ወደ ሌላ) አይለፉ፡፡ ልቡንም እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውን ፍላጎቱንም የተከተለውን ነገሩም ሁሉ ወሰን ማለፍ የሆነውን ሰው አትታዘዝ፡፡

እንዲሁም ሌሎች የድል ምክንያቶች መለያየትን መዋጋት እና አንድነትን መደገፍ ናቸው፣ ሱራ 3፡103 ላይ እንደተጠቀሰው፡

የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ፡፡ አትለያዩም፡፡ ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ፡፡ በልቦቻችሁም መካከል አስማማ፡፡ በጸጋውም ወንድማማቾች ኾናችሁ፡፡ በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ፡፡ ከእርስዋም አዳናችሁ፡፡ እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ለእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል፡፡

ሌላው የድል ምክንያት በመልእክተኛው ሁሉም ሂጅራ፣ ወታደራዊ ዘመቻዎች እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደታየው በጥንቃቄ ማቀድ ነው፡፡

አንባቢው በአሊ ሳላቢ የተጻፈውን “የእስላማዊ ዝግጅት *(ተምኪን)* ህጋዊ አካሄድ” የሚለውን መጽሐፍ እንዲያነብ ተጠቁሟል፡፡

የፈትዋ 27216 መጨረሻ

በፈትዋ 68173 ውስጥ አንባቢው “ሰው ምድርን የመውረስ” ትርጉም ምን እንደሆነ ይጠይቃል፡፡

መልሱም ሱራ 2455 እና 22፡41 በመጥቀስ በባለፈው ፈትዋ መሰረት "ምድርን መውረስ ማለት ኃብቶቿን እና በውስጥዋ የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ መቆጣጠር ነው" የሚል መልስ ተመልሷል፡፡ በተጨማሪም "አላህ እስልምናን ለሚከተሉ ሰዎች በመንፈሳዊም ሆነ በአዕምሮ ምድርን የራሳቸው እንዲደርጉ እና በውስጥዋ የሚኖሩትን ሁሉ እንዲቆጣጠሩ ቃል ገብቶላቸዋል፡፡"

አንባቢው በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጡትን ፈትዋዎች እንዲያነብ ይመከራል፡፡

10091 //27216 //14678 //40112

## *ጭብጥ 9፡ እስላማዊ ባልሆነ ሃገር ውስጥ በመኖር ላይ የተሰጡ መመርያዎችን የሚያብራሩ የድህረ ገፅ አምዶች*

የኛ አስተያየት፡ በሚከተለው ውስጥ በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱት አስተምህሮዎች ጋር የተያያዙ ብዙ መመርያዎችን እናገኛለን፡፡

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=714

ةرورضـل وأ ةحلصـــم ةجاح زوجت لا ةمـاقلإا دلابــب كـلا راف لاإ

(አስፈላጊ ወይንም ጠቃሚ ላልሆነ ጉዳይ በከሃዲዎች ሃገር ውስጥ መኖር ይፈቀዳልን)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=1204

لا حصــي بلـــط ةيســـنج ةلـود ةرفـــاك لاإ ةرورضـل

(አስፈላጊ ለሆነ ነገር፣ ለደሩርዓ ካልሆነ በስተቀር የከሃዲ ሃገር ዜጋ መሆን ይቻላልን)

http://63.175.194.25/index.php?ln=ara&ds=qa&lv=browse&QR=14235&dgn=3

ّ◌ مكـح ســـــنجتلا ةيســـــنجلاب ةيـــبروأ ملســـلل ؟

(ለሙስሊሞች የአውሮፓ ዜጎች መሆንን በተመለከተ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=1818

لا زوجي رفســـلا ىلإ دلاب رفكــلا دصـــقل هـــزنتلا

(ሙስሊም ለእረፍት ወይንም ለጉብኝት ወደ ከሃዲ ሃገር መሄድ የተፈቀደ አይደለም)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=1620

نا إ تعطتسا لامكإ ةساردلا يف كدلب وهف لضفأ

(ከተቻለ ትምህርትህን በሙስሊም ሃገር ውስጥ መጨረስ አለብህ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=2007

لاإ دلاب ريغ نيملسملا لاإ يف لاح ةرورضلا
لا زوجت ةرجهلا نم دلاب نيملسملا

(ለደሩርዓ ካልሆነ በስተቀር ከሙስሊም ሃገር ሙስሊም ወዳልሆነ ሃገር መሰደድ የተፈቀደ አይደለም)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=7517

راد ملاسلإا رادو برحلا

(የጦርነት ቤት)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=3732

ةماقلإاو يف ةلود ةرفاك طارخنلااو يف اهشيج
مكح سنجتلا

(የከሃዲ ሃገር ነዋሪ እና ዜጋ በመሆን እንዲሁም በውትድርና ማገልገል ላይ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=3562

مكح لاحترلاا نع دلب ملسم

(ከሙስሊም ሃገር ለቆ በመሄድ ላይ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=5045

زوجت ةمــاقلإا يــف دلاب رافكـــلا اذإ تنـــاك ضـرغل ةوعدلا

(ለዳዕዋ አላማ በከሃዲ ሃገራት መኖር የተፈቀደ ነው)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=6341

سـردي ميقيـــو يــف نكامــأ ةطلتخـــم فيـــك ظفحـــي همايص ؟ نــم

(ሁሉን አቀፍ በሆነ ሃገር ውስጥ የሚኖር ሙስሊም እንዴት መማር፣ መኖር እና መፆም እንደሚችል)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=25591

مكـح ةماقـإ ةاتفـــلا يــف نكــس يعمـــاج يــف ةلــود ةرفـــاك

(ወጣት ሙስሊም ሴቶች በከሃዲ ሃገራት በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚችሉ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=12716

مكـح رفســـلا دلابـــل رفكـــلا لجـــلأ جاوزلا

(ለጋብቻ ወደ ከሃዲ ሃገራት በመሄድ ላይ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=16686

ةرجهـلا بلـــع ةثــلاث برضــــأ

(የሂጅራ ጊዜ ሦስት!)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=15708

طورش زاوج ةناعإ ديرم هلاةرج ىلإ دلاب رفكلا

(ወደ ከሃዲ ሃገራት ሂጅራ የሚያደርግን ሙስሊም በመርዳት ላይ የተሰጠ መመርያ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=15784

ةماقلإا يف دلاب رفكلا لجلأ ةوعدلا داهج

(ለጂሃድ ጥሪ በከሃዲ ሃገር ውስጥ መኖር)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=17601

دق دجوت تلااح لعجت نكسلا يف دلاب رفكلا لضفأ

(በከሃዲ ሃገራት መኖርን መምረጥ የሚስችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=18886

ورضلاةر ددحت زاوج فلحلا ذخلأ ةيسنجلا نم همدع ةيعون

(ዜግነትን ለማግኘት ቃልኪዳን የመፈፀም የደሩርዓ ዓነቶች)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=18462

فيك طاتحي ملسملا هنيدل يف دلاب رفكلا

(ሙስሊም በከሃዲ ሃገር እስልምናውን ለመጠበቅ ምን ምን ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለበት)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=20063

لــه صــخرت ةرجهلا رايــدل رفكـــلا نيســـــحتل ةشـــيعملا

(የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል ወደ ከሃዲ ሃገራት ሂጅራ ማድረግ የተፈቀደ ነውን?)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=20969

ةيعـــرش ... ةبغـــر بـــلأا يـــف ةسارد هنبـــا يـــف رايـــد رفكـــلا ةرظن

(አባት ልጁን ለትምህርት ወደ ከሃዲ ሃገር ለመላክ ማሰቡን በተመለከተ የሸሪአ የሕግ አካሄድ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=21567

رذعلا رهــاقلا عفـــري مثـــإ ةمـــاقلإا يـــف دلاب رافكـــلا

(በከሃዲ ሃገር በመኖር የተፈጠረውን ወቀሳ ለማንሳት የሚደረግ ሰበብ)

http://islamweb.net/pls/iweb/fatwa.showSingleFatwa?FatwaId=23444

http://www.abubaseer.bizland.com/books/download/b33.zip

ةرجهلا لئاســــم

" دبـــع معنمـــلا نفطصـــــم ةميلـــح : فيـــلأت . ماكحأو .. " وبـــأ ريصـــب

(“ከሂጅራ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች እና መመርያዎች” በኤ.ኤም. ሐሊማህ የተጻፈ መጽሐፍ)

http://www.islamway.com/arabic/images/lessons//othymeen//mafased1.rm

حلاص نيميثعــــلا . دســـافم رفســـلا ىــلإ دلاب رفكــلا
1 ءز جلا . دمحم نـب

(ወደ ከሃዲ ሃገራት የመሄድ ክፉቶች፣ በሼም ቢ ኤስ አል-ኡሳይማይን፣ ክፍል 1)

http://www.islamway.com/arabic/images/lessons//othymeen//mafased2.rm

حلاص نيميثعــــلا . دســـافم رفســـلا ىــلإ دلاب رفكــلا
2 ءز جلا . دمحم نـب

(ወደ ከሃዲ ሃገራት የመሄድ ክፉቶች፣ በሼም ቢ ኤስ አል-ኡሳይማይን፣ ክፍል 2)

# አባሪ - ለ

**በሙስሊሞች መካከልም ሆነ ከዚያ በሻገር በሸሪአ መመርያ መሰረት የሚከወን ከእቅድ ጀምሮ እስከ ትግበራ ድረስ ያለው የእስላማዊ አስተምህሮ እድገት**

